ዘርፈ ብዙ ምላሽ ለአዕምሮ ጤና

ገጽ 9

የልጅን ለቅሶ ሸሸት

ገጽ 11

በእናት ጥላ ስር

ገጽ 16

ኢፕድ
አዲስ ዘመን
84ኛ ዓመት ቁጥር 032 ጥቅምት 2 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ታማኞቹ የልማት አርበኞች

ጌትነት ምሕረቴ

**ዜና ሐተታ**

መስከረም 30 ቀን 2017 ዓ.ም ኢትዮጵያ ለክብሯ የሚተጉትን፣ ለልማት ቀና የሆኑ ድርጅቶችን ሸልማለች። በአንድነት ፓርክ ግቢ ውስጥ በሚገኘው ሰፊው የግብር አዳራሽ ከፍተኛ ግብር ከፋይ ድርጅቶች የስድስተኛው ዙር የታማኝ ግብር ከፍዮች የምስጋናና የዕውቅና ሽልማት መርሐ ግብር ተካሂዷል። ታማኝነታቸውን በተግባር ላረጋገጡት ታታሪዎች ምስጋና አቅርባለች።

በዚህ መድረክ በተለያዩ መስፈርቶች 66 ድርጅቶች በፕላትኒየም፣ 165 ኩባንያዎች በወርቅ፣ 319 ኩባንያዎች የብር ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆነዋል። 20 ድርጅቶች ደግሞ ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት በታማኝነት ከፍተኛ ግብር በመክፈላቸው ልዩ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። ከእነዚህ በታማኝነት ግብር በመክፈልና በሕግ ተገዥነት ዕውቅናና ሽልማት ከተበረከተላቸው ድርጅቶች መካከል ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ አንዱ ነው።

ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ በስሩ ስምንት እህት ኩባንያዎች አሉት። ከእነዚህ እህት ኩባንያዎች መካከል ናሽናል ሲሚንቶ የፕላትኒየምና ልዩ ተሸላሚ ሆኗል። አራት ድርጅቶቻቸው የወርቅ ተሸላሚ ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ የብር ተሸላሚ መሆናቸውን የሚገልጹት የኩባንያው ዋና ሥራ


አቶ ብሩ ወልዴ


አቶ መልካም አሰፋ


አቶ ፍሴራ ድንቁ

ፎቶ፡ ዳኒ አበበ

አስፈጻሚ አቶ ብሩ ወልዴ ናቸው።

"ለዚህ ሽልማት የበቃነው በታማኝነትና በሕግ ተገዥነት ከፍተኛ ግብር በመክፈላችን ነው። በ2016 በጀት ዓመት ብቻ ናሽናል ሲሚንቶ ብቻ 3 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ግብር ከፍሏል የሚሉት አቶ ብሩ፤ ሀገር የምትገነባው በዕርዳታ ሳይሆን ከምታገኘው የውስጥ ገቢ ነው። ይህ ሁሉ የሚታየው መንገድ፣ ባቡር፣ ኤሌክትሪክ፣ የውሃና ሌሎች መሠረተ ልማቶች የተገነቡት በሀገር ውስጥ ገቢ ነው" ብለዋል።

ግብር ከልማት ባሻገርም በኅብረተሰቡ መካከል ፍትሐዊነት የማረጋገጫ መንገድም መሆኑን የሚገልጹት አቶ ብሩ፤ ከዚህ ሁለንተናዊ ጥቅሙ አኳያም ሁሉም ነጋዴም ሆነ ዜጋ በታማኝነት ግብር መክፈል ይኖርበታል ይላሉ።

የእሳቸው ኩባንያም ግብር በመክፈል ታማኝነቱን በአግባቡ በመወጣቱ ለዚህ ሽልማት መብቃቱን ገልጸው፤ ሀገርን ለማልማትና ከድህነት ለመውጣት ተግቶ መሥራትና ከሚገኘው ገቢ በታማኝነት ግብር መክፈል ለከፋዩም፤ ለሀገርም ክብር መሆኑን ነው የገለጹት።

ታማኞቹ የልማት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት 12 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል

ገጽ 4


ሠሳማዊት ካሳ

## ኢትዮጵያ በያዝነው ወር አሕጉርና ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን ታስተናግዳለች

ሄለን ወንድምነው

**አዲስ አበባ፡-** ኢትዮጵያ በተያዘው የጥቅምት ወር ለኮንፈረንስ ቱሪዝም አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ የተለያዩ አሕጉርና ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን ለማስተናገድ

ኢትዮጵያ በያዝነው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## "የአዲስ አበባ የምገባ ማዕከላት ዓለም አቀፍ ተሞክሮን የሚሰጡ ናቸው"

-የተለያዩ ሀገራት ጎብኚዎች

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በተለያዩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የምገባ ማዕከላት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሞክሮ የሚሰጡ መሆናቸው ተገለጸ።

የሚላን የከተማ የምግብ ፖሊሲ ስምምነት አባል ሀገራት በመዲናዋ ባሉ የምገባ ማዕከላት ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት እንደገለጹት፤ በከተማዋ ተግባራዊ ከተደረጉ ምርጥ ተሞክሮዎች መካከል ሁሉንም ያማከለው የትምህርት ቤት ምገባ እንዲሁም የማኅበረሰብ ምገባ ፕሮግራም እንደ "ሞዴል" ተወስዶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ማስተማሪያ መሆኑን ገልጸዋል።

ኬኒያዊው ኤሪክ አጋሉ በጉብኝቱ ወቅት እንደተናገረው፤ ማዕከላቱ እየሰጡ ያሉት የምገባ አገልግሎት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሞክሮን የሚሰጡ በመሆናቸው አጋር አካላት ይህንን ተግባር ሊደግፉ ይገባል።

"የአዲስ አበባ የምገባ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ፡ ዳኒ አበበ



# የሳይበር ደኅንነትን ቀዳሚ ሀገራዊ አጀንዳ በማድረግ የዲጂታል ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ ይገባል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡ የሳይበር ደኅንነትን ከሀገራዊ አጀንዳቻችን መካከል ግንባር ቀደም በማድረግ ዲጂታል ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ እንደሚገባ የብሔራዊ ባንክ ገዥ አስታወቁ።

"የቁልፍ መሠረተ-ልማት ደኅንነት ለዲጂታል ሉዓላዊነት" በሚል መሪ ቃል ለአንድ ወር የሚካሄደው 5ኛው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደኅንነት ወር በትናንትናው እለት ተጀምሯል።

በመድረኩ ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምሕረቱ እንደገለፁት፤ ወሳኝ የሆኑ መሠረተ ልማቶች ለሳይበር ጥቃት ከተጋለጡ የየትኛውም ሀገር ሉዓላዊነት ለአደጋ ይዳረጋል። በመሆኑም የሳይበር ደኅንነትን ግንባር ቀደም ሀገራዊ አጀንዳ በማድረግ የዲጂታል ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ ይገባል።

ወሳኝ መሠረተ ልማቶችን ከጥቃት ለመጠበቅም ጠንካራ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፎችን፣ ሀገራዊ የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን፣ በዘርፉ ብቁና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ኃይል ማልማት የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸዋል።

የሀገሪቱን ወሳኝ መሠረተ ልማቶች ከጥቃት መጠበቅ የሳይበር ጥቃቶችን መከላከል ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ በዲጂታል ዘመን ሉዓላዊ፣ ነፃ እና ጠንካራ ሆና እንድትቀጥል በማድረግ የሀገሪቱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ መጠበቅ መሆኑንም አንስተዋል።

ቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር ደኅንነት ሥርዓት እንዲዘረጉና አስፈላጊውን የምላሽና የቅድመ መከላከል ሥራ እንዲሠሩ በማድረግ፣ ደኅንነታቸው የተረጋገጡ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምና በየጊዜው ፍተሻና ግምገማ በማድረግ የሳይበር ደኅንነትን ከጥቃት መጠበቅ ይገባል።



አቶ ማሞ ምሕረቱ

በተጨማሪም የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን በማጠናከር የቁልፍ መሠረተ ልማት ተቋማት የሚያጋጥሟቸውን የሳይበር ጥቃቶችም ሆነ ስጋቶች በቶሎ እንዲያሳውቁ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ መለዋወጫ ሥርዓት መገንባት የሚያስፈልግ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ማሞ እንደ ሀገር የዲጂታል መሠረተ ልማታችንን ስንገነባ እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከወሳኝ ሥርዓታችን ጋር ስናዋሕድ፣ የግድ በንቃትና በጥንቃቄ ሊከወን እንደሚገባም ጠቅሰዋል።

በመሆኑም ኢትዮጵያም የዲጂታል ሀብቶቿን የመከላከል እና የመጠበቅ፣ ነፃ የቴክኖሎጂ ውሳኔዎችን የመወሰን እና የዜጎቿን ደኅንነት እና ግላዊነት የማረጋገጥ አቅም ሊኖራት ይገባል። ወሳኝ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ለመጠበቅ እያንዳንዱ የመንግሥት ተቋምም ሆነ ግለሰብ ሚናውን ሊወጣ እንደሚገባ ተናግረዋል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ትዕግስት ሃሚድ በበኩላቸው፤ የሳይበር ወር መከበር ዋና ዓላማ የማኅበረሰቡን የሳይበር ደኅንነት ግንዛቤን ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ የንቅናቄ መርሐ ግብሮችን ለማከናወን መሆኑን ገልፀዋል።

ዘንድሮም ለ5ኛ ጊዜ የምናከብረው የሳይበር ደኅንነት ወር ዋነኛ ትኩረት የሀገሪቱን ቁልፍ መሠረተ ልማቶች እና ተቋማት የሳይበር ደኅንነት በመጠበቅ የሳይበር ሉዓላዊነታችንን ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው ብለዋል።

በመሆኑም ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ እድገት ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ጥቃት በሚደርስባቸው ጊዜ በዜጎች እንዲሁም በሀገር ብሔራዊ ጥቅም እና ደኅንነት ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ጠንካራ ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ገልፀዋል።

በሀገሪቱ በ2015 ዓ.ም 6959 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች የደረሱ ሲሆን በ2016 ዓ.ም ወደ 8854 ከፍ ብሏል። ይህም ከዓመት ወደ ዓመት የሳይበር ጥቃት ቁጥሩ እያሻቀበ መሄዱን የሚያመላክት መሆኑን አስታውቀዋል።

በየዓመቱ የሚካሄዱ የሳይበር ደኅንነት የንቅናቄ መርሐ ግብሮች የሳይበር ደኅንነት ተጋላጭነት እና ወቅታዊ የሳይበር ደኅንነት ትኩረት አኳያ ለዜጎች፣ ለተቋማት እንዲሁም ለሚመለከተው ለዘርፉ ማኅበረሰብ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።



አቶ ቦሩ ሸና

# ኢንስቲትዩቱ ከ300 ሺ በላይ ለሚሆኑ ግለሰቦች የቢዝነስና አመራር ክህሎት ሥልጠና ሰጥቷል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ከ300 ሺ በላይ ለሚሆኑ ግለሰቦች የቢዝነስና አመራር ክህሎት ሥልጠና መስጠቱን የኢትዮጵያ ኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት ገለጸ።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት ምክትል ዳይሬክተር ቦሩ ሸና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢንስቲትዩቱ ከተቋቋመ አስር ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን በነዚህ ዓመታትም ክህሎትን መሠረት ያደረገ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ ለመገንባት እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል።

አቶ ቦሩ፤ ተቋሙ ከሥራ ፈጣሪ ወጣቶች ጋር እንዲሁም ከአነስተኛ ቢዝነስ ባለቤቶች ጋር የቢዝነስ እይታን ከፍ የሚያደርጉ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ሥልጠናዎችን በተለያዩ ጊዜዎች ሲሰጥ መቆየቱን ገልጸዋል።

የተቋሙ ዋና ዓላማ ግለሰቦች እንዲሁም ተቋማት ችግር የመፍታት ባሕልን እንዲያዳብሩ ማገዝ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ ተቋሙ ሥራ በጀመረባቸው ዓመታት ውስጥም ከ 300 ሺ በላይ ለሚሆኑ ሥራ ፈጣሪዎች ቢዝነስና አመራር ላይ ያተኮሩ ሥልጠናዎችን መስጠቱን ገልጸዋል።

ያሠለጠናቸው በርካታ ሰዎችም የንግድ ድርጅት መክፈታቸውና በሥልጠናው ተነሳሽነት የንግድ ድርጅታቸውን አስፋፍተው የሥራ ዕድል የፈጠሩ ግለሰቦች በርካታ መሆናቸውን ገልጸዋል።

አቶ ቦሩ ሥራ ፈጣሪዎች ይዘውት የሚመጡት ሀሳብ ወደ መሬት ወርዶ ውጤታማ እንዲሆን ከነሱ ጥረት በተጨማሪ የተለያዩ የመንግሥት የሥራ አስፈጻሚዎች ድጋፍን የሚሻ ነው ያሉ ሲሆን ለዚህም ኢንስቲትዩቱ የኢንተርፕርነር ዘርፍ ላይ የሚሠሩ የመንግሥት አካላትንም ሲያሠለጥን መቆየቱን ተናግረዋል።

በአሁኑ ሰዓትም ለ90 የመንግሥት ተቋማት አመራር ላይ ትኩረት ያደረገ ሥልጠና እየሰጠ ሲሆን ይህ ሥልጠናውም የተቋማት የሥራ ባሕል መቀየሩንና በተለይም በዩኒቨርስቲዎችና በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ውስጥ ቆመው የነበሩ ወርክሾፖች ወደ ተግባር መግባታቸውን ገልጸዋል።

ተቋሙ ከሥልጠና በተጨማሪም የሀገሪቱ ሥነ ምኅዳር ለሥራ ፈጣሪዎች የተመቸ እንዲሆን የሚያግዙ ኢንሼቲቮችን ማዘጋጀቱና በዛም ኢንቨስተሮችና ስታርትአፖች ትስስር እንዲፈጥሩ በማስቻል ወጣቶች ሃሳባቸው ተግባራዊ ሆኖ ለበርካቶች የሥራ ዕድል ሲፈጥሩ እየተስተዋለ ይገኛል ብለዋል።

አቶ ቦሩ የማኅበረሰቡን ችግሮች የማቃለልና ሀገርን ሊያሳድግ የሚያችል ትልልቅ ሀሳብ ያላቸው ወጣቶች እየተፈጠሩ መሆናቸውን በመግለጽ እነዚህን ወጣቶች መደገፍ እንደሚገባ ገልጸዋል።




# ታዳጊ ሴቶች እየተጋፈጡት ያለውን ፈተና እንዲሻገሩ ለማስቻል በጋራ መረባረብ ይገባል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ታዳጊ ሴት ልጆች እየተጋፈጡት ያለውን ፈተና እንዲሻገሩ ለማስቻል በጋራ መረባረብና ትኩረት ሰጥተን መሥራት ይገባል ሲል የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር አስታወቀ።

ዓለም አቀፉ የታዳጊ ሴቶች ቀን በዓለም ለ14ኛ፤ በሀገራችን ለ13ኛ ጊዜ "ታዳጊ ሴቶች ላይ መሥራት የነገን የተሻለች ሀገር መገንባት ነው" በሚል መሪ ሀሳብ በትናንትናው እለት ተከብሯል።

በበዓሉ የኢፌዴሪ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)፤ ታዳጊ ሴት ልጆች እየተጋፈጡት ያለውን ፈተና እንዲሻገሩ ለማስቻል በጋራ መረባረብና ትኩረት ሰጥተን መሥራት ይገባናል ብለዋል።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ያለ እድሜ ጋብቻ፣ ፆታዊ ጥቃት፣ የአቻ ግፊት እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ሴቶች መድረስ ያለባቸው ቦታ እንዳይደርሱ ምክንያት ናቸው።

የቀኑ መከበር የታዳጊ ሴቶች ድምፅ እንዲሰማ፣ መብታቸው እንዲከበር እንዲሁም ያሉባቸው ስጋቶች ላይ ተግባራዊ ምላሽ እንዲሰጥ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት የፆታ እኩልነትን ለማስፈን እንዲሁም ሴቶችን ለማብቃት ቁርጠኛ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ ወደፊትም በሴቶች መብት ዙሪያ እየታዩ ያሉ ተግዳሮቶችን በዘላቂነት ለመፍታት አበክሮ ይሠራል ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሴቶች ፊት ያሉ እንቅፋቶችን ለማንሳት በርካታ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑንና አሁን ላይ በርካታ ችግሮች ስላሉ በቅንጅት መሥራት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል።

ታዳጊና ወጣት ሴት ልጆችም አቅማቸውን እንዲያጎለበቱ፣ ጠንካራ ሥነልቦና እንዲያዳብሩ፣ ታላቅ ሕልም ማለምና ትልልቅ ዓላማዎችን ለማሳካት እንዲተጉ መክረዋል።

ሕልማቸውን ከሚያደናቅፉ እና ከትምህርት ገበታቸው ወደ ኋላ እንዲቀሩ ከሚያደርጉ የአቻ ግፊቶችም እንዲጠበቁ አደራ ብለዋል።

የሀገራችን የወደፊት ተስፋ በመሆናቸው ያላቸውን እምቅ አቅም በመጠቀም ትልቅ ነገርን ማስመዝገብና ማሳካት እንዲችሉ መደገፍ እንደሚገባ ተናግረዋል።

የሴቶችና ሕፃናት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሂክማ ከይረዲን በበኩላቸው፤ ቀኑ ታዳጊዎች ስጋትና ጥያቄያቸውን አንስተው የሚወያዩበት እንዲሁም ጠቃሚ ልምዶችን እርስ በእርስ መለዋወጥ የሚችሉበትን ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ገልፀዋል።

በበዓሉ ላይ የታዳጊ ሴቶች ፍላጎትና ጥያቄ የተንጸባረቀበት የስዕል ዓውደ ርዕይ የተጎበኘ ሲሆን ሌሎች የኪነጥበብ ሥራዎችና በሀገር አቀፍ ደረጃ የላቀ አገልግሎት በመስጠት አርዓያ የሆኑ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሴቶች ዕውቅና እንዲያገኙ ተደርጓል።

# የፍርድ ቤት አሠራርን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የተጀመሩ ሥራዎች በ2017 ወደ ሙሉ ትግበራ ይሸጋገራሉ

## -የ2017 ዓ.ም መደበኛ የዳኝነት ሥራ ተጀመረ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የፍርድ ቤት አሠራርን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የተጀመሩ ሥራዎችን ወደሙሉ ትግበራ ለማስገባት ትኩረት እንደሚደረግ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ገለጸ። የ2017 ዓ.ም መደበኛ የዳኝነት ሥራ ተጀምሯል።

መደበኛ የችሎት ሥራን ያስጀመሩት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምሕረት፤ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎትን በማሳደግ የተጀመሩ ቅንጅታዊ ፕሮጀክቶችም ወደሙሉ ትግበራ ይሸጋገራሉ ብለዋል።

የዳኝነት አገልግሎቱን ለተገልጋይ ምቹ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ የማድረግ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚተገበር ተናግረዋል።

በዋናነት የዳኝነት ሥራውን ለማቀላጠፍና ተገማች ለማድረግ የሚያስችሉ የተጀመሩና በዚህ ዓመት የሚጠናቀቁ ሥራዎች አሉ ብለዋል።

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ደረጃ ሦስት ፕሮጀክቶች ተጀምረዋል ያሉት አቶ ቴዎድሮስ፤ ስማርት ኮርት ሩም ትግበራ አንዱ መሆኑን ተናግረዋል። የማስቻያ ቦታዎች በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ መረጃዎች በዲጂታል መንገድ እንዲያዙ የሚያስችሉ ግልጽነትንም የሚያረጋግጡ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም አገልግሎት ማዳረስን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።



አቶ ቴዎድሮስ ምሕረት

ከአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የሚሠራ ሲሆን በውስጡም በርካታ ነገሮች ማካተቱን ጠቁመው፣ ቻትቦት ያለው እንደሆነና ተገልጋዮች ከሌላ ቦታ ሆነው ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተያያዘ ቅሬታ የሚያቀርቡበት፣ ሌላው ደግሞ መረጃ የሚያገኙበት ነው ሲሉ በአብነት ጠቅሰዋል።

የመረጃ ማዕከሎች በሦስቱ ፍርድ ቤቶች ተደራጅተው ባለጉዳዮች በቦታው ተገኝተው መረጃ ያገኙበት የነበረውን አሠራር በዌብሳይትና በተሠራው የሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም መረጃ የሚያገኙበት አሠራር መጀመሩንም ጠቁመዋል።

በፍርድ ቤቱ ኔት ወርክ በመጠቀም አገልግሎት የሚሰጥበት የቪዲዮ ኮንፍረንስ አሠራርን የሚያካትት መሆኑን፣ የምስልና የድምፅ ቀረፃን እንዲሁም ከድምፅ ወደ ጽሑፍ የመቀየሪያ ሥርዓትንም እንደሚያካትትም አመልክተዋል። ትግበራው በሙከራ ደረጃ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲሠራ ቆይቶ ወደትግበራ መሸጋገሩንም አመልክተዋል።

ዘንድሮ ትግበራውን የማስፋፋት ሥራ እንደሚሠራ የተናገሩት አቶ ቴዎድሮስ፤ የማስፋፋት ሥራው በፌዴራል ደረጃ ብቻ ሳይሆን በክልሎች፤ በሐረሪ ሕዝብ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በሲዳማ ክልሎችና በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች የማስፋፋት ሥራ ይቀጥላል ብለዋል።

ሁለተኛው ዋይድ ኤሪያ ኔትወርክ በሚል የሚጠራ መሆኑን በመጠቆምም፤ የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን በሙሉ በኔትወርክ በማስተሳሰር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ፕሮጀክት ሲሆን ሥራው 78 በመቶ መጠናቀቁን ተናግረዋል።

በፍርድ ቤት የሚሠሩ ሥራዎች ዲጂታል በሆነ መልክ አገልግሎት መስጠት የሚያስችለው ሦስተኛው ፕሮግራም መሆኑን የገለጹት አቶ ቴዎድሮስ፤ የተጀመረው ሥራ ዘንድሮ ይጠናቀቃል ተብሎ እንዲታሰብ አመልክተዋል።

በውስጥ አቅም እና ከሌሎች የውጭ አካላት ጋር የሚሠሩ ሥራዎች አሉ ብለዋል። ከአርካይቭ ጋር የተያያዘ በዚህ ዓመት የሚሠራ ሥራ ይኖራል፣ በዋናነት የዳኝነት ሥራውን ለማቀላጠፍ፣ ተገማች ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው።

የዳኞችን ተነሳሽነት የሚያሳድጉ ምቹ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ ያሉት አቶ ቴዎድሮስ፣ ነፃ፣ ገለልተኛ እና ቀልጣፋ የዳኝነት አሠራርን ለማጎልበት ትኩረት እንደሚደረግም ነው የተናገሩት። ዘንድሮ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ ልዩ ችሎቶችን የማደራጀት ሥራ በልዩ ትኩረት እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

2016 ዓ.ም የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ በጠቅላይ ፍርድ ቤት 16 ሺህ 636 መዝገቦች ላይ፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት 24 ሺ 853 እንዲሁም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 135 ሺ 233 መዝገቦች እልባት እንደተሰጠባቸው አመልክተዋል።

በተያያዘ ዜናም፤ በክፊል ዝግ ሆነው የቆዩት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከትናንት ጥቅምት 01 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በይፋ ወደ መደበኛ አገልግሎታቸው ተመልሰዋል።

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ 1234/13 በተደነገገው መሠረት ከነሐሴ 01 እስከ መስከረም 30 ዝግ ሆነው ይቆያሉ።

# ከመጪው ጥር ወር ጀምሮ የኢ-ፓስፖርት አገልግሎት ሊሰጥ ነው

- የፓስፖርት የአገልግሎት ጊዜ ወደ አስር ዓመት ከፍ ይላል
- በሩብ ዓመቱ ከ367 ሺህ በላይ ፓስፖርት ተሰራጭቷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ከመጪው ጥር ወር ጀምሮ የኢ-ፓስፖርት አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምር የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አስታወቀ። የፓስፖርት አገልግሎት የጊዜ ገደብም ወደ አስር ዓመት ከፍ እንደሚደረግ ተገልጿል።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሠላማዊት ዳዊት ትላንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ ከመጪው ጥር ወር ጀምሮ የኢ-ፓስፖርት አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል።

አሁን ያለውን የፓስፖርት ቡክሌት ወደ ኢ-ፓስፖርት ለመቀየር ምርት መጀመሩን የገለጹት ወይዘሮ ሰላማዊት፣ በመጪው የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት የመጀመሪያ ወር ኢ-ፓስፖርት መስጠት ይጀመራል ብለዋል።

ኢ-ፓስፖርት ሁሉም የተቋሙን ሥርዓት በዘመናዊ መልኩ የሚቀይር መሆኑን ጠቅሰው፣ የተቋሙን አገልግሎት ቀልጣፋ ለማድረግ፣ የፓስፖርት ኅትመትን ለማቀላጠፍ የሚያስችል ማሻሻያ መሆኑን ገልጸዋል።

እድሜያቸው ከ25 ዓመት በላይ ለሆናቸው ዜጎች የፓስፖርት አገልግሎትን ጊዜ ከአምስት ዓመት ወደ አስር ዓመት ከፍ ሊደረግ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፣ ከዚህ በኋላ የሚታተሙ ፓስፖርቶች የአገልግሎት ጊዜ ገደብ አስር ዓመት ይሆናል ብለዋል።

በ2017 ዓ.ም ሩብ ዓመት ውስጥ 478 ሺህ ቡክሌት ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት መቻሉን ጠቅሰው፣ ከእነዚህ ውስጥ ከ367 ሺህ በላይ ፓስፖርቶች ታትመው ለደንበኞች የተሰራጩ ሲሆን በመደበኛ 344 ሺህ 288፣ በአስቸኳይ 22 ሺህ 403፣ ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት 152፣ ሰርቪስ ፓስፖርት 298 መሆናቸውን አስረድተዋል።

ተቋሙ በኦንላይን (በይነ መረብ) የመቀበል አቅሙን በቀን ከሰባት ሺህ በላይ ማሳደጉን በመግለጽ፣ ለአስቸኳይ ፓስፖርት በቀን 600 ተገልጋዮችን የማስተናገድ አቅም መፍጠር መቻሉንም ተናግረዋል።

በሩብ ዓመቱ በቦሌ አየር ኬላ ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ መንገደኞች አገልግሎት መሰጠቱን ጠቅሰው፣ በዚህም 559 ሺህ 848 መንገደኞች ወደሀገሪቱ መግባታቸውንና 581



ወይዘር ሠላማዊት ዳዊት

ሺህ 704 መንገደኞች ደግሞ ከሀገር መውጣታቸውን ገልጸዋል።

በየብስ ኬላ በኩል ለ237 ሺህ 872 መንገደኞችን አገልግሎት መስጠት ተችሏል ያሉት ዳይሬክተሯ፣ 106 ሺህ 003 ደንበኞች ወደሀገር የገቡ ሲሆን 131 ሺህ 869 ደንበኞች ከሀገር ወጥተዋል ብለዋል።

ተቋሙ በሦስት ወር ውስጥ 259 ሺህ 705 ቪዛዎችን መስጠት መቻሉን በመግለጽ፣ ይህም ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ እንግዶች ብዛት እየጨመረ መምጣቱን የሚያሳይ መሆኑን ገልጸዋል።

በሩብ ዓመቱ በሲቪል ምዝገባ 572 ሺህ 236 ኩነቶች መመዝገባቸውን ጠቅሰው፣ ከእነዚህ ውስጥ 572 ሺህ 114 ተገልጋዮች የምስክር ወረቀት እንዲወስዱ መደረጉንም ተናግረዋል።

በተቋሙ ላይ በተደጋጋሚ ሲነሱ የነበሩ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ የማሻሻያ ሥራዎች ሲሠሩ እንደነበር ጠቅሰው፣ የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቤቱ በተለይ ተቋማዊ ሪፎርም ማድረግ ከጀመረ በኋላ መጠነ ሰፊ ለውጦችን እያስመዘገበ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም በተለይ በተቋሙ ላይ የሚነሳውን የሙስና ሠንሠለትና የተገልጋዮች እንግልት በመቅረፍ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

# ኃያላን ሀገራት የተፈጥሮ ሀብቷን ለመጠቀም የሚያደርጉት ፍትጊያ ለአሕጉሪቱ ትልቅ ፈተና ሆኗል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ኃያላን ሀገራት የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠቀም የሚያደርጉት ፍትጊያ ለአሕጉሪቱ ትልቅ ፈተና መሆኑን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ሕግ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀነራል አምባሳደር ረታ ዓለሙ ገለጹ።

የአፍሪካ የተጋላጭነት ፈተናዎች እና በዓለም አቀፍ ውድድር ውስጥ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ የጥናት ጉባኤ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ይገኛል።

አምባሳደር ረታ ዓለሙ በጉባኤው ላይ ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፤ አፍሪካ ልዩ ልዩ ባሕሎች፣ ታሪኮችና በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤት ናት።

የዓለም ኃያላን ሀገራት የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠቀም የሚያደርጉት ፍትጊያ ትልቅ ፈተና ሆኗል። በዚህም በአሕጉሪቱ ከሚስተዋሉ በርካታ ችግሮች ጀርባ እነዚህ እጆች አሉ።

ስለሆነም የአፍሪካ ሀገራት ያለባቸውን ፈተና ለመቋቋም እና የዜጎቻቸውን ሕይወት ለመለወጥ ያላቸውን አቅም እና ሀብት በማስተባበር መሥራት እንደሚገባቸው አመልክተዋል።

አባል ሀገራቱና በንግድ እና ኢንቨስትመንት ያላቸውን ትስስር ማጠናከር እንዳለባቸው ጠቅሰው፤ የአፍሪካ ነፃ ንግድ ቀጣና በዚህ በኩል ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል። የአፍሪካ ኅብረትም በአሕጉሪቱ ጉዳዮች ላይ ያለውን የመሪነት ሚና ማጠናከር እንደሚገባው አስገንዝበዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዲፕሎማሲ መግቢያ በር ናት ያሉት አምባሳደር ረታ፤ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ቁልፍ ሚና እንደምትጫወትም ጠቁመዋል።

ውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጀፋር በድሩ በበኩላቸው፤ በዓለም ላይ ያለው የጂኦ-ፖለቲካ ፋክክር የፈጠራቸው ፈተናዎች የአፍሪካን የተጋላጭነት ፈተና እንዳባባሰው ገልጸዋል።

በዓለም ላይ ያሉ ጦርነቶች እና ግጭቶች በአፍሪካ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት፣ የወጪ ንግድ እና አጠቃላይ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ማሳደራቸውን ተናግረዋል።

ድህነት፣ ግጭቶች፣ የሕዝብ እድገት፣ ተፈጥሯዊ አደጋዎች፣ ጽንፈኝነት እና ሌሎች ፈተናዎች የአፍሪካን ተቋማዊ አቅም ደካማ ማድረጉን ጠቁመዋል።

የአፍሪካ ሀገራት በዓለም አቀፍ ደረጃ የኃይል ፋክክሩ የፈጠረውን ፈተና እና ውስጣዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት አበክረው መሥራትና ሚዛን ጠብቀው መሄድ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

አሕጉሪቱ ዓለም ባለው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እሽቅድድም ምክንያት እየፈተነች ነው። ይህም አሕጉሪቱ በሁሉም መስክ ወደፊት እንዳትራመድ እንቅፋት ፈጥሯል። ይህን ችግር ለመሻገር አፍሪካውያን አንድነታቸውንና ትብብራቸውን ማሳደግ አለባቸው ብለዋል።

የጥናት ጉባኤው የአፍሪካን የተጋላጭነት ፈተናዎች ላይ መፍትሔ ለማበጀት እና በዓለም አቀፍ ውድድር ውስጥ ካሉ ዕድሎች ተጠቃሚ ለመሆን በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ሳይንሳዊ ምክረ ሀሳቦች እንደሚቀርቡበት አመላክተዋል።

የአልጄዚራ የጥናት ማዕከል የጥናት ዘርፍ ኃላፊ ኢዘዲን አብደልሙላ (ዶ/ር)፤ የዓለም ኃያላን ሀገራት በአፍሪካ ውስጥ ፉክክር የሚያደርጉት አሕጉሪቱ ያላትን የተፈጥሮ እና የሰው ኃይል ሀብቶችን ለመጠቀም ነው ብለዋል።

ይህ ፍላጎት ከቅኝ አገዛዝ እና ከቅኝ ግዛት እሳቤዎች የተወረሰ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ ፈተና ዓለም አቀፋዊ ይዘት አለው።

ስለሆነም አፍሪካ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠቃሚነቷ ለማረጋገጥ መሥራት እንዳለባት አመላክተዋል።

ጉባኤው የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት እና የአልጄዚራ የጥናት ማዕከል በትብብር ያዘጋጁት ሲሆን፤ "አፍሪካ የተጋላጭነት ፈተናዎች፤ በዓለም አቀፍ ውድድር ካሉ ዕድሎች ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ" በሚል መሪ ሃሳብ ላይ ያተኮረ ነው።



# የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት 12 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሦስት ወራት በቅርቡ የተደረገውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተከትሎ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በካፒታል ደረጃ 12 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከፍተኛ አመራሮች በዱከም የሚገኘውን የኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ የሥራ እንቅስቃሴ ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።

በዚሁ ወቅት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ዘለቀ ተመስገን (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ ለውጡን ተከትሎ ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢን ለመፍጠር በተሠሩ የሕግ፣ የኢኮኖሚና ሌሎችም በርካታ ማሻሻያዎች በየጊዜው ወደኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ የሚመጡ ባለሀብቶች ቁጥር ጨምሯል። በዚህም ኢትዮጵያ ከምሥራቅ አፍሪካ ግንባር ቀደም የኢንቨስትመንት መዳረሻ ሆናለች።

የኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ ተኪ ምርቶችን እያመረተ ለሀገር ውስጥ ገበያ እያቀረበ ሲሆን በውስጡ 153 ድርጅቶች አሉት ከእነኝህ መካከል 95 በመቶ የሚሆነው በቻይና ባለሀብቶች የተያዘ መሆኑን የገለፁት ዘለቀ (ዶ/ር)፤ የኢንዱስትሪ ፓርኩ ካሉት የግል ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተጠቃሽ ነው ብለዋል።

እንደ ዘለቀ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ከ3ሺህ 300 በላይ የቻይና ፕሮጀክቶች በኢትዮጵያ ተግባራዊ እየተደረጉ ሲሆን ይህም ከየትኛውም ሀገር ተቀዳሚ ቁጥር ነው። በዚህም ከ325ሺህ በላይ ለሆኑ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል።

እንዲሁም የክህሎት፣ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እየተደረገ መሆኑን በመግለፅ፤ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከውጭ ለሚመጡ ባለሀብቶች ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢን የመፍጠር ሥራን እየሠራ መሆኑን ዘለቀ (ዶ/ር) ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ዳጋቶ ኩንቤ በበኩላቸው፤ ኮሚሽኑ የውጭ ኢንቨስተሮች ወደኢትዮጵያ በመምጣት መዋዕለንዋያቸውን እንዲያፈሱ፣ በቂ የውጭ ምንዛሪ እንዲገኝ፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርና የእውቀት ሽግግር እንዲኖር ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል ነው ያሉት።

በቅርቡ የተደረገውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያን ተከትሎ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ቁጥር ጨምሯል በዚህም ቁጥሩ ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 12 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም ዝግ የነበሩ የወጪ፣ የገቢ፣ የችርቻሮና የጅምላ የንግድ የሥራ ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረጋቸውን ተከትሎ ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ብቻ 72 ጥያቄዎች መምጣታቸውን ያነሱት አቶ ዳጋቶ፤ በዚህም 41 በገቢ፣ 31 በወጭ ንግድ ዘርፍ ለመሳተፍ የቀረቡ ጥያቄዎች ሲሆኑ ከእነኝህ ውስጥ 12ቱ ይሁንታ ማግኘታቸውን ጠቁመዋል።

ኮሚሽኑ በባለሀብቶች ዘንድ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታትና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴውን ለመደገፍ በተጨባጭ መሬት ላይ ወርዶ እየሠራ መሆኑን አቶ ዳጋቶ ገልጸዋል።

## "የአዲስ አበባ የምገባ ማዕከላት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተማሪዎችን በትምህርታቸው ውጤታማ ማድረግ የሚቻለው ምገባን ጨምሮ ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን በማሟላት እንደሆነ በመጥቀስ፤ አዲስ አበባ በተለይ በትምህርት ቤት ምገባ የወሰደቻቸው እርምጃ የሚደነቅና ለሌችም ትምህርት የሚሰጥ ነው ሲል ተናግሯል።

ሴኔጋልን በመወከል በጉብኝቱ የተሳተፈው ጆሴፍ ሳምቡ በበኩሉ በተለያየ የምገባ ማዕከላት በመዘዋወር የተመለከታቸው ተግባራት ከተማዋ ምን ያህል ለማኀበረሰቡ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች እንደሆነ ማስተማሪያ ነው ብሏል። በትምህርት ቤት ውስጥ ያለው የተማሪዎች ምገባ በመማር ማስተማሩ ላይ ትልቅ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያለው በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ሲል መክሯል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ምነወር ኑረዲን እንደገለጹት፣ ትምህርት ቤቶችን ሳይጨምር የምገባ ማዕከላት እየሰጡ ባሉት አገልግሎት ከ36 ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጐች ተጠቃሚ ሆነዋል።

በትምህርት ቤት ምገባ ከ801ሺህ በላይ ተማሪዎች ተጠቃሚ ሲሆኑ፣ አጠቃላይ የግብዓት አቅርቦቱና የትምህርት ቤት ምገባው በጀት ከዘጠኝ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን ገልጸዋል። በዚህም ለ16ሺህ እናቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል ብለዋል።

በዚህ ሥራ አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ዕውቅናዎችን ማግኘቷን የተናገሩት ኃላፊው፤ የምገባ ማዕከላቱ የበርካታ ዜጐችን ሕይወት ከመደጎም አልፎ ለተለያዩ ሀገራት ተሞክሮን የሰጠ መሆኑን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

እኤአ በ2015 የተቋቋመውና 233 ከተሞችን በአባልነት ያቀፈው የሚላን የከተማ ምግብ ፖሊሲ ስምምነት በከተሞች ውስጥ ዘላቂ የምግብ ሥርዓት አተገባበርን ለማስተዋወቅ አልሞ እየሠራ ያለ ነው። ኢትዮጵያም የዚሁ አካል አባል በመሆን በምገባ ሥርዓት ዕውቅናን አትርፋለች።

የፖሊሲ ስምምነት አባል የሆኑና ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ የከተማ ተወካዮች፤ እንዲሁም ከጣሊያኗ ሚላን ከተማ ፖሊሲውን የሚመሩ አካላት የአዲስ አበባን ተሞክሮ ለማየት ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ የተለያዩ የምገባ ማዕከላትን በትላንትናው ዕለት የጎበኙ ሲሆን፤ በማዕከላቱ የተመለከቱት ሥራ ለወከሏቸው ሀገራት ትምህርት የሰጠ መሆኑን ገልጸዋል።

## ታማኞቹ የልማት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አቶ መልካም አሰፋ የማራቶን ሞተር ኢንጅነሪንግ መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናቸው። ድርጅታቸው የ2016 በጀት ዓመት ጨምሮ በተከታታይ አምስት ዓመታት በታማኝነት ግብር በመክፈል የወርቅ ሜዳሊያ ሽልማት አግኝቷል።

"ግብር መክፈል ግዴታ ነው። ይህን ግዴታችንን በታማኝነት ግብር በመክፈል ለሀገራችን ዕድገት የበኩላችንን እየተወጣን እንገኛለን" የሚሉት አቶ መልካም፤ ባለፉት አምስት ዓመታት ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ግብር መክፈላቸውን አውስተዋል። ሽልማቱ ትልቅ ክብር እንዳገኘን ተሰምቶናል። ይህን ክብር ለማስጠበቅ አሁንም ብዙ ሥራ መሥራት ይኖርብናል። ወደፊትም በሀገር ልማት ላይ የምናበረክተውን አስተዋፅዖ ለማላቅ ተግተን እንሠራለን ብለዋል።

የሚያገኙትን ትርፍ የሚያውሉት የማስፋፊያ ሥራዎችን በማከናወን መሆኑን አመልክተው፤ ኩባንያቸው በአሁኑ ጊዜም 14 አይነት የሚሆኑ ሞዴል መኪናዎችን ይገጣጥማል። ይህም ከግብር ጎን ለጎን የቴክኖሎጂ ሽግግር በመፍጠር፣ በሥራ ዕድል ፈጠራና የውጭ ምንዛሪን በማዳን ረገድ ሀገራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ እንደሚገኙ ነው የነገሩን።

ግብርን በታማኝነት በመክፈልም ሆነ ጥራትና ብዛት ያላቸውን የመኪና ምርቶች በማምረት ለሀገራችን ልማት ትልቅ አስተዋፅዖ ለማበርከት እንሠራለን የሚሉት አቶ መልካም፤ ሁሉም ነጋዴ በወቅቱና በታማኝነት ግብር በመክፈል ለሀገሩ ልማት የበኩሉን ድርሻ ማበርከት እንደሚጠበቅበት ገልጸዋል።

በ2016 በጀት ዓመት አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ግብር ከፍለናል። ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት በታማኝነት ከፍተኛ ግብር በመክፈላችን የፕላቲኒየም ተሸላሚ ስለሆንን ልዩ ተሸላሚ ሆነናል የሚሉት የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክን በመወከል ሽልማቱን ያገኙት አቶ ፍሌራ ድንቁ፤ አንድ ድርጅት በሀገሩ ሠርቶ ትርፍ ካተረፈ ለመንግሥት ግብር መክፈል ግዴታ አለበት ነው ያሉት።

ለሀገር ልማት ግብር በመክፈል የበኩሉን ድርሻ መወጣት ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ መሆኑን አመልክተው፤ ምክንያቱም ከግብር የተሰበሰበው ገንዘብ ለሀገር ልማትና ደኅንነትን ለማስጠበቅ የሚውል ነው። ከዚህ አኳያ የእኛን አርዓያነት ተከትሎ ሁሉም ግብር ከፋይ በታማኝነት ግብሩን መክፈል ይኖርበታል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በ2015 በጀት ዓመት በተካሄደው የአምስተኛው ዙር የታማኝ ግብር ከፋዮች የምስጋናና የዕውቅና መርሐ ግብር ላይ 500 ታማኝ ግብር ከፋዮች ምሥጋና እና ዕውቅና እንደተሰጣቸው ይታወሳል። በ2016 በጀት ዓመት በ6ኛ ዙር የታማኝ ግብር ከፋዮች የምስጋናና ዕውቅና መርሐ ግብር ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት 550 ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ዕውቅናና ምስጋና ተበርክቶላቸዋል።

## ኢትዮጵያ በያዝነው ወር አሕጉርና ዓለም አቀፍ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዝግጅት እያደረገች መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ። ከአንድ ሺህ 500 በላይ ዓለም አቀፍ እንግዶች የሚሳተፉበት ኮንፈረንስ እንደሚካሄድ ተመላክቷል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሠላማዊት ካሣ ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ በቱሪዝም ዘርፉ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን አስመልክተው ትናንት ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ ሰጥተዋል።

በተያዘው የጥቅምት ወር ለኮንፈረንስ ቱሪዝም አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ አሕጉርና ዓለም አቀፍ ሁነቶች እንደሚጠበቁ ገልጸው፤ "ከረሀብ ነፃ የሆነ ዓለም መፍጠር" በሚል መሪ ሀሳብ ከጥቅምት 26 እስከ 28 ቀን 2017 ዓ.ም የሚካሔደው ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ አንዱ ነው ብለዋል።

ዓለም አቀፍ ፈተና የሆነውን ረሀብ በተደራጀ መልኩ መፍትሔ ለመስጠት የዓለም ሀገራት መንግሥታት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የዓለም አቀፍ ተቋማትና ድርጅቶች በጋራ የሚመክሩበት እና ልምድ የሚለዋወጡበት መሆኑን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ዓመታት በበጋ መስኖ፣ በአረንጓዴ ዐሻራ፣ በኩታ ገጠም እርሻ፣ የአየር ንብረት ለውጥን በመዋጋትና በሌሎች ንቅናቄዎች በምግብ ራሷን ለመቻል የሠራቻቸውን ሥራዎች በተመለከተ ተሞክሮ ታካፍላለች ሲሉ አብራርተዋል።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም፣ በዓለም የምግብ ፕሮግራም እና ረሀብን ለመዋጋት የተደረገ ዓለም አቀፍ ጥናት ይፋ እንደሚደረግ አመላክተዋል።

በኮንፈረንሱ ከአንድ ሺህ 500 በላይ ዓለም አቀፍ እንግዶች፣ የሁሉም የአፍሪካ ሀገራት ተወካዮች እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ30 በላይ የሚሆኑ ተቋማት ተወካዮች ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

የአፍሪካ የእግር ኳስ ኮንፌደሬሽን ኮንፈረንስም ከጥቅምት 9 ቀን እስከ ጥቅምት 12 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ የሚካሄድ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ያሏትን እቅዶች፣ ከስፖርት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የመሠረተ ልማት ግንባታዎች፣ እና ሌሎች ሥራዎችን ለማስተዋወቅ ዕድል ይፈጥራል ሲሉ ተናግረዋል።

ሦስተኛውን የአፍሪካ የመከላከያ ሚኒስትሮች ኮንፈረንስንም ከጥቅምት 5 ቀን ጀምሮ እስከ 7 ቀን 2017 ዓ.ም በአዲስ አበባ ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

ኮንፈረንሱም ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሠላምና መረጋጋት ያላትን ሚና የምታሳይበት እና ሀገራት ልምድ የሚለዋወጡበት እንደሚሆን አስታውቀዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፣ ኮንፈረንሱን ለመሳተፍ የሚመጡ እንግዶች በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳዮች ከሚያደርጓቸው ምክክሮች ጎን ለጎን እንደሀገር የሠራናቸውን በርካታ የልማት ሥራዎች የሚጎበኙ ይሆናል። ይህም የሀገሪቱን የቱሪዝም ኮንፈረንስም ተጠቃሚነት የሚያሳድግ ነው።

ኮንፈረንሶችን ለማካሄድ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቂ ዝግጅት መደረጉንና እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ በኮንፈረንሱም አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ ማዕከል መሆኗን ከማሳየት ባለፈም እ.ኤ.አ በ2023 ብቻ በዓለም አቀፍ ደረጃ አንድ ነጥብ ስምንት ትሪሊዮን ዶላር ከተንቀሳቀሰበት የኮንፈረንስ ቱሪዝም ተጠቃሚ እንድትሆን ዕድል የሚፈጥርላት መሆኑን አስታውቀዋል።

በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የለሙትን በርካታ የቱሪስት መዳረሻዎች ለማስገብኘትም ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ጨምረው ገልጸዋል።

መስከረምና ጥቅምት ወር ከፍተኛ የሆነ የቱሪስት ፍሰት የሚኖርበት እና በርካታ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ የአደባባይ በዓላት የሚከበሩበት ወር መሆኑን ገልጸዋል።

ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ የአደባባይ በዓላት ለቱሪዝም ዕድገት፣ ለሀገሪቱ የገጽታ ግንባታ፣ የማኅበረሰቡን መስተጋብር እና የእርስ በእርስ ግንኙነት ለማጠናከር፣ የኢትዮጵያን ባሕል ለሌሎች የዓለም ሀገራት ለማስተዋወቅና ሌሎች በርካታ ጠቀሜታዎችን አስገኝቷል ብለዋል።

ቱሪዝም ለሀገሪቱ የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ ለማወቅ፣ ውሳኔ ለመስጠት፣ በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ፓሊሲ ቀረጻና ስልታዊ እቅድን እውን ለማድረግ እና ሌሎች ጠቀሜታዎችን የሚያስገኝ የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ወደ ተግባር መግባቱን አስታውሰዋል።

# የናይል የትብብር ማዕቀፍ- ለፍትሃዊ ተጠቃሚነት

**እስማኤል አረቦ**

ኢትዮጵያ የጥቁር ዓባይ መነሻ ስትሆን 86 በመቶ የሚደርሰው የናይል ወንዝ ውሃ ታመነጫለች። ይህ የውሃ ድርሻዋም እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ ባለሙሉ መብትና ባለብዙ ተጽዕኖ አሳራፊ ሀገር እንድትሆን አድርጓት ቆይቷል።

ሆኖም ከቅኝ ግዛት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ያላትን መብትና ተጽዕኖ ፈጣሪነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጣች መጣች። በተቃራኒው ደግሞ ቀደም ሲል ለኢትዮጵያ ሲገብሩና ሲማለዱ የነበሩት ግብጾችና ሱዳኖች የቅኝ ገዢዎችን፤ በተለይም የእንግሊዝን ተጽዕኖ ፈጣሪነት በመጠቀም የበላይነቱን ለመያዝ ጥረዋል። የተዛባ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መብቶችን በመጥቀስ የመከራከሪያ አጀንዳ አድርገው ማቅረብ ሞክረዋል።

በታሪካዊ እና ተፈጥሮአዊ መብቶች ላይ ተመስርተው በታችኛው ተፋሰስ አገራት ከሚቀርቡ የመብት ክርክሮች መለስ ዓባይን አስመልክቶ እስካሁን ያለው የመከራከሪያ ነጥብ ከቅኝ ግዛት ጋር የተያያዙ ውሎች ናቸው። የመጀመሪያው በቅኝ ግዛት ዘመን እ.ኤ.አ ግንቦት 7 ቀን 1929 በታላቋ ብሪታኒያና በግብፅ መካከል የተደረገው ስምምነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ከሰላሳ ዓመት ቆይታ በኋላ ማለትም ከነጻነት ወዲህ እ.ኤ.አ ሕዳር 8 ቀን 1959 በሱዳንና ግብፅ መካከል የተፈረሙ ስምምነቶች ለአብነት ይጠቀሳሉ።

እነዚህ ሁለት ስምምነቶች በሚፈረሙበት ወቅት እንግሊዝ ከላይኛው ተፋሰስ አገራት ሱዳንን፣ ታንዛኒያን፣ ኡጋንዳን፣ እና ኬንያን በመወከል ግዴታ ከመግባቷ ውጪ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎቹ የተፋሰሱ ሀገራት ተካፋይ አልነበሩም። በተለይም ኢትዮጵያ በወቅቱ ነፃ ሀገር ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በስምምነቱ ተሳታፊ መሆን ቢገባትም በሂደቱ በጋራ መብቷን እንድትወስን ምንም አይነት ጥያቄ ሳይቀርብላት ቀርቷል።

በ1929 እና 1959 በተደረጉት ስምምነቶች መሰረት ግብፅ በዓባይ ላይ የባለቤትነት መብት ስትጎናፀፍና በተጠቃሚነት ረገድም ከ55 ቢሊዮን ኪዩቢክ በላይ ውሃ ድርሻ እንዲኖራት፤ ሱዳንም 18 ቢሊዮን ኪዩቢክ የውሃ መጠን ድርሻ እንዲኖራት ተደርጓል። ከ86 በመቶ በላይ የሚሆነው የናይል ውሃ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ግን ቅንጣት ታክል የውሃ ድርሻ እንዲኖራት ሳይደረግ የበይ ተመልካች ሆና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ቆይታለች።

እነዚህ ሁለቱ ስምምነቶች እስከዛሬም ድረስ በሕዳሴ ግድብ ላይ በሚደረጉ ውይይቶች እንደማጣቀሻ እየቀረቡ ግብጾች በማደናገሪያነት እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ። አድሏዊና አፍትሃዊ የሆኑት የ1929ኙም ሆነ የ1959ኙ ስምምነቶች ከ86 በመቶ በላይ የናይል ውሃ ምንጭ የሆነችውን ኢትዮጵያን ያገለሉ መሆናቸው እየታወቀ ግብጽ ዛሬም ድረስ ሙጥኝ ብላ ትገኛለች።

ግትር የሆነው የግብጽ አቋም ከፍተኛ ቁጭት እና ሀገራዊ የመልማት ፍላጎት እልህ ሲፈጥር ቆይቷል። ይህ ሀገራዊ ቁጭትና እልህም ጊዜው ፈቅዶ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም የሕዳሴ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ጉባ ላይ ተጥሏል። የኢትዮጵያውያንም የዘመናት ቁጭት መልስ ያገኘበት ታሪክ ተመዝግቧል። የኢትዮጵያም ተነሳሽነት በሌሎቹ ተፋሰሱ ሀገራት ዘንድ ከፍተኛ የመልማት ፍላጎት ተስፋ ፈንጥቋል።

በተፋሰሱ ዙርያ ያሉ ሕዝቦች ቁጥር እየጨመረ በመሄዱና ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጥቅም ላይ የማዋል ፍላጎታቸው እያደገ በመሄዱ ኢትዮጵያ ባሻገር የሌሎችም ፍላጎት መሆን ጀምሯል። በወንዙ የላይኛው ክፍል የሚገኙ ሀገራት ስለዓባይ ውሃ አጠቃቀም ከዚህ በፊት የተፈረሙትን የቅኝ ግዛት ስምምነቶች በመንቀፍ እንደማይቀበሉት በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በተደጋጋሚ አሳውቀዋል።

**እግረ መንገዷንም የሕዳሴ ግድብ ግንባታን ወደ ፍጻሜው በማድረስ መጪውን ብሩህ ጊዜ እየተጠባበቀ ች ነው**

ከ1999 እ.ኤ.አ ጀምሮም የናይል ተፋሰስ ትብብር (Nile Basin Initiative) የተሰኘ ጊዜያዊ የትብብር ማእቀፍ በማቋቋም አንድ ልዩ የናይል ቤዚን ኮሚሽን ለመመስረት ፍላጎት አሳዩ። በዓለም አቀፍ ሕግ ይዘት የተቃኘ ተፋሰስ- አቀፍ ውል ለማዘጋጀት በናይል የሚኒስትሮች ጥምረት (counselee) በኩል ድርድር ሲያደርጉ ቆይተዋል።

እ.ኤ.አ ግብፅና ሱዳን የፈረሙት የ1959 ስምምነት የዓባይን ውኃ ሀብት ከአሥር የተፋሰሱ ተጋሪ ሀገሮች ለሁለቱ ብቻ የሚያከፋፍል በመሆኑ ጊዜያዊ መፍትሔ እንጂ ዘላቂ ስምምነት ሆኖ ሌሎቹን ተጋሪ አገሮች ለማስገደድ እንደማይችል የዘርፉ ምሁራን ሲወተውቱ ቆይተዋል። ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ ጨምሮ በሁሉም ዘንድ የሚነሳ ገዥ ሀሳብ ነው።

ኢትዮጵያም ይህንኑ መነሻ በማድረግ ከግብጽ እና ሱዳን ጋር ተከታታይነት ያላቸውን ድርድሮች በማድረግና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ አካሄድን በመከተል ዛሬ ላይ አሁን ከምትገኝበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። እግረ መንገዷንም የሕዳሴ ግድብ ግንባታን ወደ ፍጻሜው በማድረስ መጪውን ብሩህ ጊዜ እየተጠባበቀች ነው። ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ሀገራትም በጋራ መብታቸውን የማስከበር እንቅስቃሴ ውስጥ በመግባት የናይል የትብብር ማዕቀፍ ዕውን የሚሆንበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርገዋል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በዓለም ላይ ወደ 276 የሚጠጉ ድምበር ተሻጋሪ ወንዞች አሉ። እነዚህን ወንዞች 145 የሚሆኑ ሀገራት ይጋራሉ። አንዳንድ ሀገራት ወንዞቹን የሚመለከት ሕግ አላቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የጋራ የውሃ አጠቃቀም ሕግ የላቸውም። ነገር ግን ሕጉ ያላቸው ሀገራት ውሃን ዘላቂና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚነታቸውን እያረጋገጡ ይገኛሉ። አንዱ ሕጋዊ ማዕቀፍ ሆኖ በቀጣይ የናይልን የውሃ አጠቃቀም ፍትሃዊነትን የሚያረጋግጠው የናይል የትብብር ማዕቀፍ ነው።

የናይል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት የዓባይን ውሃ በጋራ፣ በእኩልነትና ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ውሃውን መጠቀምና አብሮ መንከባከብ የሚያካትትና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች የሚተዳደሩባቸውን መርሆችን ጭምር ያካተተ ማዕቀፍ ነው። ይህም በአሥራ አንድ ሀገራት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው።

ጉዳዩን የኢትዮጵያ መንግስት የቅርብ ክትትል ያደረገበት በመሆኑ የተሳካ እየሆነ መጥቷል። በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተለያዩ ሀገራት መሪዎችን በሚያገኙበት አጋጣሚ የውሃ ሀብትን በጋራ ማልማትና መጠቀም የሚቻልባቸውን መንገዶች ያነሳሉ። ይህም የኢትዮጵያ የውሃ ዲፕሎማሲ ሥራ ማሳያ ነው።

ኢትዮጵያ ቀድማ ማዕቀፉን ያጸደቀች ሲሆን ከዛ በኋላ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋዳንዳ ገብተውበት በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል። ይህ የመጣውም በጋራ ለመልማት ካለ ፍላጎት የመነጨ ነው። በቅርቡ ደግሞ ብሩንዲና ደቡብ ሱዳን በምክር ቤቶቻቸው አጽድቀውታል።

ይህ መሆኑ ደግሞ ለዘመናት እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የላይኛው ተፋስስ ሀገሮች ከውሃው በፍትሃዊነት የመጠቀም መብታቸውን ከማረጋገጡም በሻገር ኢትዮጵያ ከሱዳንና ከግብጽ ጋር ስታደርገው የነበረውን የፍትሃዊነት ጥያቄና በጋራ የመልማት ሀሳብ ሌሎች ሀገራት እንዲቀላቀሉና ክርክሮችንም የሚያካሂዱት ሀገራት ሳይሆኑ ኮሚሽኑ እንዲሆን ያስችላል።

ይህ ማለት ጉዳዩ የኢትዮጵያ እና የግብጽ ብቻ ሳይሆን የ11ዱም ሀገራት ጉዳይ እንዲሆን አድርጎታል። ጠቅለል ሲደረግ የናይል ትብብር ማዕቀፍ ወደ ኮሚሽን ማደጉ የሚከተሉትን ጥቅሞች ይዞ ይመጣል። የመጀመሪያው እና ዋናው ነገር የናይልን ውሃ በትብብር ለመጠቀምና ለማልማት ያስችላል። በቅኝ ግዛት ውሎች ውሃውን ከመጠቀም ተገለው ነበሩ የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት ውሃውን በፍትሃዊነት የመጠቀም መብት ይጎናጸፋል።

ኢትዮጵያ ይህንኑ ሀሳብ መነሻ በማድረግ ከግብጽ እና ሱዳን ጋር ተከታታይነት ያላቸውን ድርድሮች በማድረግና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ ሀሳብን እያራመደች ዛሬ ላይ ደርሳለች። እግረ መንገዷንም የሕዳሴ ግድብ ግንባታን ወደ ማገባደዱ በማድረስ መጪውን ብሩህ ተስፋ በመጠባበቅ ላይ ትገኛለች። በተለይም የናይል የትብብር ማዕቀፍ ወደ ኮሚሽን ደረጃ መሸጋገሩ የኢትዮጵያ ጉዳይ ብቻ መስሎ የቆየው ውዝግብ ሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት በእኔነት ስሜት እንዲሚገቱበት እና እንዲከራከሩበት እድል የሰጠ ሆኗል።

በተፋሰሱ ሀገራት ዘንድ የሚታየውን አለመግባባት እና ውዝግብ የሚያረግብ ይሆናል። የአባይ ግድብ ጉዳይ ከሶስቱ ሀገራት እና አህጉር አልፎ ዓለም አቀፍ መወያያ አጀንዳ እስከመሆን ደርሷል። ለመጀመሪያ ጊዜም በጸጥታው ምክር ቤት የታየ አነጋጋሪ አጀንዳ ለመሆን በቅቷል።

ይህ ጉዳይ ከባህሪው በላይ ተለጥጦ ዓለም አቀፋዊ የጸጥታ ችግር ጭምር ተደርጎ ከመወሰዱም በላይ የአንዳንድ ሀገራት መሪዎች ጭምር በቦንብ እንዲመታ ምክር እስከመስጠት ደርሰዋል። ይህ ውዝግቡ የደረሰበትን ጡዘት የሚያሳይ ነው። የተፋሰሱ ሀገራት አሁን በደረሱበት ደረጃ ችግራቸውን ሁሉ በኮሚሽኑ በኩል የሚፈቱ በመሆኑ ወደ ሰላምና ትብብር የሚመጡበት አጋጣሚን ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል።

ከዚህም በዘለለ የሚቋቋመው ኮሚሽን የናይልን ውሃ ከብክነት በጸዳ መልኩ በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ስትራቴጂ ያወጣል ተብሎ ይጠበቃል። የናይል ወንዝ የአፍሪካን 1/10 የቦታ ስፋት የሚሸፍን ነው። አስራ አንዱ ሀገራትም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተፋሰሱ ሀገራት ተብለው ይጠራሉ።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ በናይል የትብብር ማዕቀፍ ውስጥ እስከ 300 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን የዚህ ወንዝ ልማት በቀጥታ ከነዋሪዎች ሕይወት መሻሻል ጋር የሚያያዝ ነው።

የናይል የትብብር ማዕቀፍ እዚህ ደረጃ እስኪደርስ ኢትዮጵያ በፍትሃዊነት መርህ የዓባይን ውሃ መጠቀም ብቻ ሳይሆን የማልማትም ሥራ እያከናወነች ነው። ከዚህም ባሻገር የወንዙን ጤናማ የፍሰት ሂደት ለመጠበቅና ዘላቂ በሆነ መልኩ ለሁሉም ሀገራት በቂ ውሃ እንዲኖር በማሰብ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በቢሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞችን በመትከል ላይ ትገኛለች።

የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ለውሃ መጠን መጨመር ጉልህ ሚና አለው። ችግኞች በተተከሉ ቁጥር አካባቢ ላይ የሚደርሰውን የመሬት መራቆት ይቀንሳል። የደን ሽፋንን ያሻሽላል። የግድቦችንም እድሜ ያራዝማል። የተፋሰሱ ሀገራትም በቂ ውሃ በዘላቂነት ማግኘት እንዲችሉ ይረዳል።

ባለፉት አምሥት ዓመታት ኢትዮጵያ በአረንጓዴ አሻራ በተከለቻቸው ከ40 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ውስጥ ወደ ስምንት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን የሚሆነው የተተከለው በዓባይ ተፋሰስ ነው። የዓባይን ውሃ በማልማት የሚመጣው ጠቀሜታ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለታችኛው ተፋሰስ ሀገሮችም ጭምር ጠቀሜታው የጎላ ነው። ይህ የኢትዮጵያ እንቅስቃሴ የናይልን ውሃ በፍትሃዊነት የመጠቀም ፍላጎቷ አንዱ ማሳያ ነው።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# "ግብጽና ሶማሊያን በተመለከተ አካሔዳችን የተጠና መሆን አለበት"

**ተሻለ ሰብሮ (ዶ/ር)**
**የቀድሞ ዲፕሎማትና ፖለቲከኛ**



ፎቶ በረከት ታደሰ

አስቴር ኤልያስ

**በሆሳዕና ከተማ ዙሪያ የምትገኘው ለምቡዳ ዱምበንች ቀበሌ የትውልድ ስፍራቸው ናት። ትምህርት ቤት ገብተው መማር የጀመሩት እንደሌሎቹ አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን አጸደ ሕጻናት ወይም አንደኛ ክፍል በመግባት አይደለም። ከአንድ እስከ ሶስተኛ ክፍል ያለውን ትምህርት አባታቸው በቤት ውስጥ ጥሩ አድርገው ስላስተማሯቸው ቀጥታ የገቡት አራተኛ ክፍል ነው። እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን የተማሩት በዚያው በሆዕሳና ከተማ "ራስ አባተ" በሚባል ትምህርት ቤት ሲሆን፣ የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍልን ደግሞ የተማሩት ጩንቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ከ11ኛ ክፍል ጀምሮ ያለውን ትምህርታቸውን ደግሞ በባህር ዳር ከተማ በሚገኘው በፖሊ-ቴክኒክ የቀጠሉ ሲሆን፣ ለአራት ዓመትም ተከታትለው በአድቫንስ ዲፕሎማ ለመመረቅ በቅተዋል - የዛሬው የዘመን እንግዳችን ተሻለ ሰብሮ (ዶ/ር)።**

እንግዳችን፣ ባገኙት ዲፕሎማ ተቀጥረው ጥቂት ከሰሩ በኋላ እድል አግኝተው በዘመኑ አጠራሩ ወደ ሶቬየት ኅብረት አቅንተዋል። በዚያም በአዘርባጃን ስቴት በባኩ ከተማ በራሻይኛ ቋንቋ በኪቭ ዩኒቨርሲቲ ለስድስት ዓመታት ያህል በዓለም አቀፍ ሕግ ተምረው በከፍተኛ ውጤት በሁለተኛ ዲግሪ ተመርቀዋል። በወቅቱም የኢትዮጵያ ተማሪያዎች ማኅበር መስራችና ለተከታታይ አምስት ዓመት ያህል መሪም ሆነው ሰርተዋል።

በወቅቱ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በከፍተኛ ውጤት ማጠናቀቃቸውን ተከትሎ የእርሳቸውና አንደኛ የወጡት ተማሪዎች ፎቶግራፍ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ በሚገኙ አዳራሾች ጭምር ይሰቀል ነበር። የሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዳጠናቀቁም በዚያው የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት የጀመሩ ሲሆን፣ የመማር እድል የተሰጣቸውም ካመጡት ከፍተኛ ነጥብ በመነሳት ነበር።

ይሁንና የዛሬው የዘመን እንግዳችን ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ጀምረው ገና ሶስት ያህል ወራት እንዳስቆጠሩ በደርግ ዘመን በነበረው በ"እናት አገር ጥሪ" መሰረት አገር ትበልጣለች ብለው የጀመሩትን ትምህርት ለጊዜው ቆም አድርገው ወደ እናት አገራቸው ኢትዮጵያ በመምጣት በቀጥታ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተቀጠሩ። በዚያም ዲፕሎማት በመሆን አገለገሉ።

የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪያቸውን በወቅቱ በጅምር ይተውት እንጂ ቁጭት ስለነበረባቸው ከበርካታ ዓመታት በኋላ በማኔጅመንት እና ሊደርሺፕ (Management and leadership) በኢትዮጵያና በአሜሪካ አገር ቨርጂንያ ተመላልሰው ተምረው ከሁለት ዓመት በፊት መመረቅ ችለዋል። የዛሬው የዘመን እንግዳችን የቀድሞው የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ (ኢራፓ) መስራችና ፕሬዚዳንት ሆነው ፓርቲውን የመሩ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ግን ፓርቲያቸው ኢራፓ ወደ ኢዜማ መቀላቀሉን አውግተውናል። ከእኚህ አንጋፋ ፖለቲከኛና የቀድሞ ዲፕሎማት ጋር ያደረግነውን ቆይታ አጠናቅረን አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ከሚዲያው አካባቢ ርቀዋል፤ በፓርቲ ውስጥ የነበረዎ እንቅስቃሴም ደብዝዟል፤ ምክንያቱ ይሆን? ከሶስተኛ ዲግሪ ምረቃ በኋላ ምን እየሰሩ ነው?**

**ተሻለ (ዶ/ር)፡-** ሁለትና ሶስት ያህል ዓመት የፒ.ኤች.ዲ ትምህርቴን ለመከታተል ስል ጠፋ ብዬ ነበር። ይሁንና ስለአገር ጉዳይ በተፈለኩበት ጊዜ ሁሉ በ"ያገባኛል" መንፈስ ሐሳቤን ከመስጠት ተቆጥቤ አላውቅም። የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ መስራችና ፕሬዚዳንት ሆኜ ለ11 ዓመታት ያህል ሰርቻለሁ። ከዚያ በኋላ ወደ ኢዜማ መቀላቀል ነበረብን።

እርግጥ ነው፤ በወቅቱ ብልጽግናም መግባት ምርጫችን ነበር። ምክንያቱም በወቅቱ ከሁሉም ኃላፊዎች ጋር እንነጋገር ነበር። ብልጽግና ለጊዜው ፕሪንሲፕሉ ቢኖርም ገና ጉዳዩ እምብዛም ጎልቶ አልወጣም ነበር። በወቅቱ የመደመርን ፍልስፍና ሙሉ ለሙሉ እያካሔደ ይሁን እንጂ ቴክኒካል ስራዎች ላይ አልተዘጋጀም ነበር። ስለዚህም በወቅቱ ቶሎ ተዘጋጅቶ የተሻማን ኢዜማ ነበር።

በኢዜማ ውስጥ እንቀሳቀል እንጂ እኔ በወቅቱ በአመራርነት ልቀጥል አልፈለግኩም። ምክንያቱም በግልጽ አሳውቄ ወደ ትምህርት ቤት በመግባቴ ነው። እየተማርኩ እያለ ምንም እንኳ የወትሮውን ያህል በተደጋጋሚ ባልገኝም አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በሚዲያ እንደ አንድ የሕግ ምሁርም ሆነ ዲፕሎማት ስሳተፍ ቆይቻለሁ። በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይም በተጠራሁበት መድረክ ላይ ሁሉ አለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ ያልዎ ተሳትፎ ከፍ ያለ ነው፤ እንደሚታወቀውም ግድቡ ሲጠናቀቅ የወራት ያህል ጊዜ ቀርቶታልና እዚህ በመድረሱ ምን ተሰማዎ?**

**ተሻለ (ዶ/ር)፡-** ከግድቡ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ድርድሮች ሲካሔዱ ቆይተዋል። ብዙዎች ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚሞክሩ ነበሩና እሱ ሁሉ ተግዳሮት አልፎ ዛሬ ላይ መድረስ በመቻሉ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እጅግም ደስተኛ ነኝ።

በተለያየ ጊዜ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ጋር በሚደረገው መስተጋብር የበኩሌን ለመወጣት ጥረት አድርጌያለሁ። ወደ ሕዳሴ ግድቡ አምስት ስድስት ያህል ጊዜ ከልዑካን ቡድን ጋር ሔጄ ጎብኝቻለሁ። በዚህ ግድብ ላይ ኢትዮጵያውያን በቁርጠኝነት የመሳተፋቸውን ያህል ከአጼ ኃይለስላሴ ጀምሮ ያሉ የኢትዮጵያ መሪዎች ጥናት በማስጠናት ብርቱ ትግል ከማድረግ እስከ ግድቡን መጀመርና መፈጸም የደረሱ በመሆናቸው ታላቅ ስኬት ነው።

እኔን በጣም ያስደሰተኝ ኢኮኖሚያዊ ድሉ አይደለም። ፖለቲካዊ ስኬቱ ነው። በጣም ያስገረመኝ ነገር ቢኖር ጦርነትን ማክሸፍ መቻላችን ነው። ምክንያቱም ከሕዳሴው ግድብ በተቃራኒው የቆሙ አካላት ሁሌም አማራጫቸው ጦርነት ነው። የታላቁ ሕዳሴ ግድብ እውን መሆን ኢኮኖሚያዊም ፖለቲካዊም ውጤት አሳየ ማለት ነው። ስለዚህ ይህ በግድቡ የተገኘው ውጤት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ድል ነው። እንዲሁም ሞራላዊ ድል ነው። በዚህ ደግሞ በጣም ደስተኛ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ የቀድሞ ዲፕሎማት እንደመሆንዎ ባለፉት አምስት ዓመታት በተለይ ደግሞ ባለፈው ዓመት የነበረውን ዲፕሎማሲያዊ አካሔድና ውጤቱን የተመለከቱት እንዴት ነው?**

**ተሻለ (ዶ/ር)፡-** እኔ ቀደም ሲል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ባልደረባ ሆኜ ለ11 ዓመታት ያህል ሰርቻለሁ። በሰራሁበትም ዘመን በተወሰነ መልኩ በአገር ደረጃ በደርግ ዘመነ መንግስት ከሱማሊያ ጋር ጦርነት የነበረበት ጊዜ ነው። በተጨማሪም የውስጥ ጦርነት ነበር። የውስጥ ጦርነቱ ልክ አሁን እንደምናየው አይነት ነው ማለት ይቻላል።

በእኔ እምነት ለውጪያዊም ሆነ ለውስጥ ጦርነቶች ባለቤቱ አንድ ነው። በዚያን ወቅት ግጭቶች ሁሉ የሚዘወሩት ከአንድ ጣቢያ ነው የሚል አተያይ አለኝ። እሱም ካይሮ ላይ ነው ባይ ነኝ። ከእርሷ ኋላ ያለች ደግሞ ዋሽንግተን ናት፤ እዚህ ላይ ምንም አይነት ብዥታ ሊኖር አይገባም። ስለዚህ አሁንም እየተደገመ ያለው የዚያ አይነት አካሄድ ነው።

በእርግጥ ዲፕሎማሲ በየዘመኑ የሚፈተንበት ወቅት ይኖራል። በእርግጥ ሁሉም ዘርፎች ይፈተናሉ። ነገር ግን ያንን ፈተና ለመቋቋም አንደኛ አንጻራዊ ሰላምን እየጠበቅን መሆን አለበት። በወቅቱ የደርግ መንግስት ሲያደርግ የነበረው ሰላምን ለማስፈን ደፋ ቀና ከማለት ጎን ለጎን ልማትንም በማሳለጥ ነበር። እንዲሁም መሰረት ልማትንም በማስፋፋት መታገልን ምርጫው አድርጎ ነበር።

በአሁን ወቅት ደግሞ እየተካሔደ ያለው ነገር ሲጤን የመሰረተ ልማቱ ስራ በስኬታማነት እየተሰራ በመሆኑ በአገር ውስጥ ፈታኝ የሆኑ ነገሮች ያሉ አያስመስለውም። በገጠርም ሆነ በከተማ አካባቢ እየተካሔደ ያለው ልማትና እድገት የሚያስገርም ነው። በተለይም ደግሞ ዲፕሎማሲያዊ አካሔዱ ሲታይ ባለፈው ዓመት ብቻ በርካታ ውጤታማ ስራዎች በመሰራታቸው በዘርፉ ብዙ ድል መመዝገቡ ሲታይ አስደናቂ ነው። ኢትዮጵያ ከባድ ውጥረት ውስጥ ሆና እና ጉሮሮዋ ታንቆ ባለበት በዚህ ጊዜ ውስጥ ጉልህ ስራዎች እየተሰሩ ነው።

በተለይ የዲፕሎማሲያዊ ስራ ላይ በእኔ በኩል ከሚጠበቀው በላይ ድልን መቀዳጀት የተቻለበት ዓመት ነው ብዬ መናገር እችላለሁ። በጣም ብዙ ነገርም እየተሰራ መሆኑን ማስተዋል ችያለሁ። ዲፕሎማቶቻችንም ሆኑ አምባሳደሮቻችን በአሁኑ ወቅት የእረፍት ጊዜ የሌላቸው መሆኑን ማጤን ይቻላል። በመንግስት በኩል በየአቅጣጫው ያለው እንቅስቃሴና ውጤቱ ሲታይ ያለዕረፍት እየተሰራ መሆኑን አመላካች ነው። እየተሰራ ያለው ስራ እንደ ዲፕሎማትም እንደ ወታደርም፤ እንደ ዲፕሎማት ጭምር እየተነጋገሩ የሚሰሩበት ወቅት ላይ እንገኛለን።

የውስጥና የውጭ አፋኝ ኃይሎችን ሁሉ መቋቋም የሚያስችለው መሳሪያ እግዚአብሔር ራሱ እርዳታ ካላደረገ በስተቀር አንዳንዴ የኢትዮጵያ ጉዳይ እንቆቅልሽ ሆኖ የሚታይ ጊዜ እንዳለ ግን መሸሽግ አልችልም። የኢትዮጵያን ጉዳይ ዝም ብዬ ሳጤነው እጅን በአፍ የሚያስጭን ሆኖም የሚታየኝ ጊዜ ይበዛልና ነው።

በተለይ ከዲፕሎማሲው አኳያ የብሪክስ አባል አገር የሆንበት ምክንያት በተሰራው ያላሰለሰ ስራ ምክንያት ነው። ይህም ታላቅ ድል ሆኖ የተመዘገበ ነው። ይህ የብሪክስ አባልነታችን ጉዳይ ለእኔ እጹብ ድንቅ የሆነ ድል ነው። ምክንያቱም ይህ የብሪክስ አባልነት ቅቡልነታችን የሚያስገርመኝ ጉዳይ ነው። ግብጽ ልክ እንደ እኛው አዲስ ገቢ ባትሆንና ቀድማ ገብታ ቢሆን ኖሮ እንዳንገባ ትገዳደረን ነበር ስልም ሐሳቤን መግለጽ እሻለሁ።

ሌላው በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ተከስቶ የነበረው ግጭት በሕይወትም በንብረትም ጉዳት ያስተናገድንበት ቢሆንም በመጨረሻ በሰላም መቋጨት መቻሉ የዲፕሎማሲ ውጤት ነው። በእርግጥ በዚህ ላይ ውጣ ውረድና ከፍታና ዝቅታ እንዳለ የሚታወቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አንድ ፖለቲከኛና የሕግ ሰው የቀጣናዊ ትስስራችን ምን መምሰል አለበት ይላሉ?**

**ተሻለ (ዶ/ር)፡-** እኔ መሆን አለበት የምለው፤ ቀጣናዊ ትስስሩ በኢትዮጵያ ሐሳብ አመንጪነትና የበላይነት መሳለጥ አለበት ነው፤ ይህን የምለው ስሜታዊ ሆኜ አይደለም፤ አገሬ አቅም ስላላትም ጭምር ነው። በተለይ ደግሞ እኔ በዚህ መንግስት እምነት አለኝ፤ ይህንን አልክድም። በኢትዮጵያ መንግስት መሪነትና የበላይነት ቢመራ እድለኞች ነን ባይ ነኝ፤ ይህ መሆኑ ጠቀሜታው ደግሞ ለእኛ ብቻ ሳይሆን በዙሪያችን ላሉ ለቀጣናው አገራት ጭምር ነው።

ይህ ሲሆን ሰላም ይሰፍናል፤ መከባበርና የጋራ እድገት ይመጣል። በአሁኑ ወቅት በቀጣናው ያለው ድባብ ደስ የማይል ነው። ነገር ግን ያንን ደስ የማይለውን አየር መቀየር የሚችል ባለራዕይ ከኢትዮጵያ ውጭ ያለ አይመስለኝም። ኢትዮጵያ እና መሪዎቻችን ይህን መጥፎ ድባብ ለመቀየር እቅዳቸውን ቢገፉበት ውጤታማነቱ ለአገርም በዙሪያው ላሉትም አገራት ነው።

ዲፕሎማሲውም ሆነ ፖለቲካው በእኛ አሸናፊነት ቢሄድ እና የመሪነቱን ቦታ ኢትዮጵያ ከጨበጠች ሌሎች ከእኛ ጋር ስለሚተባበሩ የተሻለ ቀጣናን ትስስርን ለመፍጠር ያስችላል ብዬ አስባለሁ። የቱንም ያህል ጋሬጣ ቢበዛብንም በመሪነታችን ስፍራ ላይ ሆነን መቀጠል አለብን። የመሪነታችንን ሚና ለጎረቤት አገር ሳይሆን ያውም ከሩቅ ለመጣ አካል አሳልፈን መስጠት የለብንም። ምክንያቱም ቀጣናውን መምራት የሚያበቃን ብዙ አሳማኝ ነገሮች ጭምር ስላሉን ነው። ስለዚህም የመሪነቱ ሚና በእዚህ ትውልድና መንግስት እጅ ላይ ያለ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ብዙዎች ኢትዮጵያውያን፤ ኢትዮጵያ ቋሚ ጠላት እንዳላት አድርገው ይቆጥራሉ፤ እንደ አንድ የቀድሞ ዲፕሎማትም**

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## “ግብጽና ሶማሊያን በተመለከተ...

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

**ሆነ ፖለቲከኛ ቋሚ ጠላትም ሆነ ቋሚ ወዳጅ አለ ብለው ያምናሉ?**

**ተሻለ (ዶ/ር)፡-** ቋሚ ወዳጅ፣ አልፎ አልፎ ጠላት ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል። ከዚህ የተነሳ ቋሚ ወዳጅም ሆነ ቋሚ ጠላት አለም፤ የለምም እላለሁ። ይህ የእኔ እምነት ነው። ቋሚ ጠላት አለን ያልኩበት ዋና እና በቂ ምክንያት ስላለኝ ነው፤ ይህን የምለው ዛሬም ብቻ አይደለም፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እየሰራሁ ባለሁበት በ1970ዎቹ ዓ.ም የጎረቤት አገራት ኤክስፐርት ነበርኩ። ሁልጊዜ የሚያነጫንጩኝ በርካታ ምስጢራዊ መረጃዎች በእጄም ገብተው ነበር። በወቅቱም ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ አለቃዬ ስለነበሩም በአጎራባች አገራት አብሬያቸው እንቀሳቀስ ነበር። በእነዚያ ጊዜያት የማይናቁ መረጃዎችንም አውቅ ስለነበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁንም ባጤንኩት ሁኔታ ግብጽን ቋሚ ጠላታችን ናት እላለሁ።

ለዚህ ምክንያቴ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከወዲያኛውም የትኛውንም መሪዋን ብትቀያይርና የትኛውም ፓርቲ ቢመራት በኢትዮጵያ ላይ ያላትን የጠላትነት አቋሟን የማትቀይር አገር ናት። ወታደራዊም መንግስት ይምጣ ሲቪል፤ በተለይ የዓባይን ውሃ በተመለከተ ያላቸው አቋም አንድ አይነት ነው። የአባይ ወንዝ ቋሚ ውሃ እንደሆነው ሁሉ ግብጽም የኢትዮጵያ ቋሚ ጠላት ሆና ዘልቃለች፤ ትቀጥላለችም።

የተፈጥሮ ሀብቱን በመተባበርና በጋራ ማልማት ይቻላል። ኢትዮጵያ ደግሞ በፊትም ሆነ አሁን እያራመደች ያለችው መርህ ይህንኑ ነው። እርሷ ግን በጣም ራስ ወዳድ የሆነች አገር ስትሆን፣ ምሁራኗም ጭምር እንደዚያው ናቸው። 24 ሰዓት ምርምር የሚካሔደው በኢትዮጵያ ዙሪያ ነውና ነው።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ ሆኜ በተለያየ ጊዜ ወደግብጽ አቅንቻለሁ። በፐብሊክ ዲፕሎማሲ በኩልም እንዲሁ ተጉዥያለሁ። ሕዝቡንም ሆነ የተለያዩ ተቋማትንና ተማሩ የተባሉትን ባነጋገርናቸው ጊዜ ብዙዎቹ የዓባይን ውሃ መነሻ እንኳ ጨርሶ የማያውቁ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። ብዙዎቹ የሚቆጥሩት የናይል ውሃ መነሻው ከምስራቃዊ ግብጽ በኩል እንደሆነ ነው። ለቀሪዎቹም ቢሆን እውነተኛ መነሻውን የሚያስተምራቸው የለም።

ስለዚህ ግብጽ ቋሚ ጠላታችን ስለመሆኗ ከመናገር የሚያሸኮረምመን ነገር አይገባኝም ባይ ነኝ። ኬንያን ወይም ሌላውን አገር በምናይበት መነጽር ግብጽን ለማየት መገደድ የለብንም። ከሌሎቹ ጋር በተለያየ ነገር ላንስማማ እንችል ይሆናል፤ ነገር ግን በመነጋገርና በመወያየት የሚፈታ እና ስናደርገውም የመጣነው ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በአንድ ቤተሰብ መካከል እንኳ መጋጨት አለ፤ መስማማትም አለ። ስለዚህ ግብጽና ሱማሊያን በተመለከተ ግን አካሔዳችን የተጠና መሆን አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘት የሚያስችላትን ስምምነት ከራስ ገዟ ሱማሌላንድ ጋር መፈራረሟ ይታወሳል፤ ይህን ጥያቄ በማንሳቷ ብቻ ብዙ ተግዳሮት እየደረሰባት ነው፤ ኢትዮጵያ ጥያቄውን ማንሳቷ ክፋቱ ምኑ ላይ ነው ይላሉ?**

**ተሻለ (ዶ/ር)፡-** አለመታደላችን ሆኖ ነው እንጂ ይሻለን የነበረውማ የራሳችንም አሻራ ያረፈበት አሰብ ነበር። አሰብም ሆነ ምጽዋ የቀድሞ መንግስቶቻችን አሻራ ያለበት ነበር። የኢሕአዴግ መንግስት ትቶልን ከሔደው ነቀርሳ መካከል አንዱ የጎሳ ፖለቲካ ሲሆን፣ ሌላው ወደብ ማሳጣትን ነው። ኤርትራ ነጻ አገር ልሁን በማለቷ እዛ ላይ ብዙ ማለት አልፈልግም። ነገር ግን ታላቅ ሕዝብንና አገርን መውጫ እና መግቢያ በር እንዳይኖረው አድርጎ የከረቸመበት የኢሕአዴግ መንግስት የሁልጊዜ ተወቃሽ እንደሆነ ይዘልቃል።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እጅግ እየጨመረና እያደገ ነው። ከተጠበቀው በላይ እየሆነ በመምጣቱ የግድ ወደብ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፤ ለዚህ የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄን ደግሞ የዓለም አቀፉም ሕግ ቢሆን የሚፈቅድ ነው። ኢትዮጵያ የባሕር በርን በሰላማዊ መንገድ ማግኘት እንደምትችል አያጠራጥርም። ደግሞም የኢትዮጵያ መንግስትም ወደዚህ ጥያቄ ሲገባና ሲፈራረም ዝም ብሎ ዘው ያለበት ነገር እንዳልሆነ የሚታወቅ ነው። ወደ ፊርማውም የገባው የተለያዩ አማራጮችንም አይቶና ገምግሞ እንደሆነ የሚታመን ነው።



በጅቡቲ ብቻ የሚደረገው ቅብብሎሽ ኢትዮጵያን በፈለገችው ልክ ሊያስተነፍሳት አላስቻላትም፤ ኢትዮጵያ በጣም እያደገች ነው። ከዚህ የተነሳ በብዙ አቅጣጫ ብዙ አማራጮችን ያየች ስትሆን፣ ምንም እንኳ እነዚያ ላይ ተስፋዋ ባይሟጠጥም አማራጯን ማስፋት ግድ ይላታልና ያንን ማድረጓ አግባብ ነው።

ይሁንና ይህ የኢትዮጵያ ጥያቄ እንዳይሳካ በውስን ኃይላት ብዙ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፤ እንዲያውም ግብጽ ወደ ጎረቤት አገር ሱማሊያ የመምጣቷም አንዱ ገፊ ምክንያት ይህን ለማሰናከል በማሰብ እንጂ ለሱማሊያ ወይም ለሱማሊላንድ አስባ እንዳልሆነ የሚታወቅ ነው። ይሁንና ኢትዮጵያ ጤናማ በሆነ መንገድ ጥያቄዋን አቅርባ መስመር ውስጥ እየገባች በመሆኑ ከዚህ በኋላ ወደኋላ ማለት አይቻልም። በዚህ በኩል ከሕዝቡም ዘንድ ለመንግስታችን ድጋፍ ያለ በመሆኑ የሚጠበቅብን ከግብ ለማድረስ መስራት ብቻ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርበት ያሉ ጎረቤት አገራትም ሆኑ በርቀት ያሉ አገራት ኢትዮጵያን ተረድተዋታል ብለው ያስባሉ?**

**ተሻለ (ዶ/ር)፡-** እኛ ብዙ ወዳጆች አሉን፤ እኔ በራሴ የግል ምክንያትም ሆነ በሌላ ሌላ ምክንያት ወደውጭ አገር ወጣ ገባ የምልበት ምክንያት ብዙ ነው። ከብዙ የውጭ ዜጎች ጋር የምገናኝበትም ጉዳይ በርካታ ነው። እናም የታዘብኩት ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ በብዙዎቹ ዘንድ ቀድሞውኑም ቢሆን ታዋቂ መሆኗን ነው። ኢትዮጵያ፣ ከአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ታዋቂ ናት። ምክንያቱ ምንድን ነው ያልሽኝ እንደሆን አንዳንዴ ለጥፋት የመጣብን ነገር ኢትዮጵያን የበለጠ እንድትታወቅ አግዟታል። አጼ ቴዎድሮስ ያደረጉት ውጊያ እርሳቸውንና ኢትዮጵያ ይበልጥ እንዲታወቁ ያበቃ ነው። ወደ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክም ሆኑ አጼ ኃይለስላሴ ዘንድ ሲመጣም የሆነው ነገር ተመሳሳይ ነው።

የተደረጉብን የግፍ ጦርነቶችና ጥቃቶች እና በቅኝ አንገዛም ባይነታችን አገራችን ኢትዮጵያን በብዙዎቹ ዘንድ እንድትታወቅ ያደረጋት ነው። በደርግም እንዲሁ ነው፤ በተለይ በ1969 እና 1970 ዓ.ም አካባቢ፤ ሶማሊያ ልትሸከመው የማትችለውን የጦር መሳሪያ በአሜሪካ አስታጣቂነትና በዛይድባሬ ግንባር ቀደምትነት ዓለም ሁሉ በወቅቱ ሲተባበርብን የሚታወስ ሲሆን፣ ምንም እንኳ ልጆቻችን መስዋዕት ቢሆኑና ኢኮኖሚያችንም ቢጎዳ በኢትዮጵያ አሸናፊነት መደምደሙ ሁሉም የሚያውቀው ሐቅ ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም ልክ እንደ አድዋ ድል የበላይነታችንን ያስተወዋቅንበት ድላችን ነው። በወቅቱ እኔ የኢሰፓ የፓርቲው አንደኛ ጸሐፊ እንዲሁም ከፍተኛ ዲፕሎማትም ስለነበርኩ ጉዳዩን በቅርበት የማውቀው

**የሚያገፋፋን የግል ጥቅም ነው። ግጭት ውስጥ የሚያስገባቸው ለአገር ሳይሆን ለወገን፣ ለሰፈር ምናልባት አልፎ ለጎሳ እና ለዘር በሚል የሚደረግ ጥቅም ፍለጋ ነው፡፡ የዚህ ጥቅም ምንጩ አሁንም ቢሆን ከውጭ ነው**

ጉዳይ ነበር።

ስለዚህ በቅርበትም ሆነ በርቀት ያሉ አገራት ኢትዮጵያን መረዳት ብቻ ሳይሆን በአሸናፊነቷም ጠንቅቀው ያውቋታል። በተመሳሳይ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ የማትበገር አገር ስለመሆኗ አሳምረው ያውቃሉ ባይ ነኝ። መሪያችንም በአሁኑ ወቅት እያደረጉ ያለው ስራ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በማስገረም ላይ ያለ ከመሆኑም በተጨማሪ በዓለም ሚዲያዎችም ሆነ ፖለቲከኞች ዘንድ እውቅናውን አግኝተዋል። እንዲህ ስል የሚጠሉን እንዳሉ ከግምት ውስጥ መግባቱ ሳይዘነጋ ነው።

በጥቅሉ በውጭ በኩል ጥሩ የሆነ የአገር ገጽታ ግንባታ እንዳለን የማይካድ ሐቅ ነው እላለሁ። በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው በኩል አስገራሚ የሆኑ ስራዎች ከመሰራታቸው አልፎ አመርቂ ውጤት እየተመዘገበም ይገኛል። ከፖለቲካውና ከኢኮኖሚው ወጣ ስንል ደግሞ ኢትዮጵያን በተለያዩ መድረኮች የሚያስጠሯት አትሌቶቻችን ሌላው ኩራታችን ናቸው። ዳያስፖራውም ቢሆን ለአገራችን ስኬትም ሆነ እውቅና የተጫወተው ሚና የሚዘነጋ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- በአገር ውስጥ የተፈጠረውን የሰላም መታጣት ማስተካከል የሚቻለው እንዴት ነው? ኢትዮጵያውያንስ እርስ በእርስ መገፋፋታቸውን ትተው ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ድርሻቸው ምን መሆን አለበት ይላሉ?**

**ተሻለ (ዶ/ር)፡-** ኢትዮጵያውያን በተለይ ከለውጡ በኋላ የምንገፋፋውና ግጭት ውስጥ የገባነው ለአገር ሳይሆን ለጥቅማችን ስንል ነው። የሚያገፋፋን የግል ጥቅም ነው። ግጭት ውስጥ የሚያስገባቸው ለአገር ሳይሆን ለወገን፣ ለሰፈር ምናልባት አልፎ ለጎሳ እና ለዘር በሚል የሚደረግ ጥቅም ፍለጋ ነው። የዚህ ጥቅም ምንጩ አሁንም ቢሆን ከውጭ ነው።

በግል ጥቅም ተሳክረው ግር ግር የሚፈጥሩትን የሚያባብሰው እና ቤንዚን የሚያርከፈክፈው ደግሞ ውጭ አገር ያለው አካል ነው። የእርሱ ልጅ ሳይሞትና ንብረቱ ሳይወድም በተደላደለ ሁኔታ ከአገር ውጭ ተቀምጦ እዚህ ያለውን የሚያባላው የውጪው ኃይል ነው።

እንዲያውም በግልጽ እንዳሉትም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ተቃዋሚዎችንና አመጽ የሚያስነሱትን እንደግፋለን ሲሉ የውጭ ኃይሎች ተናግረዋል። እንደ እሱ ማለት ደግሞ መበጥበጣችንን እንቀጥላለን እንደማለት ነው። ብጥበጣውን በዘር፣ በጎሳ፣ በክልልና በሌሎች ነገሮች በመከፋፈል ቀጥለዋል። ይህ ደግሞ የግብጽ አጀንዳ ስለመሆኑ አያጠራጥርም። ይህን የሚያጠናክሩትና እንደ ቤታቸው ወደ ግብጽ መለስ ቀለስ የሚሉ የአሜሪካ ዲፕሎማቶች ናቸው። ምክንያቱም በምስራቅ የአፍሪካ ክፍል መግባት የሚችለው የግብጽ ጦር ነው በሚል እየፈቀደ ያለው ይኸው የኋይት ሃይውስ መንግስት ነው።

የአገር ውስጥ ሰላምን በተመለከተ ገና በእንጭጭነቱ መቅጨት ተገቢ ነበር፤ እንዲህ ስል የሰው ሕይወት ሳይጠፋና ንብረትም ሳይወድም ለማለት ነው። ይሁንና አሁንም ቢሆን ለሰላም ሲባል መሰለቸትና እልህ መግባት አያስፈልግም። መናናቅም ሳይኖር ለሕልውና ሲባል ሰላም ማምጣት ተገቢ ነው። ከውጭ የሚመጣውን ጫና ለማጥፋት በአገር ውስጥ ያለነው አካላት ለሰላማዊ ድርድር ራስን ማዘጋጀት መልካም ነው። ለዚህ ለሰላማዊ ድርድር መንግስትም ሆነ ሕዝብ ጫና መፍጠር አለባቸው።

በተለይ በቦታውና በስፍራው ያሉና ችግር የተፈጠረባቸው ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ሰላምን ፍለጋ ሊነቃቁና ሰላም እንዲታወክ የሚያደርጉትን አካላት “በቃችሁ” ሊሏቸው ይገባል። “ማረስ፣ መነገድ፣ ማምረት እንሻለን” በሚል መነሳሳት ይጠበቅባቸዋል እንጂ ሁሉን ነገር መንግስት ይጋፈጥልኝ በሚል ለመንግስት ብቻ መጣል ተገቢ አይደለም።

በአሁኑ ወቅት የሚያስፈልገው የአሸናፊነት ጥያቄ ሳይሆን የጋራ ቤታችንን በጋራ መስራት ነው። የጋራ ቤትን በጋራ መስራትን የማይፈልግ አካል ካለ ግን ማፍረስ እንደማይችል ሊገነዘብ ይገባዋል። የማፍረስ ተልዕኮ ይዞ የሚንቀሳቀስ አካል ካለ አፈርሳለሁ የሚለው የሌላውን ቤት ብቻ ሳይሆን የእርሱንም ጭምር መሆኑን መረዳት አለበት።

ኢትዮጵያ ይህንን ፈተና ታልፋለች። ታሪክ እንደሚያሳየን ትናንትም የነበረብንን ፈተና በድል ተሻግረናል። ጊዜው ተቀያየረ እንጂ ጠላት ያው ጠላት ነው። ስለዚህ ተስፋ የሚያስቆርጥ አንዳች ነገር የለም። መንፈሰ ጠንካራ ባለራዕይ ሆነን እንሻገራለን። ለዚህ ደግሞ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ሰላምን ለማምጣት ከመንግስት ጋር ሆኖ መስራት አለበት እላለሁ። ሁሉንም ጥፋት ወደመንግስት መወርወርና መቀመጥ ስህተት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በቢሯችን ተገኝተው ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ተሻለ (ዶ/ር)፡-** እኔም ስለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## ዘርፈ ብዙ ምላሽ ለአዕምሮ ጤና

**አስናቀ ፀጋዬ**

ከዓለም ሕዝብ አንድ አምስተኛ ያህሉ እርዳታ የሚሻ የአእምሮ ጤና ችግር ያለበት መሆኑን ከዓለም ጤና ድርጅት በቅርቡ የወጡ መረጃዎች ያሳያሉ። ከዚህ ውስጥ ከ76 እስከ 86 ከመቶ ያህሉ ደግሞ ሕክምና ያላገኙ የአእምሮ ጤና ችግሮች ያለባቸው መሆኑን አመላክቷል።

ይኸው መረጃ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የአእምሮ ጤና ችግር የሚጀምረው በአስራ አራት ዓመት እድሜ ክልል ውስጥ መሆኑንና እድሜያቸው ከ15 እስከ 29 ዓመት ውስጥ ባሉ አምራች ወጣቶች ለሚከሰተው ሞት ራስን ማጥፋት ሁለተኛው ገዳይ ምክንያት መሆኑንም ያሳያሉ።

ከ 90 በላይ የሚሆኑ ራስ ማጥፋት መንስኤዎች የሚከሰቱት ደግሞ ባልታከመ የአእምሮ ጤና ችግር ምክንያት መሆኑንም እነዚሁ መረጃዎች ጠቁመው፤ ከዚህ ውስጥ 78 ከመቶ ያህሉ ራስን ማጥፋት የሚታየው በታዳጊ ሀገሮች መሆኑንም አስታውቀዋል።

በጥቅሉ በድባቴ /depression/ እና ተያያዥ የአእምሮ ጤና ችግሮች ብቻ ዓለማችን በየዓመቱ ከ 2 ነጥብ 5 እስከ 8 ነጥብ 5 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደምታጣም ይኸው መረጃ ይጠቁማል።

በኢትዮጵያም ሁሉንም የአዕምሮ ጤና ሕመሞች ከግምት ውስጥ በማስገባት ከአምስት ሰዎች ውስጥ አንዱ የአዕምሮ ጤና ችግር እንዳለበት ከጤና ሚኒስቴር በተገኙ መረጃዎች አማካኝነት ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህም የስነ-ባህሪይ ችግሮችን (personality disorder)፣ እንቅልፍ ማጣትን፣ ድብርትን፣ ጭንቀት እና ሌሎችም ሕመሞችንም ሊያጠቃልል እንደሚችል መረጃው ይጠቅሳል። ከነዚህ መረጃዎች በመነሳት ለአእምሮ ጤና ትልቅ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ መገመት አያዳግትም።

ለዛም ነው የዓለም አእምሮ ጤና ቀን በየዓመቱ የሚከበረው። የዘንድሮው የዓለም አዕምሮ ቀንም "በስራ ቦታ ለአዕምሮ ጤና ቅድሚያ የሚሰጥበት ጊዜ ነው!" በሚል መሪ ቃል የጤና ሚኒስቴር በሽታ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ስራ አስፈጻሚ፣ የክልል ጤና ቢሮዎችና የሆስፒታሎች ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ በወራቤ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በዚህ ሳምንት ተከብሯል።

የጤና ሚኒስቴር የሚኒስትር ዴኤታ ከፍተኛ አማካሪ አቶ ሌሊሴ አማኑኤል በመድረኩ የመክፈቻ ንግግራቸው እንደገጹት፣ ይህንን ቀን የምናከብርበት ዋነኛ ዓላማ ስለ አእምሮ ጤና ያለው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ በአእምሮ ጤና መታወክ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰቡና እና ዘርፈ ብዙ እየሆኑ በመምጣታቸው፤ ችግሮቹ የሚሹት ምላሽም እንዲሁ ዘርፈ ብዙ በመሆናቸው የአእምሮ ጤና ችግር እያደረሰው ካለው ጫና አንፃር የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እየሰጡት ያለው ምላሽ አናሳ በመሆኑ ነው። ስለሆነም በቅንጅት መስራት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ጤና ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳሙኤል ዳርጌ በበኩላቸው፣ የዓለም በሽታዎች ጫና መረጃ እንደሚያሳየው በዓለማችን የአእምሮ ሕመም ስርጭት ከ1 ነጥብ 5 ቢሊየን በላይ ሰዎች ተጠቂ ሲሆኑ በአህጉራችን በአፍሪካ ወደ 116 ሚሊዮን ያክል ሰዎች ከአእምሮ ሕመም ጋር ይኖራሉ። ከዚህም ውስጥ የድባቴ ሕመም ትልቁን ድርሻ ይይዛል። በሀገራችን በኢትዮጵያ ከ5 ሰዎች አንዱ/ዷ በሕይወት ዘመናቸው ውስጥ በአዕምሮ ሕመም የመያዝ እድል አላቸው። ችግሩን ስፋት ያህል መስራት ብዙ መስራት ይጠበቅብናል ሲሉም አሳስበዋል።

የአእምሮ ጤና ላይ ጤና ሚኒስትር በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፣ ከዚህ ውስጥ የ5 ዓመት የአእምሮ ጤና ስትራቴጂ እቅድ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውል እየሰራ ይገኛል። ‹‹የዛሬው የአእምሮ ጤና ቀን ስናከብር በወራቤ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በአእምሮ ጤና ላይ የተሰሩ ስራዎችን ልምድና ተሞክሮ ለመውሰድ በማሰብ ነው›› ሲሉ በጤና ሚኒስቴር የሽታ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ስራ አስፈጻሚ ዶ/ር ሕይወት ሰለሞን ገልፀዋል።

የወራቤ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር ዶ/ር ካሊድ ሽፉን በበኩላቸው፣ ሆስፒሉ ከአእምሮ ጤና ጋር በተያያዘ እንደ ሀገር ከአማኑኤል ሆስፒታል ቀጥሎ ፎረንሲክ ሳይካትሪ፣ በስፔሻሊቲና ሰብ ስፔሻሊቲ አገልግሎት በመስጠት በተመላላሽ እና ተኝቶ ሕክምና የጎላ አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሆነ ገልፀዋል።

ሁሉም ሰው የትም ቦታ ሁለንተናዊ ጤና እንክብካቤ ማግኘት እንዲችል የጤና ሚኒስቴር የአእምሮ ጤና አገልግሎት ከመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት እስከ ስፔሻሊቲ አገልግሎት ድረስ በሚገኙ የተለያዩ የጤና ተቋማት ተደራሽ እንዲሆን ትልቅ ትኩረት በመስጠት እየሰራ ይገኛል። ይሁን እንጂ አሁንም በአእምሮ ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ በርካታ ችግሮች እንዳሉ ይነገራል።

ዶክተር ሙሉቀን ተስፋዬ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ የአእምሮ ሀኪምና ረዳት ፕሮፌሰር ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፣ የአእምሮ ጤና የባህሪ፣ የስሜትና የአስተሳሰብ ጤንነት ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። ይህም አንድ ሰው በባህሪ፣ በስሜትና በአስተሳሰብ የተረጋጋ ሆኖ በሕይወት ለሚገጥሙት የተለያዩ ጫናዎች መፍትሄ ማበጀት የሚችልበት የአእምሮ ጤና ሁኔታ ላይ ሲሆን፤ በማህበረሰቡም ውስጥም አምራች ሆኖ ሲገኝ የአዕምሮ ጤናው የተሻላ ደረጃ ላይ ነው ብሎ መግለፅ ይቻላል።

እንደ ዶክተር ሙሉቀን ገለፃ፣ የአእምሮ ጤና መታወክ ስርጭቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይ ደግሞ ግጭቶች በሚበዙባቸው ቦታዎች ላይ የስርጭቱ መጠን በጣም ከፍ ያለና ከአራቱ ሰው አንዱ ላይ በሕይወት ዘመኑ እርዳታ የሚሻ የአእምሮ ጤና ችግር እንደሚገጥመው ያሳያል። የኢትዮጵያ ሁኔታም ሲታሰብ የአእምሮ ጤና ችግር እንዳለ ያሳያል። በቅርቡ የተሰሩ ጥናቶችም ይህንኑ ያመለክታሉ።

የአእምሮ ጤና ችግር በብዙዎች ዘንድ ሲታሰብ ወደ አእምሮ የሚመጣው ራሳቸውን የጣሉና የጎዱ ሰዎች ቢሆንም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሰዎች ከአንድ ከመቶ በላይ አይሆኑም። ነገር ግን እንደ አብዛኛው ሰው የሆኑና 99 ከመቶ የሚሆኑት ማሰብና መናገር የሚችሉ ግን ደግሞ በገጠማቸው የባህሪ፣ ስሜትና አስተሳሰብ ጫና የአእምሮ ሕመም ውስጥ የሚገቡ አሉ።

የተሻለ መስራትና ፍሬያማ መሆን ሲችሉም በሕመሙ ምክንያት ጫና ውስጥ የሚቆዩም ይኖራሉ። ይህም በየሁሉም ቤት ውስጥ ያለና ውጤቱም ኢኮኖሚውን፣ ፖለቲካውንና የተሻለ ለመኖር የሚያስፈልጉ እሴቶችንም ጫና ውስጥ የሚከት ነው። ከዚህ አኳያም ሁሉም ግንዛቤውን በማስፋት ለመፍትሄው መረባረብ ይጠበቅበታል።

ጥናቶቹ ከአራቱ ሰው አንዱ በዚህ የአእምሮ ችግር ውስጥ እንደሚያልፍ የሚያሳዩ በመሆናቸው ችግሩ ቅርብ መሆኑንና የጤና ሁኔታን አሳሳቢ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥም አንዱ ስርጭቱ በመሆኑ የአእምሮ ጤና ችግር በኢትዮጵያ እጅግ አሳሳቢ መሆኑንና የእያንዳንዱን ሰው ርብርብ የሚፈልግ ነው። የአእምሮ ሕመም የትኛውንም የማህበረሰብ ክፍል የሚያጠቃ መሆኑ፣ በሌላ በኩል ሕመሙ ሕይወትንም ጭምር የሚቀጥፍ ከመሆኑ አኳያ በሁሉም አቅጣጫዎች ርብርብ ይፈልጋል።

ዶክተር ሙሉቀን እንደሚያስረዱት፣ ከሕክምና ተቋማት ተደራሽነት አኳያ በኢትዮጵያ 10 ከመቶ የሚሆኑ የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ሰዎች ወደ ሕክምና ተቋም በመሄድ ባለሞያ ያገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ የሕክምና ክትትላቸውን አጠናቀውና አስፈላጊውን እንክብካቤ የሚያገኙት ግን ከአንድ በመቶ አይበልጡም። ይህም የሕክምና ተቋማት ተደራሽነትን ከማስፋትና አገልግሎቱን ከማዳረስ አንፃር ብዙ ስራዎች መስራት እንዳለባቸው ይጠቁማል።



የአእምሮ ጤና እንክብካቤ ከመስጠት አንፃርም ቀደም ሲል በተወሰኑ ሆስፒታሎች ብቻ ሲሰጥ የነበረው አገልግሎት በሁሉም ሆስፒታሎች ውስጥ ከሌሎች ሕክምናዎች ጎን ለጎን እንዲሰጥ እየተደረገ ይገኛል። በዓለም ጤና ድርጅት አቅጣጫ መሰረትም ማህበረሰቡ ለአእምሮ ሕክምና አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆንና ባሉት ሆስፒታሎች ውስጥ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ሞያተኞችን ማብቃትና ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራዎች እየተሰሩ ነው። ማግለልና መድሎንም ለመቀነስ ሕብረተሰቡ በነዚህ ሆስፒታሎች ውስጥ ያሉ የአእምሮ ሕክምና አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ይመከራል። ይሁንና ከችግሩ ስፋት አንፃር ይህ በቂ ነው ለማለት አያስደፍርም።

ከአእምሮ ጤና ሕመም ጋር በተያያዘ እንደ ችግር ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የግንዛቤ እጥረት መሆኑን የሚናገሩት ዶክተር ሙሉቀን ታማሚው በራሱ የአእምሮ ጤና ችግር ሲገጥመው ሕመሙ አለብኝ ብሎ ላያምን ይችላል ይላሉ። አንዱ የሕመሙ መገለጫም ያለውን ሁኔታ መረዳትና እርዳታ የመሻት ባህሪውን ተፅእኖ ስለሚጨምር የሕመሙ ሌላኛው ችግር መሆኑን ይገልፃሉ።

በሌላ በኩል የአእምሮ ሕሙማንን በሕክምና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የማህበረሰቡ ንቃተ ሕሊና አለማደግ በራሱ ሌላ ችግር መሆኑንና በአእምሮ ጤና ላይ ያለው ግንዛቤ ማነስም ትልቅ ማነቆ ሆኖ መቆየቱን ዶክተር ሙሉቀን ይጠቁማሉ።

ይህንን ሁሉ መንገዶች አልፎ ታማሚው በራሱ ተነሳሽነት፣ በቤተሰብና በሕብረተሰብ እገዛ የሕክምና አገልግሎቱንና ርዳታውን ለማግኘት ፍላጎቱ ቢኖረው እንኳን ረጅም መንገድ ለመጓዝ እንደሚገደድ ያመለክታሉ። ታማሚው በበቂ ሁኔታና ሕክምናው በሚፈቅደው አግባብ ለምሳሌ ተኝቶ መታከም ቢፈልግም አገልግሎቱን በቀላሉ ማግኘት እንደማይችልም ይገልፃሉ። በዚህም ምክንያት ረጅም ጉዞ ላለመሄድ ታማሚዎች አገልግሎቱን ማግኘት እየፈለጉ በቤታቸው ለመቅረት እንደሚገደዱም ይጠቁማሉ።

ከዚህ ሁሉ ውጣውረድ በኋላም ታማሚዎች የሕክምና አገልግሎቱን ቢያገኙ እንኳን ከመድሃኒት እጥረት ጋር በተያያዘ ለከፋ እንግልት እንደሚዳረጉም ዶክተር ሙሉቀን ያስረዳሉ። አንዳንዶቹም ሕማማቸው እንደገና ሲያገረሽና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ውስጥ ሲገቡ እደሚታዩም ይገልፃሉ።

የአእምሮ ጤና ደህንነትን ለማከም የሚያስፈልጉ ወሳኝ መድሃኒቶችም በአሁኑ ግዜ ገበያ ላይ እንደልብ እንደማይገኙ ጠቁመውም፤ ይህም በተለይ ለአእምሮ ታማሚዎች ረጅም ግዜ የሚሰጡ መድሃኒቶች እንዲቆራረጡ፤ ይህንንም ተከትሎ የጤና ባለሞያው ተነሳሽነት የሚቀንስና የመንፈስ ስብራትንም የሚፈጥር መሆኑንም ይጠቁማሉ። ይሁንና ችግሮቹ ብዙ ወጪ የሚጠይቁ ባለመሆናቸው ጠንካራ ስራዎች ከተሰራባቸው ሊስተካከሉ እንደሚችሉ ይናገራሉ።

ዶክተር ሙሉቀን እንደሚሉት፣ ከአእምሮ ሕክምና ባለሞያዎች ጋር በተያያዘ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ሲሆን በአእምሮ ሕክምና ስፔሻሊስት ደረጃ ሲታይ ቁጥሩ አሁንም አነስተኛ ነው። ይሁንና ከሌሎች አፍሪካ ሀገራት ጋር ሲነፃፀር አበረታች ሁኔታዎች እንዳሉ ያሳያሉ። በስልጠና ላይ የሚገኙና በቀጣይ ወደ አገልግሎት የሚገቡ ባለሞያዎችም አሉ። ይሁንና ከሚፈለገው መጠን ጋር ሲወዳደር የነዚህም ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው።

በተመሳሳይ ሌሎችም በማስተርስ ደረጃ ያሉ የአእምሮ ጤና ሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ባለሞያዎችም አሉ። በአእምሮ ጤና ላይ አተኩረው የሚሰሩ ሳይካትሪክ ነርሶችም ይገኛሉ። የነዚህ ሁሉ ሞያተኞች ርብርብ ነገሮችን ለማሻሻል የራሱ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ሆኖም አሁንም የአእምሮ ጤና ሞያተኞችን በስፋት አሰልጥኖ ማውጣት ያስፈልጋል።

የአዕምሮ ችግሩን ከመፍታት አኳያ ሁሌም የጤና ባለሞያዎች በቅድሚያ የሚመክሩት ቅድመ መከላከልን ነው። ከዚህ አንፃር በቅድሚያ የአእምሮ ጤና ምንነት ላይ በቂ ግንዛቤ መጨበጥ ያስፈልጋል። ከአእምሮ ጤና ጋር በተያያዘ የማህበረሰቡ ንቃተ ህሊና እንዲጎለብትም ሁሉም ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል። የተለያዩ የሞያ ማሕበራትም በአእምሮ ጤና ጉዳዮች ላይ በጋራ መስራትና ግንዛቤ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል።

እያንዳንዱ ግለሰብም በእለት ተእለት ሕይወቱ ለአእምሮ ጤና የሚያግዙ ነገሮችን መተግበር ይጠበቅበታል። ለምሳሌ አመጋገብን፣ የእንቅልፍ ስርዓትን ማስተካከል ጭንቀትና ሃሳብን ለማስወገድ የጤና ባለሞያዎችን ማማከር ያስፈልጋል። ከሱስ አምጪ ነገሮች ራስን ማራቅ፣ ማህበራዊ ሕይወትን ማዳባር፣ መንፈሳዊ ሕይወትን ማጠናከር እንዲሁም የስሜት፣ የባህሪና የአስተሳሰብ ለውጦች ሲያጋጥሙ በቶሎ እርዳታ ማግኘት ችግሩን በአጭሩ ለመፍታት ያስችላል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የከበሩ ማእድናትን የሚያስጌጡት የጥበበኛው እጆች

ፍሬሕይወት አወቀ

አዲስ አበባ ተክለሃይማኖት አካባቢ ተወልዶ ያደገው የዛሬው የስኬት ገጽ እንግዳችን የበርካታ ባለሙያዎች ባለቤት ነው። ለእጅ ሥራና ለጥበብ ልዩ ፍቅር አለው። ከልጅነት እስከ ዕውቀት የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን በመስራት ነው ያደገው። ከዚህ ጎን ለጎንም ለማዕድን ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን፣ በተለይ በማዕድን ዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ በርካታ ዜጎችን መድረስ ችሏል። ስልጠና ከመስጠት በተጨማሪም የከበሩ ድንጋዮችን እያሸሞነሞነ፤ በከበሩ ድንጋዮች ላይ እሴት እየጨመረ ለገበያ ማቅረብ ከጀመረ ሰንብቷል።

የስኬት እንግዳችን አቶ የዝና ማሞ ይባላል። የዝና ጌጣጌጥ እና ተዛማጅ ሥራዎች ማምረቻ ድርጅት መስራችና ባለቤት ነው። የማዕድን ዘርፉን ከተቀላቀለ ከሶስት አስርት ዓመታት በላይ አስቆጥሯል። ከማዕድን ሥራው አስቀድሞ በርካታ የጥበብ ሥራዎች ይሰራ እንደነበርና በተለይም በስዕል ሥራዎች እንደሚታወቅ አጫውቶናል። ለዚህም በመስሪያ ቦታው የሚታዩ ስዕሎች ምስክር ናቸው። ከስዕል ሥራው ባሻገር የሸክላ ሥራ፣ የእንጨት ሥራ፣ ሽመና፣ ቅርፃ-ቅርፅና ሌሎችንም ይጠበብባቸዋል። ለሁሉም የእጅ ሥራ ጥበቦች ተሰጥኦና ልዩ ፍቅር ያለው በመሆኑ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁስን በሙሉ ራሱ ያመርታል።

የጥበብ ሥራ የተሰጠው አቶ የዝና፤ ውስጣዊ ፍላጎቱን በትምህርትና በልምምድ አሳድጓል። የከፍተኛ ትምህርቱን በስዕልና ቅርጻቅርጽ በመከታተልም ዲፕሎማ አግኝቷል። በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅቶ በሚሰራበት ወቅት ያጋጠመው የትምህርት ዕድል ማዕድን ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ በር የከፈተለት እንደሆነም ይናገራል። መንግሥት ባመቻቸለት ዕድል በቻይና የጌጣጌጥ ሙያን ተምሯል። ይሁንና የጌጣጌጥ ሙያን መማር ብቻውን ምንም ዋጋ እንደሌለው በመረዳት በከበሩ ማዕድናት ዙሪያም የተለያዩ ስልጠናዎችን በግሉ እዚያው ቻይና ተመላልሶ ከከበሩ ማዕድናት ጌጣጌጦች እንዴት እንደሚሰሩ ስልጠና ወስዷል። በዚህም የተለያዩ የምስክር ወረቀቶችንም አግኝቷል።

በጌጣጌጥ ሥራ መሰረታዊ ከሚባሉት ማቅለጥ፣ መበየድ፣ መቁረጥ መሳብ፣ ወደ ሽቦ መቀየር፣ ወደ ጠፍጣፋ መቀየርና ሌሎችንም ጨምሮ እስከ መጨረሻ ያለውንና ዛሬ ላይ የደረሰውን ቴክኖሎጂ በስልጠና ማግኘቱን ይገልፃል። ዛሬ ላይ የደረሰው የመጨረሻው ቴክኖሎጂ ካስቲንግ ወይም ሞልዶችንና ጌጦችን በኮምፒዩተር እየታገዙ ዲዛይን ማድረግና መስራት እንደሆነ ጠቅሶ፤ እነዚህን ስልጠናዎችም በግሉ ቻይና ተመላልሶ እንዳገኛቸው ያመለክታል።

በተለያዩ የስዕል ሥራዎቹ እንዲሁም በቅርጻ ቅርጽ ሥራው የሚታወቀው አቶ የዝና፤ የማዕድን ዘርፉን በዕውቀትና በከፍተኛ አቅም ለመስራት እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ትልቅ ደረጃ ላይ የማድረስ ራዕይ ሰንቋል። በተለይም የዝና ጌጣጌጥ እና ተዛማጅ ሥራዎች ማምረቻ ድርጅት ሲመሰረት ከውጭ የሚገቡ ጌጣጌጦችን በሀገር ውስጥ መተካትን ዋና ዓላማው አድርጎ መነሳቱን ይናገራል። ይህንንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ማሳካት እንደሚቻልም ሙሉ ዕምነት አለው።

አቶ የዝና እንደሚለው፤ በአገር ውስጥ በቂና ገና ያልተነካ ሰፊ የማዕድን ሃብት አለ። ይህን ሃብት አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል። በርካታ ጌጣጌጦች ከውጭ አገር እየገቡ ሲሆን፤ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ጌጣጌጦች ቢኖሩም ሥራውን የሚሰሩት አብዛኞቹ የውጭ ዜጎች ናቸው። ይህን ለመቀየር ደግሞ በማዕድን ዘርፍ ስልጠና መስጠት የግድ በመሆኑ ስልጠና ሲሰጥ ቆይቷል። አሁን ላይ ደግሞ ስልጠናውን በመግታት የተለያዩ የጌጣጌጥ ሥራዎችንና የከበሩ ማዕድናትን በማቀላቀል እያመረተ ይገኛል። ምርቶቹን በተለይም ጌጣጌጦቹን ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያም ያቀርባል።

ከሚያመርታቸው ጌጣጌጦች መካከል የጆሮ፣ የአንገት፣ የጣት ቀለበቶች፣ የእግር አልቦና የመሳሰሉት ይገኙበታል። እነዚህን መዋቢያ ጌጣጌጦች ከከበሩ ድንጋዮች እያመረተ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እያቀረበ ሲሆን ለአብነትም ካናዳ፣ አሜሪካና ቻይና ምርቶቹን ልኳል። ለበቅርቡም ምርቶቹን ወደ ቻይና ለመላክ የውል ስምምነት በማድረግ በርካታ የጌጣጌጥ ምርቶችን



አቶ የዝና እንደሚናገረው፤ የከበሩ ድንጋዮች ብዙ አይነት ባህሪያትና የዋጋ ልዩነት አላቸው፡፡ ድንጋዮቹን አንድ የሚያደርጋቸው የጋራ ባህሪም አላቸው

ለመላክ በዝግጅት ላይ ነው። ለሀገር ውስጥ የወርቅ፣ ብርና ጌጣጌጥ መሸጫ ሱቆችም እንዲሁ ምርቶቹን እያቀረበ መሆኑን የጠቀሰው አቶ የዝና፤ ለብርና ጌጣጌጥ መሸጫ ሱቆች በስፋት በማቅረብ ከውጭ የሚገባውን ማስቀረት እንደሚችል ተናግሯል።

አብዛኞቹ ወርቅ፣ ብርና ጌጣጌጥ መሸጫ ሱቆች የሚይዟቸው መዋቢያ ጌጣጌጦች ከጣልያን፣ ከህንድ፣ ከቻይና ከዱባይ እንደሚመጡ የጠቀሰው አቶ የዝና፤ ከእነዚህ ሀገራት የሚገቡትን ምርቶች በከፍተኛ ጥራት በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት ትልቅ አቅም እንዳለና ይህም መቶ በመቶ እንደሚሳካ ሙሉ ዕምነቱ ነው። ለዚህም በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ የከበሩ ድንጋዮች መኖራቸው አንዱና ዋነኛው አስቻይ ሁኔታ ጠቅሶ፤ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍረት መቻሉም ሌላው ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳል። ከማምረት ባለፈም በዘርፉ ያካበተውን ዕውቅት ለሌሎች በማስተላለፍ በርካቶችን አሰልጥኖ በማዕድን ሥራ ባለሙያዎችን መፍጠር ችሏል።

‹‹በጌጣጌጥ ሥራ በርካታ ሰዎችን አሰልጥኛለሁ፤ ይህም ለእኔ ትልቅ ዕድል ነው›› ያለው አቶ የዝና፤ አዲስ አበባን ጨምሮ ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከትግራይና ከደቡብ ክልል የተወጣጡ 230 የሚደርሱ ባለሙያዎችን



ማብቃቱንም ይናገራል። ስልጠናውን ያገኙ ሰዎች በሙሉ ማዕድን በሚገኝበት አካባቢ ነዋሪ የሆኑና ማዕድን ቆፋሪዎች መሆናቸውን ጠቅሶ፤ እነዚህ ሰዎች ባገኙት ስልጠና ማዕድኑን ከማውጣት ባለፈ እሴት ጨምረው መጠቀም የሚችሉበት ሰፊ ዕድል የተፈጠረላቸው መሆኑን ይጠቁማል። ባለሙያዎቹ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ መሆን የቻሉ ሲሆን በተጨማሪም ማዕድኑ እንዳይባክንና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ያመለክታል።

ማዕድን ከመሬት እንደወጣ ሲሸጥና እሴት ተጨምሮበት ሲሸጥ የሚኖረው የዋጋ ልዩነት ሰፊ በመሆኑ በዘርፉ የሚሰጠው ስልጠና የጎላ ጠቀሜታ አለው። በተለይም ማዕድን ቆፍረው የሚያወጡ ሰዎች ስልጠናውን ካገኙ ለዘርፉ የላቀ አበርክቶ አለው። ስልጠናው በዋናነት ማዕድኑ በጥሬው እንዳይሸጥ ያደርጋል። ምክንያቱም፤ አብዛኞቹ የውጭ ዜጎች የከበሩ ድጋዮችን ገና ከአፈር ውስጥ እንደወጡ በጣም በርካሽ ዋጋ ይገዛሉ። ስልጠናው ይህን ማስቀረት ይቻላል። ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትንም ያረጋግጣል።

በተለይም በአሁኑ ወቅት ገበያው አብዝቶ የሚፈልጋቸው ውድ የሚባሉ የከበሩ ድንጋዮች ተመርጠዋል። ከእነዚህም መካከል ኤምራልድ፣ ሳፋየር፣ ሩፒ፣ ቶርማሌ ኦፓልና ሌሎችም ይገኙበታል። እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች ዋጋቸው በጣም ውድና ተፈላጊ ናቸው። ስለሆነም ሁሉም ሰው እነሱ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ነው። በማለት ያመለከተው አቶ የዝና፤ እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች ትልቅ ዋጋ የሚያወጡና ተፈላጊ እንደሆኑ ይናገራል። ጌጣጌጥ እና ተዛማጅ ሥራዎች ድርጅትም በዋናነት እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ነው። በተለይም በማዕድን ዘርፍ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ስልጠናውን እየወሰደ እሴት ጨምሮ መጠቀም እንዲችል ብርቱ ጥረት እያደረገ መሆኑንም ያስረዳል።

አቶ የዝና እንደሚናገረው፤ የከበሩ ድንጋዮች ብዙ አይነት ባህሪያትና የዋጋ ልዩነት አላቸው። ድንጋዮቹን አንድ የሚያደርጋቸው የጋራ ባህሪም አላቸው። ወደ ስልጠና የገባበት ዋናው ምክንያትም ይህ ሲሆን ባለሙያዎች ስለድንጋዮቹ ባህሪያት ማወቅና በጥንቃቄ መጠቀም አለባቸው። ለአብነትም ሳፋየር እጅግ በውድነቱ የሚጠቀስ ሲሆን አንድ ግራም ሳፋየር ከሁለት ሺ እስከ ሶስት ሺ ዶላር ይሸጣል። እሴት ለመጨመር ዕውቀት ይፈልጋል። ስለዚህ በጥንቀቄ መሰንጠቅና መዘጋጀትን ይጠይቃል። ይህ ካልሆነ ግን ይባክናል፤ በዚህ ምክንያት አብዛኞቹ ማዕድናት ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ በጥሬው ይሸጣሉ።

‹‹የማዕድን ሃብት አንድ ጊዜ ብቻ የምናገኘውና መልሰን የማናገኘው ውድ ሃብት እንደመሆኑ በአግባቡና በጥንቃቄ አልምተን ልንጠቀምበት ይገባል›› የሚለው አቶ የዝና፤ መንግሥት ለዘርፉ አሁን ከሰጠው ትኩረት በላይ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያመለክታል። ምክንያቱም አሁን ላይ ማዕድኑ እየወጣ ያለውም ሆነ እየተሰራ ያለው ባህላዊ በሆነ መንገድ በመሆኑ ውጤታማ መሆን አልተቻለም። ስለዚህ ይህን አሰራር በመቀየር ዘርፉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በስልጠና ተደግፎ በባለሙያ ሊመራ ይገባል ባይ ነው።

የማዕድን ሃብትን ከብክነት ለመከላከል ቴክኖሎጂን መጠቀም አንዱ አማራጭ እንደሆነ የጠቀሰው አቶ የዝና፤ በማምረቻ ድርጅቱ የተለያዩ ማሽኖችን እንደሚጠቀም አጫውቶናል። የሚጠቀማቸው ማሽነሪዎችም በእሱ እጅ የተሰሩ ስለመሆናቸው ይናገራል። ከውጭ የመጣውን አንድ ማሽን በመመልከት መለዋወጫውን ብቻ በመግዛት የውጭ አካሉን በሙሉ በሀገር ውስጥ ጥበበኛ የሆኑ እጆቹ መሰራታቸውን ይገልፃል። ከሰራቸው መሳሪያዎች መካከልም መቁረጫ፣ መሰንጠቂያ ዋናዋናዎቹ ሲሆኑ ሁሉንም የጌጣጌጥ ሥራዎቹንም በእነዚሁ መሳሪያዎች እያመረተ ይገኛል።

‹‹የከበሩ ድንጋዮች ከመሬት ውስጥ ወጥተው ሲሸጡና አፈራቸውን ብቻ አራግፈው ሲሸጡ ያለው ልዩነት ሰፊ በመሆኑ ስልጠና ወሳኝ ነው›› የሚለው አቶ የዝና፤ በአሁኑ ወቅት ስልጠና ላገኙ 36 ባለሙያዎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል። በአሁን ወቅትም ከ36 ባለሙያዎቹ ጋር የሚያመርታቸውን የጌጣጌጥ ምርቶችም በስፋት ለሀገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ ከውጭ የሚገባውን ምርት በማስቀረት እንዲሁም ወደ ውጭ በመላክ ጭምር የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ማሳደግ ዋነኛ ዓላማው እንደሆነና ድርብ ጥቅም ያለው መሆኑን ያስረዳል።

ስልጠና በመስጠት በዘርፉ በርካታ ባለሙያዎችን ማፍራት በመቻሉ ደስተኛ እንደሆነ የሚናገረው አቶ የዝና፤ በማምረት ሥራ ውስጥም ስልጠና ስለመኖሩ ይናገራል። አሁን ላይ በዋናነት የሚያመርታቸው ጌጣጌጦች የጆሮ ጌጦች፣ የአንገት፣ የጣት ቀለበት፣ የእግር አልቦና ሌሎችም ይገኙበታል። በቀጣይም የኢትዮጵያውያን ብቻ የሆኑ እንደ መስቀል፣ አሸንክታብ፣ አልቦና ሌሎች ባህላዊ ቁሳቁሶች ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራ ያመለክታል። ‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን የተሻለ ነገር ያለን ህዝቦች ብንሆንም፤ ያሉንን የተሻሉ ነገሮች አውጥተን መጠቀም አልቻልንም›› በማለት ያክላል።

በተለይም የኢትዮጵያ ብቻ የሆኑና ኢትዮጵያዊ ቀለም ያላቸውን ባህላዊ ቁሳቁሶች ኢትዮጵያዊ በሆኑ የከበሩ ድንጋዮች በማምረት ዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥ መግባት እንደሚቻል አመልክቷል። በቀጣይም ጉዞው ወዳዛው እንደሆነ የጠቀሰው አቶ የዝና፤ ለዚህም ሰዓሊና ቀራጺ መሆኑ በብዙ እንደጠቀመው አጫውቶናል። የአቶ የዝና ድርጅት ማንኛቸውም በእጅ የሚሰሩ የጥበብ ሥራዎችን ከስዕል ጀምሮ እየሰራ አሁን ላይ ትልቁን ትኩረት ለማዕድኑ በመስጠት በቀን በትንሹ ሁለት ኪሎ ግራም እንደ መስቀል፣ የጆሮ ጌጥ፣ የአንገት ጌጥና ሌሎችንም ያለቀላቸው ምርቶችን እያመረተ ይገኛል።

በልደታ ክፍለ ከተማ በጥቃቅንና አነስተኛ በግል ኢንተርፕራይዝ ተደራጅቶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው የዝና ጌጣጌጥ እና ተዛማጅ ሥራዎች ማምረቻ ድርጅት፣ በቀጣይ ማስፋፊያ እንደሚያስፈልገውም ያመለክታል። ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት በአገር አቀፍ ደረጃ ትልቅ የጌጣጌጥ ማምረቻ መሆኑን ጠቅሶ፣ በቀጣይም ሥራውን በማስፋት ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መሸጋገርና ተመሳሳይ ድርጅቶችን ማስፋፋት ፍላጎቱ እንዳለው ይናገራል። ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ከማስፋፋት ባለፈ የመስሪያ ማሽኖችን ችግር መፍታት እንዲሁም ከውጭ የሚገቡትን ጥሬ ዕቃዎች ማለትም ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች ግብዓት መሆን የሚችሉ ጥሬ ዕቃዎችንና ሌሎች ጌጣጌጥ ለሚያመርቱ አምራች ድርጅቶች ድንጋዩን በቴምፕሌት አዘጋጅቶ የማቅረብ ዕቅድ እንዳለው ያስረዳል።

ለማዕድን ዘርፍ ሙሉ ጊዜውን የሰጠው አቶ የዝና፤ በስራዎቹና በሚሰጣቸው ስልጠናዎች የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን ጨምሮ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች የምስክር ወረቀቶችን አግኝቷል። ‹‹የማዕድን ሥራ ከትልቅ ኢንቨስትመንት ይልቅ ትልቅ ልብ የሚፈልግና በፍቅር የሚሰራ ሥራ ነው›› በማለት ይገልፃል።

ለሙያው ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ ሥራውን ሲጀምር አንስቶ ያጋጠሙትን በርካታ መሰናክሎች ቱታ ለብሶ አቧራ በማራገፍና በመሥራት ማለፍ እንደቻለ ይገልጻል። ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ የተለያዩ ስልጠናዎችን ለሙያው ፍላጎት ላለቸው በመስጠት እንዲሁም መንግሥታዊ ለሆኑ ጥሪዎች ምላሽ በመስጠትና በመኖሪያ አካባቢውም እንዲሁ አቅሙ በፈቀደው ልክ ድጋፎችን እንደሚያደርግ ነው ያስገነዘበው።

## ተናጋሪው ዶሴ

# የልጅን ለቅሶ ሽሽት

**ምሕረት ሞገስ**

በወጣትነቱ በፍቅር የወደቀው ወጣት ዳዊት ሰለሞን ትዳር ለመመስረት ያለቅጥ ቸኩሏል። ገና በ17 ዓመቱ ከፍቅርተ ቶሎሳ ጋር በጥድፊያ ፍቅር ውስጥ ሲገባ፤ ስለወደፊት ሕይወቱ እምብዛም አልተጨነቀም። ሲያያት ውሎ አቅፏት ቢያድር አይጠግባትም። ፍቅርተ ምንም እንኳን የዳዊትን ያህል ባትሆንም፤ በፍቅር ውስጥ ገብታለች። ሆኖም የሁለቱም ቤተሰቦች ልጆቻቸው በፍቅር መውደቃቸውን አልወደዱትም።

ወጣቶቹ በፍቅር ከመውደቅ አልፈው፤ በትዳር ለመጣመር ሲወስኑ ስለቤተሰቦቻቸው አልተጨነቁም። የአካባቢው ሰው ገሚሱ « አይን ይብላችሁ...» እያለ ሲያንጓጥጣቸው፤ ገሚሱ «ጎሽ...» እያለ እየካባቸው፤ ለተወሰኑ ወራት ፍቅራቸው አገር መንደሩን አስደነቀ። ብዙ አልቆዩም፤ ዳዊት 18 ዓመት ሲሞላው፤ ፍቅርተ ደግሞ ገና በ17 ዓመቷ ትዳር መሰረቱ።

ፍቅርተ እና ዳዊት ትዳር ውስጥ ሲገቡ፤ ምን ሰርተው በምን መልኩ ራሳቸውን እንደሚያስተዳድሩ አልወሰኑም፤ አለመወሰን ብቻ ሳይሆን ምን በልተው በምን አይነት መጠለያ ውስጥ እንደሚኖሩ አላሰቡበትም። ቤተሰብ ሳይፈቅድ እና ሳይደሰት፤ ሽማግሌ ተልኮ ልጃችሁን ለልጃችን ሳይባባል፤ በደፈናው ተያይዘው ተጋብተናል ብለው ከአምቦ ወደ አዲስ አበባ አቀኑ።

### ትዳር

ዳዊት እና ፍቅርተ ትዳር መሰረትን ብለው በጋራ ለመኖር ቢወስኑም፤ ገንዘብ ስለሌላቸው ብዙ መቆየት ተሳናቸው። ዳዊት በትምህርቱ ከ10ኛ ክፍል አልዘለቀም። እንኳን በቅጡ ትምህርቱን አጠናቆ ዲግሪውን ላልጫነ ወጣት ቀርቶ፤ ትምህርቱን በማዕረግ አጠናቅቆ ዲግሪ ለያዘውም መከራ የምታሳየዋ አዲስ አበባ ለዳዊትም ሆነ ለባለቤቱ ፈታኝ ሆነችባቸው።

ፍቅርተ ቤት ውስጥ ያለምንም ሥራ ያለ በቂ ገንዘብ ውላ ስታድር፤ መከፋት ጀመረች። ዳዊት የፋብሪካ ሰራተኛ የመሆን ዕድሉን ስላገኘ፤ ቀን ሲሰራ ውሎ ማታ ለመኝታ ይገባል። ፍቅርተን እንደቀደመው በፍቅር ሊያጫውታት አልቻለም። ጊዜ የለውም፤ ቤት ከገባ በአብዛኛው ከፍቅርተ ጋር ስለውሎዋ ሳያወራ፤ ሳያመሽ ቶሎ ይተኛል። በለሊት ተነስቶ ወደ ሥራ ይሔዳል።

ሰው በተለይም ዳዊት ከጎኗ ሆኖ እንዲያጫውታት የምትፈልገዋ ፍቅርተ ዳዊት ሲተኛ ትበሳጫለች። በእንዲህ መልኩ አንድ ዓመት አለፈ። ፍቅርተ ዳዊትን ብትወደውም ለመለየት አሰበች። ነገር ግን እርሱን ትታ የምትሔድበት አልነበረም። ከዳዊት ጋር ትዳር ስትመሰርት ከቤተሰቦቿ ጋር ተለያይታለች።

አንዳንድ ቀን ተከፍታ ስታለቅስ ትውላለች። ሲመሽ በተስፋ ዳዊትን ትጠብቃለች። ዳዊት ግን ቤት ሲደርስ እንደነገሩ የቀረበለትን እራት ቀምሶ፤ ቶሎ ይተኛል። ዳዊት ፍቅርተን አይቶ ማልቀሷን አያውቅም። እንደውም ሙሉ ትኩረቱን እየነፈጋት ሔደ። ግራ የገባት ፍቅርተ ቀስ በቀስ ከአከራይዋ ጋር መነጋገር ጀመረች። ከሌሎች ተከራይ ጎረቤቶቿ ጋር ማውራት እና ሚስጥሯን ማካፈል ጀመረች። ሁሉም እንድትወልድ መከሯት። ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ ገና በ18 ዓመቷ ፀነሰች።

ዳዊት የፍቅርተ መፀነስ አላስደሰተውም። ልጅ ወልዶ ማሳደግ ቀርቶ፤ ፍቅርተ እና ራሱን በትክክል ለማኖር ተቸግሯል። ፍቅርተም ብትሆን ጎረቤቶቿ መከረዋት እንጂ ልጅ ወልዶ የማሳደግ ጉዳይ እጅግ ሊከብዳት እንደሚችል ገምታለች። ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ ባልና ሚስቱ በተፀነሰው ልጅ ዙሪያ መግባባት ላይ ደረሱ። ዳዊት ፅንሱን አስወርጂ አላት። ፍቀርተ ዳዊት ያላትን በመስማት ውርጃ ይካሔድበታል ወደ ተባለ አንድ የጤና ተቋም አመራች።

በጤና ተቋሙ ውስጥ ያለው ባለሞያ ማስወረድ እንደማትችል እና ፅንሱ ሶስት ወር እንዳለፈው አረዳት። ለማስወረድ ከሞከረች ሕይወቷ ላይ ከባድ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል መከራት። ፍቅርተ ለዳዊት በጤና ባለሞያው የተነገራትን በሙሉ ነገረችው። ዳዊት ለማመን ተቸገረ። በፍፁም ልጅ መውለድ አልፈለገም። ፍቅርተ ዳዊትን እንደምንም ተማፅና እና ብዙ ለምናው ልጁ እንዲወለድ እንዲፈቅድ አስገደደችው። ብዙም ሳይደሰት እንደተከፋ ተስማማ። ፍቅርተ እንደወጉ እርጉዝ ሆና ታየች። እንዳይደርስ የለም የመውለጃ ጊዜዋ ደረሰ።

### የፍራኦል ውልደት

ፍቅርተ ለመውለድ ቀኗ ሲገፋ እንደብዙዎቹ ነፍሰ ጡሮች የገንፎ ዕህል አላስፈጨችም። ቤቴን ላሳምር ብላ አልተጨነቀችም። ለነገሩ የገንፎ እህል ለማስፈጨትም ሆነ ቤት ለማሳመር ብትፈልግም አትችልም። ምክንያቱም የፍቅርተ እና የዳዊት ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ነው። አንዳንዴ ምንም እንኳ እንደማንኛውም ነፍሰጡር ሴት መብላት ብትፈልግም፤ በቤቱ የሚበላ ስለማይኖር ምግብ ሳትበላ የምትውልባቸው ቀኖችም ነበሩ።



ሆዷ እየገፋ ወሯ እየገባ ሲሔድ፤ ዳዊት መጨነቅ ጀመረ። አንዳንዴ እርሷን ላለማየት እንቅልፍ እስኪጥላት አምሽቶ መግባቱን ተያያዘው። አምሽቶ ይገባል፤ ሳታየው ማልዶ ይወጣል። ቤት መግባቱን የምታውቀው እኩለ ለሊት ላይ ከጎኗ ተኝቶ ስታገኘው ብቻ ነው። ቃላትን ሳይለዋወጡ ሳምንታት ተቆጠሩ። ምጧ ሲመጣ ጎረቤቶቿ ስልክ ደወሉለት። ዳዊት ስልክ አንስቶ ምላሽ አልሰጠም። አፋፍሰው ጤና ጣቢያ ወሰዷት። ዳዊት አጠገቧ ሳይደርስ ለጇን ተገላገለች።

ፍቅርተ ዳዊት እና ቤተሰቦቿ ሳይኖሩ፤ በባዕዳን ተከባ በሰላም በመገላገሏ ከዘመድ በላይ (ፍራኦል) ስትል ለልጇ ስም አወጣችለት። ዳዊት ፍቅርተ በሰላም መገላገሏን ከሰማ በኋላ አጠገቧ ተገኘ። በእርግጥም ልጅ መውለድ መቻሉን አየ። አቅፎ የሕፃኑን ግንባር ሳመ። ልጁን እና ሚስቱን ይዞ ወደ ቤቱ ገባ።

ፍራኦል የፍቅርተን ጡት ቢመጠምጥም አይበቃውም። በቂም የሚበላም ሆነ የሚጠጣ ነገር ስለማታገኝ ጡቷ አያግትም። ፍራኦል ሲርበው አምርሮ ያለቅሳል፤ አንዳንዴ ከማልቀስ አልፎ አጥግቡኝ በሚል ድምፀት ይጮሃል። ዳዊት የፍራኦልን ለቅሶ መስማት አይችልም። ማታ ቤት ሲገባ ፍራኦል ካለቀሰ፤ ዳዊት ለፍቅርተ «ልጅሽን ዝም አሰኚው።» ብሎ ይጮህባታል። ደንግጣ ብንን ትልና መልሳ ልጇን አቅፋ አብራ ታለቅሳለች።

### ሽሽት

ዳዊት መጨነቅ የማይፈልግ ሰው ሆኖ፤ ገና በለጋነቱ እርሱ ሳይጠነክር ትዳር መስርቶ ልጅ መውለዱ ቁጭት ውስጥ ከተተው። ሰርቶ የሚያገኘው ገቢ አነስተኛ በመሆኑ፤ ለልጁ ወተት መከራየትም ሆነ በየቀኑ መግዛት ከበደው። ፍቅርተ የሚሰጣት ገንዘብ እንደማይበቃት ስትነግረው ቀድሞም አትውለጂ እያልኩሽ የወለድሽው አንቺ ነሽ ብሎ ደጋግሞ ከመውቀስ ባሻገር፤ « እኔ መጨነቅ አልፈልግም። እንደውም ልጅሽን ይዘሽ የትም መሔድ ትችያለሽ።» እያለ ፍቅርተን ማበሳጨት የየዕለት ተግባሩ አደረገው።

ፍቅርተ በበኩሏ ምንም እንኳ የዳዊት ፍቅር ቢለቃትም ለልጇ ስትል መታገስን መረጠች። ሆኖም ትዕግስቷ ብዙ አልዘለቀም። ልጇ ስድስት ወር ሆኖት ምግብ ሲጀምር፤ ሕፃኑን ፍራኦል ቤት ውስጥ ለዳዊት ጥላለት ለመሔድ ወሰነች። ከልጇ የርሃብ ለቅሶም ሆነ ከባሏ ከዳዊት ወቀሳ ለመሸሽ መጥፋት መፍትሔ እንደሆነ አሰበች። ከማሰብ አልፋ የባሏን የመውጫ ሰዓት ጠብቃ ልጇን አስተኝታ ቀድማ በመውጣት ከአካባቢው ርቃ ሔደች።

ዳዊት እንደለመደው አምሽቶ ቤት ሲገባ ፍቅርተ ቤት ውስጥ የለችም። ሽንት ቤት ሔዳ ይሆናል ብሎ ቢጠብቃትም አልተመለሰችም። በጥበቃ ለሊቱ ተጋመሰ። እናቱ አስተኝታው የሄደችው ሕፃን ፍራኦል ከእንቅልፉ ሲነቃ ፍቅርተ የለችም። እንደለመደው ማልቀስ ጀመረ። የተወለደ ቀን ብቻ ያቀፈው አባቱ ግራ ገብቶት አንስቶ አቀፈው። ፍራኦል ግን ማልቀሱን አላቆመም። ዳዊት ግራ ገባው፤ ለሊቱን ሙሉ ቆሞ አቅፎት አደረ። ጠዋት ሲነጋለት ሕፃኑን ይዞ ወደ አምቦ ጉዞ ጀመረ።

ዳዊት ፍራኦልን ይዞ ወደ አምቦ ለመሔድ የወሰነው ፍቅርተን አገኛታለሁ ብሎ አስቦ ነበር። ነገር ግን ፍቅርተ አምቦ አልተመለሰችም። ልጁን ይዞ ወደ ቤተሰቦቹ ሔደ። ለእናቱ «ፍቅርተን እስካገኛት ተንከባከቢልኝ» ብሎ ለእናቱ ሰጠ። እናቱ ዳዊትን አስጠነቀቁ። በሳምንት ውስጥ ልጁን የማይወስድ ከሆነ ቤቱ ድረስ በመሔድ እንደሚመልሱለት ነገሩት። ዳዊት ልጁን ፍራኦልን ለእናቱ ሰጥቶ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ።

ሥራ ቀርቶ በየመንገዱ ፍቅርተን ቢፈልጋትም ሊያገኛት አልቻለም። ለፖሊስ ጣቢያ አመለከተ። ነገር ግን አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም እንደተባለው አውቃ የጠፋቸውን ፍቅርተ በቀላሉ ልትገኝ አልቻለችም። ዳዊት በአራተኛው ቀን ተመልሶ ወደ ሥራ ገባ። እናቱ ፍራኦልን ያሳድጉታል ብሎ ቢመኝም እንዳሰበው አልሆነም። የዳዊት እናት ከአምቦ ጊንጪ አካባቢ ተነስተው ወደ አዲስ አበባ መጡ። ልክ በሳምንቱ ለዳዊት ልጁን ሰጥተው፤ ወደ አምቦ ተመለሱ።

ፍራኦል እናቱ ጥላው ከጠፋችበት ቀን ጀምሮ ከበፊቱ በባሰ መልኩ አልቃሻ ሆኗል። ዳዊት እናቱ ልጁን ፍራኦልን ጥለውበት ሲሔዱ፤ በኪሱ ምንም ዓይነት ገንዘብ አልነበረም። ወተት መግዛት አልቻለም። ዳዊት ልጁን የሚያበላው እና የሚያጠጣውን ነገር አጣ። መብላት እና መጠጣት የፈለገው ሕፃን ፍራኦል፤ ደጋግሞ ሲያለቅስ ዳዊት ከማባበል ይልቅ መበሳጨት ጀመረ። አልጋ ላይ ወረወረው ፍራኦል ሲያለቅስ ቆይቶ በድካም እንቅልፍ ወሰደው።

የሕፃኑ አባት ለሊቱን ሙሉ ሲያለቅስ የነበረው ፍራኦል እንቅልፍ ስለወደው ተደሰተ። እርሱም ከጎኑ ተኛ። ነገር ግን ከእንቅልፍ መንቃት አይቀርምና ፍራኦል ነቅቶ እንደተለመደው ማልቀሱን ቀጠለ። ቀድሞ የተበሳጨው ዳዊት የሚያደርገው ጠፋው። የጊቢው ሰዎች የሕፃኑን ለቅሶ ቢሰሙም፤ ዳዊትን እናግዝህ አላሉትም። ዳዊትም ጠይቆ መታገዝ አልፈለገም። ነገር ግን ከለቅሶ ድምፅ መሸሽ ፈለገ። እንደሚስቱ ጥሎ ለመጥፋት አላሰበም። ሌላ ሃሳብ መጣለት። ሕፃኑን ገድሎ እጁን ለፖሊስ ለመስጠት ወሰነ።

በጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ አምስት ሰዓት አካባቢ ዳዊት የልጁን የሕፃን ፍራኦልን አንገት አነቀ። የሕጻን ነፍሱ በሲቃ ተጨነቀች። እንደአቅሙ ነፍሱ እንዳትወጣ ተወራጨ። ሆኖም የገጠመው ከንድ ብርቱ ነበር እና ተሸነፈ፤ ትንፋሹም ላትመለስ አመለጠች። አሁን እንደቀደመው ነቅቶ በድጋሚ የሚያለቅስበት ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ አከተመ። የዳዊት ጭንቀላት አረፈ። አባት ዳዊት የሕፃኑን የለቅሶ ድምፅ ሽሽት መጨረሻው ሕፃኑን በመግደል ተጠናቀቀ።

ድርጊቱን የፈፀመው ዳዊት ቀድሞ እንዳሰበው እጁን ለመስጠት አልደፈረም። ይልቁኑ ተደብቆ ማንም ሳያውቅ የሕፃኑን አስከሬን በማዳበሪያ ጠቅልሎ ቆሻሻ ላይ ለመጣል ወሰነ። የሕፃኑ የለቅሶ ድምፅ ማቆምን ተከትሎ ጎረቤቶች መከታተል ጀመሩ። ዳዊት ቀስ ብሎ የሕፃኑን አስከሬን ከጊቢ ይዞ ሲወጣ፤ ጎረቤቶቹ ተመለከቱት። እየተከታተሉት የት ምን እንደሚያደርግ አጣሩ።

ዳዊት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ልዩ ስሙ ማንጎ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ባለ የቆሻሻ መጣያ ሥፍራ ላይ የሕፃኑን አስከሬን በማዳበሪያ ጥሎ ሸሸ። የተከተሉት ሰዎች የጣለውን ማዳበሪያ ሲያዩ የሕፃኑን አስከሬን አገኙ። በፍጥነት ለፖሊስ በማመልከታቸው ዳዊት ሰለሞን በዛው ቅፅበት በቁጥጥር ስር ዋለ።

### የፖሊስ ምርመራ

የደረሰውን ጥቆማ ተከትሎ በፍጥነት ቦታው ላይ የደረሰው የፖሊስ ምርመራ ቡድን የሕፃን ፍራኦልን አስከሬን በጥንቃቄ በማንሳት ለቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ለፎረንሲክ የምርመራ ክፍል አስከሬኑን ላከ። ሳይውል እና ሳያድር በዕለቱ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር አዋለው። የምርመራ ቡድኑ የወንጀሉን መነሻ፣ ወንጀሉ የተፈፀመበትን ሁኔታ የሚያመላክቱ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን አደራጅቶ እና አዳብሮ ለአቃቤ ሕግ አቀረበ።

### የክሱ ዝርዝር

አቃቤ ሕግ በበኩሉ፤ ከፖሊስ የምርመራ ቡድን የቀረበለትን መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን አዳብሮ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 540ን ተላልፎ ተገኝቷል ሲል ክስ ለመመስረት የወንጀል ዝርዝሩን አቀረበ።

አቃቤ ሕግ በክስ ዝርዝሩ ላይ እንዳብራራው፤ የ21 ዓመት ዕድሜ ያለው ተከሳሽ ዳዊት ሰለሞን በጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ልዩ ስሙ ማንጎ ሰፈር በሚባል አካባቢ ከቀኑ 5 ሰዓት አካባቢ «ሕፃኑ ለቅሶውን አላቆም አለኝ» በሚል ሰበብ የሕፃኑን አንገት አጥብቆ በመያዝ ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርጓል። አልፎ ተርፎ የሕፃኑን አስከሬን በማዳበሪያ ቆሻሻ መጣያ ቦታ ወስዶ በመጣሉ በተራ የሰው ግድያ ወንጀል ተከሷል።

በተጠርጣሪው ዳዊት ሰለሞን ላይ የስምንት ምስክሮች ቃል የተደመጠ ሲሆን፤ ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከፎረንሲክ የምርመራ ክፍል የአስከሬኑን የምርመራ ውጤት በተመለከተም በቁጥር ጳሀ8/1529 በጥቅምት 21 ቀን 2016 ዓ.ም የተሰጠ የሟች የሞት ምክንያትን የሚያስረዳ የሕክምና ማስረጃ ቀርቧል። የተከሳሽ የእምነት ክህደት ቃል እና የሟች የአሟሟት ሁኔታ እና የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙን የሚያሳይ 36 ፎቶ እና ተጠርጣሪው የእምነት ክህደት ቃሉን ሲሰጥ የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል የያዘ ሲዲም ለፍርድ ቤቱ ቀርቧል።

### ውሳኔ

ተከሳሽ ዳዊት ሰለሞን በተከሰሰበት ተራ ሰው የመግደል ወንጀል ጉዳዩ በፍርድ ቤት ክርክር ሲታይ ቆይቶ ተጠርጣሪው ጥፋተኛ ነው የሚል ብይን ተሰጥቷል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት በሰኔ 21 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት፤ ፍርድ ቤቱ ክስ እና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ ተከሳሹን ያርማል፤ ሌሎችንም ያስተምራል ብሎ ባመነበት በአስራ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ውሳኔ አስተላልፏል።

# ድንገተኛ ታዋቂነት ብቻውን ሲመጣ

**ዋሰልኝ አየለ**

‹‹አታሞ በሰው እጅ ያምር፤ ሲይዙት ያደናግር›› የሚባለው አባባል በየአጋጣሚዎች ልንጠቀመው የሚያስገድድ ገላጭ አባባል ነው። ‹‹ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው›› የሚለውም ይተካዋል። የእነዚህ ሁለት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ትርጉም፤ እኛ ልናደርገው የማንችለውን ነገር፣ ሌላ ሰው ሲያደርገው ግን እንተቻለን፣ እንወቅሳለን ለማለት ነው።

ታዋቂ ሰዎች መድረክ ላይ ወይም ሚዲያ ላይ ቀርበው በሚናገሩት ነገር አጀንዳ ሲሆኑ ይስተዋላል። ተቀምጦ የሚከታተላቸው ሰው ነገሮችን ለማሰላሰል፣ ዓውዳዊ ትርጉም ለመስጠት፣ መባል ያለበትንና የሌለበትን ለማገናዘብ የተረጋጋ ቀልብ አለው። ስለዚህ የተናገሯትን ሁሉ ይመነዝራል። ተናጋሪው ግን በተለይም የቀጥታ ሥርጭት ከሆነ፤ በሆነ ቅጽበታዊ ስሜት ሊሳሳት ይችላል። የፕሮዳክሽን ቀረጻም ቢሆን በየመሐሉ ‹‹ይሄን ቁረጡልኝ›› አይልም። የሚቆረጠውንና የማይቆረጠውን የሚወስነው የሚዲያው ዝግጅት ክፍል ነው። እንደ ሚዲያው ባሕሪ ደግሞ አነጋጋሪ የሆነ ነገር የሚፈልግም ይኖራል፤ ያንን ርዕስ ያደርገዋል። በአጭሩ ታዋቂ ሰዎች ሰው ናቸውና በቅጽበታዊ ስሜት ሊሳሳቱ ወይም መባል የሌለበት ነገር ሊናገሩ ይችላሉ ለማለት ነው።

ዋናው ጉዳዬ ግን ብዙ ታዋቂ ሰዎች ታዋቂነት ብቻውን የመጣባቸው መሆኑን ነው። ምንም እንኳን በቅጽበታዊ ስሜት ማንኛውም ሰው አግባብ ያልሆነ ነገር የሚያስብና የሚያደርግ ቢሆንም፤ ታዋቂነት ሲመጣ ግን ተደራሽነት ይሰፋልና ጥንቃቄ ያስፈልጋል፤ አዋቂ ለመሆን መዘጋጀት ያስፈልጋል።

ከወቀሳው በፊት ግን አንድ ነገር ላድንቅ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የማያቸው ወጣቶች አስተዋይነታቸው፣ ትሕትናቸው፣ ጥንቃቄያቸው ይገርመኛል። በሆነ አጋጣሚ ታዋቂ ሆነው ቴሌቪዥን ላይ ሲቀርቡ፤ የሆነ ስህተት ሠርተው ይህ የተወደደላቸው ታዋቂነት እንዳይበላሽ እያልኩ እሳቀቃለሁ። ሲናገሩ ግን ምሑራን ላይ እንኳን የማይታይ ትሕትና እና ጥንቃቄ ያላቸው ናቸው። በተለይም አንዳንዱ ጠያቂ የተመልካች ቀልብ ለመያዝ ሲል ወይም ፕሮግራሙን ለማስተዋወቅ ሲል የማይጠየቅ ጥያቄ ይጠይቃል። በዚህ ጊዜ ልጆች በጥንቃቄና በጥበብ የሚወጡበት መንገድ ያስደንቀኛል።

እዚህ ላይ አንድ የሥራ ባልደረባዬ በቅርቡ ያጋራኝን ሀሳብ ልጨምር። ‹‹የ12ኛ ክፍል ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ከውጤታቸው በላይ የሚያስገርመኝ አስተዋይነታቸው ነው›› ነበር ያለኝ። እኔም በቀረቡበት ሚዲያ ሁሉ ልብ ብዬ ሳይ ከአካዳሚ ውጤታቸው በላይ አስተዋይነታቸው አርዓያ ይሆናል። በልማዳችን እውቀት የምንለው ሒሳብ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ... በአጠቃላይ አካዳሚያዊ በሆኑ የትምህርት አይነቶች ነው። ዳሩ ግን ሁለገብ የሆነ አስተዋይነትና ግንዛቤ ነው ብቁ የሚያደርጋቸው።

አንዳንድ በዘፋኝነት ወይም በሆነ ተሰጥዖ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ሰዎች ሚዲያ ላይ ቀርበው ሲናገሩ ስሰማ ያስደምሙኛል። በዚህኛው ሙያ ውስጥ ሆነው እንዴት ይሄኛውን አወቁት እያልኩ እቀናባቸዋለሁ። አስተዋይ ናቸው፤ ጠንቃቃ ናቸው። መባል ያለበትንና የሌለበትን እንደ ዓውዱ የሚለዩ ናቸው።

በተቃራኒው ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አሳቃቂ የሆነው ታዋቂነት በድንገት የመጣባቸው ሰዎች ነገር ነው። አዋቂነት ሳይኖራቸው በሆነ ድንገተኛ አጋጣሚ ታዋቂነት ይመጣባቸዋል። እነዚህ ሰዎች በቀረቡበት ሚዲያና መድረክ ሁሉ የሚያሳቅቅ ንግግር ያደርጋሉ፤ በእርግጥ አንዳንዶቹ መነጋገሪያ መሆኑን ስለሚፈልጉትም ነው ይባላል።

ታዋቂ ሲሆኑ ብዙ ልብ መባል ያለባቸው ነገሮች አሉ። ምክንያቱም ታዋቂ ሲሆኑ ብዙ ሚዲያ እና መድረክ ላይ የመቅረብ ዕድሉ ይመጣል። እነዚህ መገናኛዎች ላይ ሲቀረብ ተደራሽነት ይሰፋል፤ በብዙዎች ዓይንና ጆሮ መግባት ይመጣል። ስለዚህ ‹‹ወደ ሕዝብ ስሄድ ምን መሆን አለብኝ?›› ለሚለው ከፍተኛ የሆነ ቅድመ ዝግጅት ያስፈልጋል። በየዘርፉ ያሉ ጓደኞቻቸውን ማማከርና መጠየቅ ያስፈልጋል። ማንበብና ሚዲያዎችን መከታተል ያስፈልጋል። በትንሹም ቢሆን ሀገራዊ ጉዳዮችን ማወቅ፣ ቢያንስ ጉልህ ጉልህ የሆኑትን ታሪካዊ ክስተቶችንና የሀገር ባለውለታዎችን ማወቅ ያስፈልጋል።

ችግሩ ግን ታዋቂነት በድንገት ለመጣባቸው ሰዎች ከዜሮ መጀመር ነውና አስቸጋሪ ያደርገዋል። በአስተዳደጋቸው ያልነበረ ነገር ከሆነ፤ በድንገተኛ ታዋቂነት አዋቂነት ሊመጣ አይችልም፤ ምክንያቱም ታዋቂ ከሆኑ በኋላ ጊዜ የላቸውም። በብዙ ነገር ይዋከባሉ፤ የሚያስተናግዱት ሰው ይበዛል። ስለዚህ አላዋቂ ሆኖ ለመቅረት ይገደዳሉ ማለት ነው።

ታዋቂነት በድንገት የመጣባቸው ሰዎች በየመድረኩና በየሚዲያው በሚሠሩት ስህተት ሲወቀሱ፤ ብዙ ሰዎች ‹‹ምን አገባችሁ! አርፋችሁ የራሳችሁን ኑሮ ኑሩ፣ ምቀኝነት ነው..›› ይላሉ። ‹‹የወፍ ምስክሯ ድንቢጥ›› መሆኑ ነው። አንድ ሰው በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ አያገባህም አይባልም። ሀገራዊ ጉዳይ የሚሆኑት እነዚህ ትንንሽ የሚመስሉ ማኅበራዊ ጉዳዮች ናቸው።

ከምንም በላይ ግን አንድ ልብ ያልተባለ ነገር አለ። እነዚህ ዕውቀትና ግንዛቤ የሌላቸው ታዋቂ ሰዎች ዝም ከተባሉ ነገ የሀገራዊ ጉዳይ ተሳታፊ ሆነው ይመጣሉ። በአንዳንድ መድረኮችም አይተናል፤ መንግሥት የሕዝብን ቀልብ የያዘ መስሎት በድንገት ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን በአንዳንድ ቤተ መንግሥታዊ ጉዳዮች ሳይቀር ተሳታፊ ሲያደርግ ይስተዋላል። የሚፈለገው ፊታቸው መታወቁ ብቻ ነው ማለት ነው?

እነዚህ ድንገተኛ ታዋቂዎች ዝም ከተባሉ ለትልልቅ ኃላፊነቶች ይታጫሉ፣ ይመረጣሉ ማለት ነው። ብዙ ጊዜ የምናየው ችግርም ይሄው ነው፤ ከብቃት ይልቅ ፊታቸው በስክሪን ስለታወቀ ብቻ ለሆነ ኃላፊነት መምረጥ፣ አማካሪ ማድረግ።

ታዋቂ ሲሆኑ አማካሪ ያስፈልጋል። አማካሪ ማለት የግድ በከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ደረጃ ያለው አይነት ማለት አይደለም። ለሚፈልጉት ዘርፍ ቅርበት ያለውን ሰው መጠየቅ ማለት ነው። ዳሩ ግን እነርሱ ማንን ፈርተው ያማክራሉ? እንደፈለጋቸው ይሳሳታሉ፣ እንደፈለጋቸው ያደርጉታል። ማኅበራዊና ሀገራዊ ጉዳይ ካበላሹ በኋላ ‹‹በእኔ ሕይወት ማን ምን አገባው!›› ይላሉ፤ በአንተ(አንቺ) ሕይወት ማንም አያገባውም፤ በሚናገሩት ነገር ግን ያገባናል።

አንዳንዶቹ ደግሞ የታዋቂነትን ባሕሪ የሚያውቁት አይመስልም። የሆነ ነገር ሲያጋጥማቸው ታዋቂ ስለሆኑ ያጋጠማቸው መሆኑን አያጤኑትም።

ለምሳሌ፤ ብዙ ታዋቂ ሰዎች ላይ የታዘብኩት ነገር፤ በስማቸው የሚከፈት የማኅበራዊ ገጽ ሲያስተባብሉ ሲሳደቡ ነው። በስማቸው አካውንት የከፈቱ ሰዎችን በነውር ቃላት ይሳደባሉ። እርግጥ ነው በታዋቂ ሰው ስም ሐሰተኛ አካውንት መክፈት ነውር ነው፤ በራስ አለመተማመን ነው። ይሄ ነውር መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። የታዋቂዎቹ ችግር ግን ታዋቂ ስለሆኑ ያጋጠመ መሆኑን ልብ አለማለታቸው ነው። ይህ በሌላውም ዓለም ያለ ነው። የእነርሱ አለመሆኑን ወይም ማኅበራዊ ሚዲያ እንደማይጠቀሙ ማሳወቅ በቂ ሆኖ ሳለ፤ የእርግማን መዓት ሲያወርዱ ይሰማል። እደግመዋለሁ! የችግሩ አሳሳቢነት ጠፍቶኝ አይደለም፤ ዳሩ ግን ታዋቂ ሲሆኑ የሚያጋጥም ነውና ጨዋራቸውን መላጥ አይገባቸውም።

እዚህ ላይ ግን ተከታዮችም ልብ ማለት ያለባቸው በታዋቂ ሰው ስም የተከፈተ የማኅበራዊ ገጽ ሁሉ የዚያ ሰው ነው ወይም አስተማማኝ ነው ማለት አይደለም።

በአጠቃላይ ታዋቂነት ሲያጋጥም አዋቂነትና አስተዋይነት ሊጨመርበት ይገባል።

## ዓለም አቀፍ

# ከጃፓን የአቶሚክ ቦምብ ጥቃት የተረፉት የዘንድሮውን የኖቤል የሠላም ሽልማት አሸነፉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በዓለም ላይ በአሰቃቂነቱ የሚጠቀሰው አሜሪካ በጃፓን የፈጸመችው የአቶሚክ ቦምብ ጥቃት የተረፉ ሰዎችን ያቀፈው ኒሆን ሂዳንክዮ የተሰኘው ድርጅት የዘንድሮው የኖቤል የሠላም ሽልማት አሸናፊ ሆነ።

ከሂሮሺማ እና ናጋሳኪ የቦምብ ጥቃት የተረፉት ሰዎች ስብስብ የሆነው ይህ ድርጅት በዓለም ላይ ያለውን የኒውክሌር ጦር መሣሪያን ለማስወገድ እያደረገ ላለው ጥረት ከኖርዌይ የኖቤል ኮሚቴ ሽልማት ዕውቅና ተሰጥቶታል።

“ድርጅቱ በዓለም ላይ ፀረ-ኒውክሌር እንቅስቃሴ እንዲኖር ትልቅ አስተዋፅዖ አድርጓል” ሲሉ የኖቤል ኮሚቴ ሰብሳቢ ጆርገን ዋትን ፍሬድነስ ተናግረዋል።

በአቶሚክ ቦምብ የደረሰውን እልቂት ምስክርነት በመስጠት የኒውክሌር ጦር መሣሪያዎች እንደገና ጥቅም ላይ መዋል እንደሌለበት ከፍተኛ ሥራ መሥራታቸው ተዘክሯል።

በአውሮፓውያኑ 1956 የተመሠረተው ይህ ድርጅት በኒውክሌር ጦር መሣሪያ ምክንያት የደረሱ አሰቃቂ እልቂቶችን እና ስቃይ ምስክርነትን እንዲሰጡ ከጥቃት የተረፉትን ወደተለያዩ ሀገራት በመላክ ይሠራል።

ስብስቡ ሥራቸውን የጀመሩት የሂሮሺማ እና ናጋሳኪ ውድመት ከደረሰ ከአስር ዓመታት በኋላ ነው።

ቡድኑ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ለኖቤል ሽልማት ታጭቶ የነበረ ሲሆን በአውሮፓውያኑ 2005 ከኖቤል



ኮሚቴ ልዩ እውቅና እንደተሰጣቸው ድረ-ገጹ ያትታል።

በአውሮፓውያኑ 1945 አሜሪካ የዩራኒየም ቦምብ በሂሮሺማ ከተማ አዘነበች። ዓለም በአሰቃቂነቱ የሚያወሳው የጃፓኖቹ ሂሮሺማና ናጋሳኪ ከተሞች ላይ የአሜሪካ የአውቶሚክ ቦምቦች ዘንበውበታል፣ የሰው ልጅ እንደ ቅጠል ረግፈውበታል።

በእነዚህ የቦምብ ጥቃቶች ምን ያህል ሰዎች እንዳለቁ ትክክለኛ ቁጥር ባይኖርም ከሂሮሺማ 350 ሺህ ሕዝብ ውስጥ 140 ሺዎቹ ሞተዋል። በናጋሳኪም እንዲሁ 74 ሺዎች ተፈጅተዋል።

በአውቶሚክ ቦምቡ ጥቃቱ ምክንያት ጃፓን በ1937 እጅ ሰጥታለች። እንዲሁም የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ክፍል የሆነውና በእስያ የነበረውን ጦርነት ማብቂያን ያበሰረ ነው ቢሉም አንዳንዶች በዚህ ሃሳብ አይስማሙም።

የቡድኑ አንደኛው ኃላፊ የሆኑት ቶሺዩኩ ሚማኪ ከሽልማቱ በኋላ ለጋዜጠኞች “በሕልሜም ቢሆን ይህንን አላስብም ነበር” ሲሉ መናገራቸውን አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ የዜና ወኪል ዘግቧል።

ባለፈው ዓመት በእስር ላይ የምትገኘው ኢራናዊቷ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ናርጅስ ሞሃማዲ የኖቤል የሠላም ሽልማት አሸናፊ ነበረች።

ናርጅስ የሽልማቱ አሸናፊ የሆነችው በኢራን በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጭቆና በመታገል እንዲሁም ሁሉም ዜጎች ሰብዓዊ መብቶቻቸው ተከብሮ እና ነፃነት የሚያገኙበትን ዓለም ለመፍጠር ባደረገችውም ትግል እንደሆነም ኮሚቴው አስታውቆ ነበር።

ከሁለት ዓመት በፊት የኖቤል የሠላም ሽልማት አሸናፊ የነበሩት ሜሞሪያል የተባለ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ቡድን፣ ዩክሬናዊ የሰብዓዊ ተሟጋች ማዕከል ‘ሴንተር ፎር ሊበርቲስ ‘ እንዲሁም በእስር ላይ የሚገኘው የመብት ተሟጋች አሌስ ቢያሊያትስኪ ነበሩ።

ሩስያ በዩክሬን ላይ ወረራ ፈጽማ ጦርነቱ በተፋፋመበት ወቅት ሠላም እንዲሰፍን ላደረጉት ትግልም እውቅና ተሰጥቷቸዋል።

የኖቤል የሠላም ሽልማት ከተቋቋመበት ከአውሮፓውያኑ 1901 ጀምሮ 110 ግለሰቦች እና 30 ድርጅቶች አሸናፊ ሆነዋል።

ከዚህ ቀደም ፓኪስታናዊቷ የትምህርት ተሟጋች ማላላ ዩሳፉዚ እንዲሁም የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሽልማቱ አሸናፊ ሆነዋል።

# ደስተኛ ለመሆን የሚያግዙ ልማዶች

**አስናቀ ፀጋዬ**



በዓለም አቀፍ ደረጃ በዓመት 700 ሺህ ሰዎች ራሳቸውን እንዲሚያጠፉ ድብርት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ሀዘን እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ቀዳሚ ምክንያቶች እንደሆኑ ይነገራል። በዓለም አቀፍ ደረጃ 40 በመቶ የሚሆኑ በአዋቂ እድሜ ላይ የሚገኙ ሰዎች ደስተኛ እንዳልሆኑም መረጃዎች ያሳያሉ። በርካታ ውጥረት እና ውጥንቅጥ በሞላባት ዓለም ውስጥ ሰዎች መሰረታዊ የኑሮ ጥያቄን ለመሙላት ከሚያደርጉት ግብግብ ባለፈ ደስተኛነትን ፍለጋ በርካታ ጊዜያቸውን ያጠፋሉ።

ደስተኛ የመሆን ሚስጥር በተለያዩ ምሁራን እና ፈላስፎች የተለያየ ትርጓሜ ቢሰጠውም ሰዎች እንደሚገኙበት ኢኮኖሚያዊ፣ የጤና እና ማህበራዊ ሁኔታ ደስተኝነትን የሚለኩበት መንገድ ይለያያል። በድብርት፣ ተስፋ በመቁረጥ፣ የሕይወት ትርጉም በማጣት፣ በጭንቀት፣ ሀዘን እና በኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሰበብ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዓመት 700 ሺህ ሰዎች እራሳቸውን እንደሚያጠፉም ነው የሚገለፀው። በተለያየ ጊዜ የተደረጉ ጥናቶች ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ 40 በመቶ በአዋቂ እድሜ ላይ የሚገኙ ሰዎች በሕይወታቸው ደስተኛ አለመሆናቸውን እንደተናገሩ ይጠቁማሉ።

በእርግጥም ደስታ ለጥቂቶች ብቻ የሚገለጥ ሚስጥር አይደለም። ደስተኛ መሆን እንፈልጋለን ግን አልቻልንም የሚሉ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃል? ነገር ግን ለመደሰት ከየት ልጀምር? የሚለውን ጥያቄ በሚከተለው መልክ በጥቂቱ መቃኘቱ ግድ ይልሃል።

1. ደስተኛ ለመሆን ቀጠሮ አትያዝ፡- ሕይወቴ ሲቀየር፣ ስኬታማ ስሆን፣ ያሰብኩትን ሳሳካ እደሰታለው እያልክ የምታስብ ከሆነ ደስታህ መቼ እንደሚመጣ አታውቀውም። መቼ እንደምትመጣ የማታቃትን ወዳጅህን እንደመጠበቅ ሰቀቀን ይሆንብሃል። ብዙዎቻችን ጤናማ፣ ደስተኛ እና ውጤታማ መሆንን እንመኛለን። ለዚህም የተዋበ መልክ እና ቁመና፣ የተትረፈረፈ ገንዘብ፣ ቆንጆ መኪና አልያም ቪላ ቤት እንዲኖረን እንሻለን። ይሁን እንጂ እነዚህም ሆኑ ሌሎች የተመኘናቸው ነገሮች ሁሉ ቢሟሉም የፈለግነውን ደስታ እና ጤና ላናገኝና ስኬታማ የሆንን መስሎ ላይሰማን ይችላል።

2. ደስተኛ ሰው ከዛሬ ጋር በቅጡ የተግባባ ሰው ነው።

3. ደስተኛ ለመሆን፤ የግድ ሃብታም፤ ስኬታማ እና ታዋቂ መሆን አይጠበቅብንም።

4. እውነተኛና ደስተኛ ሰው በሌለው ነገር እየተጨነቀ ዛሬውን የሚያባክን ሳይሆን፤ ባለው ነገር እየተደሰተ የሌለውን በተስፋ የሚጠብቅ እጅግ ብልህ ነው።

5. ለማመን ቢከብደም ሰው በምንም አይነት የኑሮ ሁኔታ ላይ ቢሆንም ደስተኛ መሆንን ምርጫው ካደረገ፤ በእርግጠኝነት ደስተኛ መሆን ይችላል።

6. ኑሮዋችን እንደ እይታችን ይወሰናል፤ የጎደለንን እያየን ማማረር፤ ወይም ያለንን እያየን ማመስገን። ሁለቱም ምርጫዎች በኑሮ ገበታችን በየቀኑ የሚቀርቡ ናቸው፤ አስተሳሰባችን ምርጫችንን ይወስነዋል።

7. እርግጥ ነው ደስተኛነት፤ በየቀኑ መፍለቅለቅ አይደለም፤ ምክንያቱም ሕይወት በውጣ ውረዶች የተሞላች ስለሆነች።

8. ደስተኛ ለመሆን ሁሌም ምርጫችን ከሆነ ግን፡- ቢያንስ ወጣውረዱን ለመጋፋጥ አንሸበርም፣ ቀናችን በሃዘን እና በማማረር አይባክንም፣ ከሌሎችን ሰዎች ጋር ስንሆን ደስ የሚል መንፈስን እናንጸባርቃለን።

9. ደስታ ተላላፊ ነው፣ ሳቅ ልክ እንደ ሰደድ እሳት ይቀጣጠላል፣ ደስተኛ ስትሆን በመንገድህ የምታገኛቸው ሰዎች ላይ ሁሉ ትልቅ ተጽዕኖ እደምታመጣ እመን።

10. ደስታ የምኞት ውጤት፣ የማሳደድ ትርፍም አይደለም። ደስታን ተመኝቶ ያገኘ፣ አሳድዶ የያዘ የለም።

11. ደስተኛ ለመሆን አትኩሮትህን በሌለህ ነገር ላይ ሳይሆን ባለህ ነገር ላይ አድርገው። ደስተኛ ለመሆን ሁሉም ነገር ሊኖርህ አይገባም። በደንብ ካስተዋልከው አሁን ያለህ ነገር ደስተኛ ለመሆን በቂ ነው። ምክንያቱም አንተ ያለህን የሚመኙ ምስኪኖች ብዙ ናቸውና።

መቼም ደስተኛ መሆን የማይመኝ ሰው ይኖራል? በፍፁም! ታዲያ ለምን አብዛኛዎቻችን ደስተኛ መሆን ያቅተናል? ለምንስ ደስተኛ አለመሆናችንን ከማመን ይልቅ ከራሳችን ለመሸሽ እንሞክራለን? በድብልቅልቁ ውስጥ እየተሹለከለክን፤ ሕሊናችን እንዳይጠይቀን አይምሮዋችንን በምኑም በምኑም ጠምደን እስከመቼ እንዘልቃለን? ደስተኛ መሆን ከበሮ በሰው እጅ ሲያዩት ያምር ሲይዙት ያደናግር ይሉት አይነት ነገር ለምን ሆነብን? መፅሃፍቱ፣ ሃይማኖቱ፣ ሳይንሱ፣ ፍልስፍናው ሁሉ ደስተኛ የመሆንን ቀመር እጅግ አቅልለው እያሳዩን ስለምን በተግባር ስንሞክረው ከበደን?

ታላቁ ፈላስፋ ሶቅራጠስ የደስተኛነን ሚስጥር እንዲህ ይገልፀዋል "ደስተኛ ለመሆን ቁልፉ አትኩሮታችንን ከስጋችን ላይ አንስተን ወደ ነፍሳችን ማድረጉ ነው" ይላል። ደስታን ከአይምሮ ውጪ የሚፈልጋት ሰው በፍፁም ሊያገኛት አይችልም። ለዚህ ደግሞ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ሃብት ሳየኖራቸው፤ ጤንነት እየጎደላቸው ደስተኛ የሆኑ ሰዎች አይታቹህ አታውቁም?

ውጫዊ ገጽታቸው ሳያምር፤ አለማዊ ፍላጎታቸው ሳይሟላ ደስተኛ የሆኑ ሰዎች አይታቹህ አታውቁም? ቤታቸው ባዶ ሆኖ፤ ዘመድ ጓደኛ እንደልብ ሳይኖራቸው ደስተኛ የሆኑ ሰዎች አይታቹህ አታውቁም?

ይህን ስናይ ደስታ በፍፁም ከቁሳዊ እና አካላዊ ነገሮች ጋር ግንኙነት እንደሌላት እናያለን።

የሰው ልጅ ሁሉ ነገር ቢኖረው አይምሮው ግን ደስታን ከተራበ ምን ዋጋ አለው?

ለምን ተፈጥሮ ያደለችንን የደስተኛነት ፀጋ በገዛ ፈቃዳችን ሳንጠቀምበት ሕይወታችን ያልፋል?

ለማመን ትንሽ ቢከብድም እንኳን እውነቱ ግን ይህ ነው........በማንኛውም አይነት የሕይወት አጋጣሚ ውስጥ ብንሆንም እንኳን ደስተኛ መሆን እንችላለን።

እስቲ አስቡት የጎደለን ነገር ቢኖር እንኳን ያለን

እንደሚበዛ ካሰብን፤ ለሌሎች ሰዎች መልካም ነገር ማድረግን ከለመድን፤

ተስፋ ከልባችን ካልጠፋ፤ ትላንትን ከዛሬ፤ ዛሬን ከነገ መለየት ከቻልን፤

በጠዋት ከምትፈካው ጀንበር ጋር አብረን ከሳቅን፤ ማታ ከምትወጣው ጨረቃ ጋር አብረን ከደመቅን፤ ከተፈጥሮ ምት ጋር አብረን ከዘፈንን፤ ከሁሉም በላይ ደስታን ከሰው ምንጭ ሳይሆን ከራሳችን የሕይወት ምንጭ ለመቅዳት ከሞከርን .......እንዴት ደስተኛ አንሆንም?

ደስታ እርስዎ ዘንድ እስኪመጣ መጠበቁን ይተውትና ደስታን እርስዎ እራስዎ መፈለግ ይጀምሩ። ደስታ በምትሃት ወይም በአንዳች ነገር የሚመጣ አይደለም። እንዲያውም ድንገት እርስዎ ላይ የሚከሰት ክስተትም አይደለም። እርስዎ እራስዎ የሚያዳብሩት/የሚያሳድጉት ባህሪ ነው እንጂ። እንዴት ደስተኛ መሆን እንደሚችሉ /ምን ደስተኛ እንደሚያደርግዎ መፈለግ ይጀምሩ። ስለዚህ በተቻለ መጠን ደስተኛ ለመሆን እራስን በማለማመድ ደስታን ማግኘት ይቻላል ማለት ነው።

10 በመቶ ብቻ በሚሆኑ በሰዎች መካከል ያለው የደስተኝነት አገላለፅ ልዩነት በሁነቶች መለያየት ሊገለፅ ይችላል። በተረፈ በአብዛኛው ሰዎች ላይ ደስተኝነትን የሚወስኑት የሰዎች ስብዕና ሲሆኑ በተለይ ሊለወጡ የሚችሉ አስተሳሰብና ባህሪይ ናቸው። ምንም እንኳን እርስዎም ብዙ ሰዎች እንደሚያስቡት ደስተኛ መሆን የሚቻለው ሀብታም ሆነው ሲወለዱ፣ ቆንጆ ሲኮን አሊያም ጭንቀት የሌለበት ኑሮ/ሕይወት ሲኖሩ ነው የሚል አስተሳሰብ ከሆነ ያልዎት እውነቱ እንደሱ አይደለም። ይልቁንስ ሀብት ያላቸው ሰዎች፣ ቁንጅና ያላቸው ወይም ጭንቀት የሌለው ኑሮ የሚኖሩ ሰዎች በአቬሬጅ ሲታይ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ካልታደሉ ሰዎች ጋር ሲዋዳደሩ ምንም የተለየ/የበለጠ ደስታ የሌላቸው መሆኑ ነው።

ስለሆነም ደስተኛ ለመሆን ሁሌም መለማመድ፣ መለማመድ አሁንም መለማመድ ያስፈልጋል። ደስተኛ ለመሆን እየፈለጉ ከሆነ የደስታዎ መጠን የሚወሰነው በምርጫዎ፣ ሀሳብዎና በተግባርዎ ላይ ነው። ግባችን ላይ ስንደርስ ወይም የተመኘነውን ነገር ስናገኝ ደስተኛ እንደምንሆን የተረጋገጠ ቢሆንም እንዲህ ዓይነቱ ደስታ ቀስ በቀስ እየከሰመ ሊሄድ ይችላል።

ዘላቂ ደስታ የሚኖረን ስኬት ወይም አንድ ዓይነት ንብረት ስላገኘን አይደለም። ከዚህ ይልቅ አንድ ሰው ጤናማ መሆኑ በተለያዩ ነገሮች ላይ የተመካ እንደሆነ ሁሉ እውነተኛ ደስታም የተለያዩ ነገሮች ድምር ውጤት ነው።

ሁላችንም የተለያየን ሰዎች ነን። አንተን የሚያስደስትህ ነገር ሌላውን ሰው ላያስደስተው ይችላል። በተጨማሪም ዕድሜያችን እየጨመረ ሲሄድ ፍላጎታችንም ይለወጣል። ምንም እንኳ ቀላል ባይሆንም የደስተኝነትዎን መጠን በተወሰነ መልኩ ከፍ ማድረግ ይችላሉ። ይህ ለማድረግ የሚከተሉት መንገዶች ሊከተሉ ይችላሉ።

ደስተኛ የመሆን ሚስጥር እንደ ሰው እና አካባቢው ቢለያይም የስነልቦና ሀኪሞች ማንኛውም ሰው በቀላሉ ተግብሯቸው ደስተኛ ሊሆንባቸው የሚችሉ በሚል የዘረዘሯቸውን አምስት ልማዶች ግን አሉ።

### 1. ለሰዎች ደግ መሆን ወይም በጎ ማድረግ

ሰዎች ካላቸው ነገር ላይ ቀንሰው ለሰዎች በጎ ነገርን ማድረግ ደስታ ከሚፈጥሩ የመኖር ትርጉም ጥያቄን ከሚመልሱ ልማዶች መካከል አንዱ ነው ተብሏል። ከመልካምነት በመነጨ ስሜት ለሌሎች ሰዎች የሚደረግ መልካምነት ሰዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ አመስጋኝ እንዲሆኑ፣ በራሳቸው እንዲተማመኑ እና ስለራሳቸው መልካም ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል።

በዚህ ምግባር ምክንያት በማህበረሰብ ውስጥ እና በሚገኙበት አካባቢ ሰዎች የሚሰጧቸው አክብሮት እና ተቀባይነት ስለሚጨምር በሰዎች ዘንድ መወደዳቸው ደስታን ይፈጥራል ተብሏል። ትንሽ የሚባል የደግነት ምግባር የለም የሚሉት የስነልቦና ተመራማሪዎቹ ሰዎች አካባቢያቸውን በደንብ ቢቃኙ መልካም ለመሆን ገንዘብ ማውጣት የማይጠይቁ ምግባሮችን ያገኛሉ ብለዋል።

### 2ኛ. አመስጋኝነት

ምስጋና በሀይማኖታዊው ትእዛዝነትም በጎ ምግባር ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ስለተሰጣቸው ነገር የሚያመሰግኑ ሰዎች ስለጎደላቸው ስለማይጨነቁ እንዲሁም በቁሳቁሳዊ ጉዳዮች ራሳቸውን ለማነጻጸር ጊዜ ስለማይኖራቸው ደስተኞች መሆን እንደሚችሉ ተገልጿል። ሰዎች ወደ መኝታቸው ከማቅናታቸው በፊት አልያም ከቅርብ ሰዎቻቸው ጋር ሲወያዩ አመስጋኝ ስለሆኑባቸው፣ በሕይወታቸው ስለተሰጧቸው ነገሮች ማመስገንን ልማድ ማድረግ አለባቸው ተብሏል።

ለምሳሌ በነጻነት መንቀሳቀሳቸው፣ በሕመም አልጋ ላይ ባለመዋላቸው፣ ሙሉ አካል እና ሙሉ ጤና ስላላቸው እንዲሁም ለሌሎች ውድ የሆኑ እነርሱ ጋር ግን ያሉ ነገሮችን በመቁጠር አመስጋኝ እንዲሆኑ ይመከራል።

### 3ኛ. መልካም ግንኙነትን ከሰዎች ጋር መመስረት

ማህበራዊ እንስሳ እንደሆነ የሚነገርለት የሰው ልጅ በምድር ላይ ብቸኛ ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም። ከቤተሰብ፣ ከልጆች፣ ከጎረቤት፣ ከጓደኛ በአካባቢ ከሚገኙ ሰዎች ጋር ግንኙነትን የተቃና ማድረግ የደስተኛነት ሚስጥር ከሆኑ ልማዶች መካከል አንዱ ተደርጎ ተጠቅሷል።

ሰዎች ከሌሎች ጋር የሚኖራቸው መስተጋብር አካባቢያቸው ከጭንቀት እና ድብርት እንዲሁም ያለመፈለግ ስሜትን ስለሚያጠፋ ለመኖር ተጨማሪ ምክንያትን የሚያክል ነው ሲሉ የስነ ልቦና ተመራማሪዎቹ ተናግረዋል። በችግር እና ደስታ ጊዜ በአቅራቢያ የሚገኝ ሰው መኖር እንዲሁም በወዳጆች መከበብ ሰዎች ደህንነት እና በራስ መተማመን እንዲሰማቸው ያደርጋል።

### 4ኛ. መልካም ዜናዎችን በተገቢው መጠን ማጣጣም

በርካታ የጭንቀት እና የሀዘን ዜናዎች በሞሏት ዓለም ውስጥ መልካም ዜናዎች ከብዙ ጊዜ አንድ ጊዜ የሚገኙ በመሆናቸው በልካቸው መከበር ይገባቸዋል። በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ መልካም አጋጣሚዎችን እና የስኬት ወሬዎችን ከቅርብ ሰዎች ጋር በመሰባሰብ ማክበር ሕይወት አንድ አይነት እና አሰልቺ እንዳትሆን ከማገዙም በላይ በተስፋ የተሞላ ነገ እንዲኖር ያደርጋል። በዚህም በስራ እና በሕይወት ስላጋጠሙን ስኬቶች ደስታን በተገቢው መንገድ መግለጽ ይመከራል።

### 5ኛ. ከሰዎች አለመጠበቅ

ለሰዎች ስኬት እና ውድቀት ቀዳሚ ኃላፊነቱን የሚወስዱት ራሳቸው ናቸው። መልካም ወዳጅነትን መመስረት ለደስተኛነት ወሳኝ ቢሆንም ደስተኛነት በሰዎች ላይ መንጠልጠል አይኖርበትም። ለሰዎች በሰጠናቸው መጠን ምላሽ የምንጠብቅ ከሆነ የታሰበው ሳይሆን ሲቀር ደስተኛ አለመሆንን እና ስለራስ መጥፎ ስሜት እንዲሰማ በማድረግ ከሰዎች መራቅን እና ብቸኝነትን ያስከትላል። በመሆኑም ደስተኛ ለመሆን የሚፈልጉ ሰዎች የደስተኝነት ምክንያታቸው በሰዎች ላይ መመርኮዝ የለበትም ብለዋል የስነ ልቦና ሀኪሞቹ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሠላም የሁሌም ቀዳሚ ምርጫ!

ለአንድ ሀገር ወሳኝ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል ዋነኛው የሠላም ጉዳይ መሆኑ ለማንም አጠያያቂ አይደለም። ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ለማሳካት ያለ ሠላም የሚታሰብ አይሆንም። እንደ ሀገርም ሀገር ሆኖ ለመቀጠል ሠላም የግድ ይላል። ሠላም የሁሉም ነገር መሠረት ነውና። ይሁን እንጂ የሠላም አስፈላጊነትን በቅጡ ያልተገነዘበ "ሠላም"ን እንደ ቃላቱ ፊደላት ቁጥር አሳንሶ ያያል።

የሰው ልጅ ወልዶ ለመሳም፣ አስተምሮ ለማስመረቅ፣ ድሮ ለመኳል፤ ሀብት ንብረት ለማፍራት፣ ወጥቶ ለመግባት፣ ነግዶ ለማትረፍ ሠላም ያስፈልገዋል። ሠላም ከሌለ እንኳንስ ፍላጎትን ማሳካት ቀርቶ ሊጎርሰው በእጁ የጠቀለለውን ምግብ ወደ አፉ ማድረግ ይሳነዋል። ለዚህም ነው በሀገር ላይ የተሟላ ሠላም መኖር የግድ የሚሆነው።

በአሁኑ ወቅት በመላው ሀገራችን የተሟላ ሠላም አለ ብለ ደፍሮ ለመናገር አይቻልም። በተለያየ አካባቢ የሚታይ የሠላም መደፍረስ ሀገሪቷንም ሆነ ዜጎቿን መስዋዕትነት እያስከፈለ ይገኛል። የሰው ሕይወት መጥፋት፣ የአካል መጉደል፣ የንብረት መውደም የመሳሰሉት ችግሮች በተለይ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች አንዳንድ አካባቢዎች ሲሰሙና ሲታዩ ቆይተዋል።

በዚህም ምክንያት ዜጎች ሕይወታቸውን እያጡ ነው፣ ሀብት ንብረታቸው እየወደመ እና ከቀያቸው እየተፈናቀሉ ይገኛሉ። አርሶ አደሩ የዕለት ተግባሩን ማከናወን ተስኖታል፤ ደብተር ይዞ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄደው ተማሪ ቁጥር ቀደም ሲል በሚታወቀው ልክ አይደለም። በተለይ በአማራ ክልል የሚታየው የሠላም መደፍረስ የዜጎችን ተስፋ እያጨለመ እንጂ እያለመለመ አይደለም።

የአማራ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ለ2017 በጀት ዓመት በክልሉ ከሰባት ሚሊዮን በላይ ተማሪ ለመመዝገብ አቅዶ ነበር። ነገር ግን ለመማር ምዝገባውን ያደረጉት አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ብቻ ናቸው። ይሄ የሚያሳየው ተማሪዎች እያሉ ፤ የትምህርት ፍላጎትም እያላቸው በክልሉ ባለው የሠላም እጦት ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው መራቃቸውን ነው።

በየትኛው ዓለም የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ልዩነት ይኖራል። በልዩነቱ ዙሪያ አለመግባባት ይፈጠራል። ይሄን አለመግባባት በሠላማዊ ትግል ለመፍታት ጥረት ከማድረግ ይልቅ ወደ ጦርነት ማምረት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ከአዋጪነቱ ይልቅ አክሳሪነቱ ያይላል። ጦርነት ምን ያህል በሀገር ላይ የከፋ ጉዳት እንደሚያስከትል ከትናንቱ የሀገራችን የሰሜኑ ጦርነት አይተነዋል።

ምን ያህል ዜጎቻችን በሞት እንደተለዩን ምን ያህሉ አካል ጉዳተኛ እንደሆኑ የሠላም ማጣት ምን ያክል ከባድ መሆኑን በተጨባጭ አጣጥመነዋል። የክልሉ ኢኮኖሚ ወደ ዕድገት ሳይሆን ወደ ቁልቁለት መውረዱን፣ መሠረተ ልማቱ ውድመት ምን ያህል ኢኮኖሚውን እንዳጎበጠው አስተውለነዋል። ከዚህ መማር ይገባል።

አሁንም በየትኛው አካባቢ የሚታየውና የሚሰማው ደም አፋሳሽ ግጭት ሊቆሙ ይገባል። ችግሮች በድርድር እና በውይይት መፈታት አለባቸው። የሠለጠነ ዲሞክራሲ መኖር የሚገለጠው ስለዲሞክራሲ በማውራት ብቻ ሳይሆን የተገኘውን ዲሞክራሲ በአግባቡ በመጠቀም ነው።

በመሆኑም በአማራ እና ኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኞች እየተገበሩት ያለው የትጥቅ ትግል ሀገር ከማፍረስ የዘለለ ጥቅም እንደሌለው ተገንዝበው ለሠላም እጁን ከዘረጋው መንግሥት ጋር በሠላማዊ መንገድ መነጋገር ይገባቸዋል። ስለ ሀገርና ሕዝብ ሲባል ችግሮችን በውይይት መፍታት ያስፈልጋል። ዛሬ በየትኛውም አቅጣጫ እየረገፈ ያለው የራሳችን ዜጋ ነው።

በየትኛም አቅጣጫ እየወደመ ያለው የራሳችን ሀብት ነው። ለጦርነቱ የሚውለው መሣሪያ ግዢ የሚፈጸመው በሀገሪቱ የውጪ ምንዛሪ ሀብት ነው። በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ችግሩ የአንድ ሀገር የውስጥ ጉዳይ በመሆኑ ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል። ከሚሰሙና ከሚታዩ የሠላም መደፍረሶች ወጥቶ ወደ ሠላም መንገድ መግባት ይገባል።

የጦርነትን አዋጭነት ሳይሆን አውዳሚነትን ከሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከነበረው ጦርነት አይተነዋል። ከጦርነቱ ሀገርን ማውደም፣ ዜጎችን ማሰቃየት ካልሆነ በስተቀር አንድም ያተረፍነው ነገር የለም። ስለዚህ አሁንም ሀገር ከወደመ በኋላ ሳይሆን ዛሬውኑ ወደ ሠላም መንገድ መምጣት ያስፈልጋል።

የሠላም አማራጭን አማራጭ ማድረግ አንድም የሥልጣኔ መገለጫ ነው፤ ሌላው የተነሱበትን ዓላማ ማሳካት ጭምር በመሆኑ ጽንፈኞች የሠላምን መንገድ ዋና አማራጭ ሊያደርጉ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት ከኃይል አማራጭ ይልቅ ለሠላማዊ መንገዶች ትኩረት ሊሰጡ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የጓሮ አትክልትን እንደ አንድ አማራጭ

ራስወርቅ ሙሉጌታ

ተፈጥሮና የሰው ልጅ አይነጣጠሉም፡፡ የሰው ልጅ ለተፈጥሮ በሚያደርገው እንክብካቤ መጠን በተፈጥሮ ይካሳል፡፡ ኑሮው ምቹ ይሆናል፡፡ ተፈጥሮን ባራቆተ መጠንም ሕይወቱ የተራቆተ ይሆናል፡፡ ተፈጥሮ በሰው ልጅ ለደረሰባት በደል የተናገረችው ነገር ባይኖርም የሰው ልጅ ግን ከተፈጥሮ በተግባር እየተሰጠው ባለው ምላሽ የደረሰበት ችግር የሕልውና ስጋት ይዞ ከመጣ ሰንብቷል።

ከእነዚህም ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥን ተከትሎ የሚከሰቱ የተፈጥሯዊ አደጋዎች /ጎርፍ ድርቅ ወዘተ/ የጤና እክሎች ተጠቃሽ ናቸው። ሀገራችን ኢትዮጵያም የችግሩ ተጠቂ ከሆኑ ሕዝቦች አንዷ ናት። በተለይም በተደጋጋሚ በሚከሰተው ድርቅ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ለረሃብ ዳርጓል፡፡

ይህ የተፈጥሮ አካባቢን በአግባቡ ተንከባክቦ ካለመጠበቅ የሚነሳው ችግር፤ በምግብ እህል እራሳችንን እንዳንችል በማድረግ በምግብ እህል ጠባቂ አድርጎናል። በቀላሉ ከጓሯችን ልናመርታቸው የምንችላቸውን ምግቦች ጭምር ከቀደሙት ዘመናት በተሻለ መንገድ ለማስቀጠል ሳንችል ቀርተናል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ለቅጠላ ቅጠልና ፍራፍሬ ምግቦች ያለን አመለካከት ዛሬ ላይ እንዳለው የዳበረ አልነበረም። እነዚህን ምግቦች የሚመገበው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ብቻ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በእርግጥ ዛሬም ቢሆን ለአንድ ኪሎ ሥጋና ዓሣ አልያም ወተት የሚከፈለው የገንዘብ መጠን ከአንድ ኪሎ ቆስጣና ጎመን ወይንም ሰላጣ እንደሚበልጥ መካድ አይቻልም።

የዛሬው የጽሑፌ መነሻ ሀሳብ በራሳችን አቅም ልንሠራው የምንችለውን እና የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ያለውን የጓሮ አትክልት ነው፡፡ የጓሮ አትክልት በትንሽ ቦታ ሊለማ የሚችል እየጨመረ ለመጣው የከተማ ነዋሪ የምግብ አቅርቦት ትልቅ አቅም የሚሆን ነው፡፡

ይህም ሆኖ ግን ከመጣንበት ሥራ ባሕል አኳያ ይህን ማድረግ ሳንችል ቀርተናል፡፡ ከተሞችን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች ውሃ እያለ ባዶ መሬት እያለ እንደ ሰላጣ፣ ቆስጣ፣ ጎመንና ቲማቲም ያሉ ምርቶችን በውድ ዋጋ ስንገዛ እንታያለን።

በየጓሯችን በቀላሉ ልናለማችን የምንችላቸው አትክልት እና ፍራፍሬዎች ልብ ብለን ካስተዋልነው ጠቀሜታቸው ዘርፈ ብዙ ነው። እነዚህን ምርቶች ከግቢያችን ልናገኛቸው ከመቻላችን ባለፈ ወጪ ይቀንሱልናል፤ ለጤናችንም የሚኖራቸው ፋይዳ ከፍያለ እንደሆነም ይታመናል።

ዛሬ በየአትክልት መደብሮችና በየጉሊቱ የሚሸጡልን አትክልት እና ፍራፍሬዎች በተሻለ መንገድ እና ቴክኖሎጂ ማምረት ወደሚያስችል ሥርዓት ብንሻገር፤ በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል ለምናደርገው ሀገራዊ ጥረት ሆነ የተመጣጣነ የምግብ አቅርቦትን ለመፍጠር ወሳኝ አቅም ሊሆኑ እንደሚችል ማሰብ የሚከብድ አይደለም።

በእርግጥ እራሱ የጓሮ አትክልት የሚለውን ስያሜ በሚፈጠርብን ስሜት የምንለያይ ይመስለኛል። የጓሮ አትክልት ልማት አነሰም በዛ የግብርና ሙያ የሚጠይቅ ነው። ለእኔ ዘመን ትውልድ ደግሞ የጓሮ አትክልት ልማት በየግቢያችን የምንከውነው ብቻ ሳይሆን አንድ የትምህርት አይነት ሆኖ የሠለጠንበትም ነው።

በዛ ዘመን የነበሩት ትምህርት ቤቶች የቦታ ችግር ስለሌለባቸው፤ መምህራኖች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው የእርሻ ትምህርት በመስክ ላይ የአትክልት መደብ/የእርሻ ቦታ ተዘጋጅቶ በተግባር ይሰጡ ነበር። በነገራችን ላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ «ሀይስኩል» ስንማርም ዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል የእርሻ ትምህርት ነበር።

አስረኛ ክፍል የእርሻ መምህራችን በተደጋጋሚ «ውሃ፤ አፈር፤ አየር ካለ ሕይወት አለ» በሚል ይነግሩን ነበር። ይሄ አባባል ዛሬም የሚሠራ ነው። ባጭሩ በያለንበት ቦታ በጣም በትንንሽ ቦታዎች ለይ በቀላል ወጪ የጓሮ አትክልት ማልማት እንችላለን። አንዳንድ ዕፅዋት ወዳድ ሰዎች በተጣበበ ግቢያቸው ውስጥ የተከሏቸውን ዕፅዋት ከሥራ መልስ ብቻ እየተንከባከቡ ብዙ ሲያተርፉ አይተናል።

ለዚህ ጉዳይ መንግሥትም የተለየ ትኩረት መስጠት ከጀመረ ውሎ ማደሩን ሁላችንም የምናውቀው ነው። ለዚህም የሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብር ማንሳት ይቻላል። የሌማት ትሩፋት ዓላማው የምግብ ሉዓላዊነትን ማረጋገጥና ክብርን ማስጠበቅ ነው ። በተለይም ሥጋ፣ እንቁላል፣ ማር እና ወተት ትርፍ ምርት ሆነው እንዲገኙ ማልማትና መጠቀምን መሠረት ያደረገ ነው። መርሐ-ግብሩ የኢትዮጵያን ደካማ የአምራችነት ታሪክ በመቀየር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና የኢኮኖሚ እድገትን ማፋጠንን መዳረሻው ያደረገ ነው።

በሌማት ትሩፋት ገበታን በተመጣጠነ ምግብ መሙላት ከተቻለ የእናቶችንና የሕጻናትን ፍላጎት በማሟላት በአካል የዳበረና በአዕምሮ የበለፀገ ትውልድ መገንባት ይቻላል የሚለውም ቁልፍ ዓላማው ነው። በተቃራኒው ያልተመጣጠነ አመጋገብ ጤና ላይ ከሚፈጥረው ችግር ባለፈ በሰዎች መካከል ያለውን የአኗኗር ደረጃ በማስፋት፣ ማኅበራዊ ቀውስን በመፍጠርና ኢኮኖሚውን በመጉዳት ምርትና ምርታማነትን ወደ ኋላ የሚጎትት ነው።

ይህ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ከድህነት ለመውጣት በከባድ ትግል ላይ የሚገኙ ሀገራትን የልማት ግስጋሴ በመግታት ቀድሞ ወደነበሩበት የድህነት አረንቋ እንዲመለሱ የሚዳርግ ነው። የሌማት ትሩፋት የኑሮ ውድነቱን በማስከንም ሆነ የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድም ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

መንግሥት እቅዱን ያስጀመረው በመንግሥት ደረጃ በትልቁ እንደ ሀገር ለመተግበር ነው። ማለትም እንደ ግለሰብ እነዚህን ነገሮች መሬት አውርዶ ለመተግበር የመኖሪያ አካባቢን ጨምሮ በሌሎች ነባራዊ ጉዳዮችም የሚወሰን ይሆናል። ለምሳሌ ንብ ማነብ፤ ከብት ማርባት በከተማ የአኗኗር ሁኔታ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

በአንጻሩ በትንንሽ ቦታዎች በቀላሉ ሊሠሩ የሚችሉ እንደ ቆስጣ፣ ሰላጣ ቃሪያና ጎመን የመሳሰሉትን ማልማት ግን ጥቂት የማይባሉ ሰዎች እጃቸው ላይ ያሉ አቅሞችን በመጠቀም ሊተገብሩት የሚችሉት እንደሆነ ይሰማኛል።

በአሁኑ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከልማት ጋር በተያያዘ ብዙ ለውጦች እየተከናወኑባት እንደሆነ ግልጽ ነው። ነገር ግን በአምስቱም በሮቿ በቅርብ የሚገኙ ከተሞች በዚህ ረገድ ብዙ ሊሠሩበት የሚያስችላቸው አቅም እንዳለ እገነዘባለሁ። አነሰም በዛ በየአካባቢው ውሃ አለ። ከየግለሰብ ጓሮ ጀምሮ በየሰፈሩ ጦም ውለው ጦም የሚያድሩ ብዙ ክፍት ቦታዎችም አሉ።

ምን አልባትም በየቤቱ አልያም በየጎረቤቱ ደግሞ አንድም ሆነ ሁለት ሥራ ፈት ማለቴ ሥራ አጥ አምራች ኃይል በየጓሮው አትክልት ሊያለማ የሚችል ይኖራል። ይህም በተለይ ልጆችን በቤት ውስጥ ሲንከባከቡ ለሚውሉ እናቶች የጎላ ፋይዳ ይኖረዋል።

ይህን በጥቂቱ ጠቆም ለማድረግ ያህል አነሳሁ እንጂ ሁኔታዎች የተመቻቹለትና ትንሽ የበረታ ካለ በተያያዥነት ሊሠሩ የሚችሉ ብዙ ሥራዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይሰማኛል። ለምሳሌ ከጓሮ አትክልት ልማት ጋር በግ ማደለብ፤ ዶሮ ማርባትና የመሳሰሉት። እነዚህ ነገሮች ቋሚ መተዳደሪያ መሆን የሚችሉ ናቸው።

ቀለል አድርገው ከታዩም ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ወጪዎችን ለምሳሌ ለልጆች ልብስና የትምህርት ቤት ቁሳቁስ የዓመት በዓል ግዥ የመሳሰሉትን ለመሸፈን ያስችላሉ። ይህ ደግሞ አሁን አሁን እያደገ የመጣውን የኑሮ ውድነት ለማቅለል እንደ አንድ ስትራቴጂክ አቅም ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

ከዚህ አንጻር፤ እያንዳንዱ ዜጋ በእጁ ያሉ ዕድሎችን አውቆ እና ተረድቶ ሊጠቀምበት ይገባል፤ የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማትም የዜጎችን ጥረት ከመደገፍ ባለፈ፤ ጥረቶቹ የተሻለ ውጤታማ የሚሆኑበትን አስቻይ ሁኔታ በመፍጠር መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። መልካም ግዜ።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# በእናት ጥላ ስር

መልካምሥራ አፈወርቅ

### ትናንት...

ወይዘሮዋ ከዓመታት በፊት የነበራት መልካም ትዳር ለዛሬው ሕይወቷ አይረሴ ትዝታ ነው። የዛኔ ከውድ ባለቤቷ ጋር ብዙ ውጥኖች ነበሯት። ሦስት ልጆቻቸውን በወጉ ሊያሳድጉ፣ ጎጇቸውን በእኩል ሊመሩ፣ ሲያቅዱ ቆይተዋል። ሁለቱም ቤታቸውን በ‹‹አንተ ትብስ እኔ›› ይመራሉ። የጥንድነት ሕይወታቸው የጋራ ኑሯቸውን አጣምሮ፣ ትዳራቸውን አድምቆታል።

ወይዘሮ ትዕግስት ታርቆ ጥሩ ይሏት የቤት እመቤት ነች። ባለቤቷ በወዝ በላቡ ደክሞ የሚያመጣውን ገቢ በወጉ አብቃቅታ ልጆች ታሳድጋለች፣ ቤት ጓዳዋን ትመራለች። አባወራዋ ለፍቶ አዳሪ ጎልማሳ ነው። በበቂ ልምድ የዘለቀበት የጎሚስታ ሥራ መተዳደሪያው ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል።

አንዳንዴ በሹፍርናው ሙያ ሥራ ባገኘ ጊዜ ራቅ ብሎ ይጓዛል። እንዲህ ማድረጉ ቤቱን ደጉሞ ልጆች ለማሳደግ ነው። ለእሱ ከትርፍ ጊዜው የሚገኘው ገቢ ለጎጆው ተጨማሪ እጅ ሆኖታል። ሁሌም ባለው ላይ ለማከል አቅሙ ነው። ቤቱን ደጉሞ የጎደለውን ይሞላበታል።

ባልና ሚስት ሁለት ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅን አፍርተዋል። እንደ ወላጅ ስለ ልጆቻው ብሩህ ነገ ብዙ ያስባሉ። ዛሬን አልፈው ካሰቡት ለመድረስ የእናት አባታቸው ድጋፍ የግድ ይላል። ይህ ይሳካ ዘንድ ሁሌም የአቅማቸውን ይደክማሉ። ለሁሉም ከራሳቸው ቀንሰው እንደፍላጎታቸው ይሞላሉ። ለጥንዶቹ የመጀመሪያው ፍሬ ወንዱ ልጃቸው ነው። ከእሱ ቀጥሎ ቆንጅዬ ሴት ልጅ አግኝተዋል። የእሷ ተከታይ ሌላው ወንድ ልጅ ሦስተኛ ሆኖ ይቆጠራል።

### ሁለተኛዋ ልጅ...

ቤተልሔም ለቤቱ ብቸኛዋ ሴት ልጅ ነች። ቆንጆና ዓይነግቡ ይሏት ቀልጣፋ። ቤቲ አጋጣሚ ሆኖ የተወለደችው በቤት ውስጥ ነበር። የዛኔ እናት ትዕግስት ድንገቴ ምጥ ባጣደፋት ጊዜ ሆስፒታል ለማድረስ እንዳልተቻለ ታስታውሳለች። እናም ከቤት ልትወለድ ግድ ሆነ ። በወቅቱ ታዲያ ሕጻንዋን አንስቶ እትብቷን ለመቁረጥ የፈጠነ አልነበረም።

እናት ሁነኛ ሰው ደርሶ ጉዳዩ እስኪከወን ጥቂት ደቂቃዎች መቆጠራቸውን አትዘነጋም። በግዜው ግን ‹‹ምጡን እርሺው ልጁን አንሺው›› እንዲሉ ሆኖ እናትና ልጅ የገጠማቸው ችግር አልነበረም። ሁሉም በሠላም ተጠናቀቀ። እናት ልጇን በፍቅር አቅፋ ሳመች። የአራስነት ግዜ በወጉ አለፈ። ትንሿዋ ልጅ መሳቅ፣ መጫወት፣መቦረቅ ያዘች።

ሕጻንዋ ስድስተኛ ወሯን እንደያዘች ግን ያልታሰበው ሆነ። ወላጆቿና መላው ቤተሰብ በእሷ ዕድሜ ሊሆኑ የማይገባቸውን የጤና ማጣት ምልክቶች አስተዋሉ። የሚሹትን አካላዊ ለውጥ አለማየታቸው ደግሞ ይበልጥ ሥጋታቸውን ጨመረው። ቤቲ እንደሌሎች አይደለችም። በወጉ የመተንፈስ ችግር አለባት። አንገቷን ሰቅዞ የያዘውና በግልጽ የሚስተዋለው አካላዊ ተፅዕኖ ነፃ እንዳትሆን እያገዳት ነው። መላልሶ የያዛት ጉንፋንና ትኩሳት አቅሟን አዳክሞታል። ከተወለደች በኋላ ሐኪሞች ደጋግመው ቢያዩዋትም የጤና ችግር ስለመኖሩ አልገለጹም።

ጉዳዩ ያሳሰባቸው ወላጆች ወደ ጤና ጣቢያ በወሰዷት ግዜ ከፍተኛ ክትትል እንደሚያስፈልጋት ተነገራቸው። የተጻፈላቸውን የሕክምና ማስረጃ ይዘው በፍጥነት ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አመሩ። ሆስፒታሉ ተገቢውን ምርመራ እንዳጠናቀቀ በተለየ ችግር የ‹‹ልብ ክፍተት›› ስለመኖሩ አረጋገጠ። ወላጆች ይህን ካወቁ በኋላ ሕክምናውን በተለየ ትኩረት ገፉበት።

ስድስተኛ ወሯን ያጠናቀቀችው ሕጻን አሁንም ከነችግሯ ቀጠለች። ወር አልፎ ወር ሲተካ አካላዊ ለውጥ አልታየባትም። የአንደኛ ዓመት ልደቷን ሻማ ካበራች በኋላ ሁሉም ቤተሰብ ማደግ መለወጧን ናፈቀ። እሷ ግን እንደ እኩዮቿ አልሆነችም። እያደር መቀጨጭ፣ መከሳቷ ቀጠለ። አሁንምየ ወላጆቿ ጭንቀት በኀዘን፣ትካዜ ታጀበ።

ከቤቲ ቀጥሎ ሦስተኛው ልጅ ተወለደ። ታናሿዋ መሆኑ ነው። እሱ ዕድሜውን ይዞ ዕድገቱን ቀጥሏል ። እንደ ታላቅ እህቱ እየከሳ፣ እየቀጨጨ አይደለም። የእሷም ታላቅ ቢሆን ተለየ ችግር የለውም። ያለአንዳች እንከን ጤነኛ ሆኖ አድጓል። አሁንም እናት አባት መጨነቃቸው አልቀረም። ስለሴት ልጃቸው ጤንነት አጥብቀው አሰቡ፣ ተከዙ።

እናት ትዕግስት ከሕክምናው ባለፈ ለልጇ የቻለችውን ለማድረግ ሮጠች። ፀበል እያመላለሰች አስጠመቀቻት፣ የፍላጎቷን ለመሙላትም የአቅሟን ጣረች፣ ለፋች። ሁሉም እንደታሰበው አልሆነም። የቤቲ ጤና አልተመለሰም። አሁንም ወላጆች ዓይናቸው ከልጃቸው ላይ አልተነሳም። በየግዜው ሆስፒታል ከመመላለስ አልተቃቡም።

### ተስፋ...

ውሎ አድሮ ቤቲ አካላዊ ለውጥ ታየባት። እንደ እድሜ እኩየቿ ከፍ ማለቷን ያዩ ቤተሰቦች ፈገግታቸው ተመለሰ። ይህን ተከትሎ የቀጠለው ሕክምና ግን ሌላ ችግር ስለመኖሩ አመላከተ። ከልቧ ችግር ጋር የሳንባዋ ግፊት አይሏል። እንዲህ መሆኑ የታሰበውን የልብ ቀዶ ሕክምና ለመከወን አያስችልም። በዓይኖቿ ላይ የተገኘው የሞራ ግርዶሽም እይታዋን ማዳከም ጀምሯል። ይህ እውነታ ችግሮች በነበሩበት እንዲቀጥሉ አስገደደ።

አሁን ልጆቹ እያደጉ ነው። ሁሉም ትምህርት ቤት ገብተው መማር ጀምረዋል። ባልና ሚስት እነሱን በወጉ ለማሳደግ ያጎደሉት የለም። እናት ከቤት፣ አባወራው ከውጭ እየሠሩ ለጎጇቸው ጽናት ይጥራሉ። ቤቲም በአካባቢያቸው ከሚገኝ ትምህርት ቤት ገብታለች። ለዘለቄታዊ መፍትሔ በውጭ አገር የተገኘላት ሕክምና በተስፋ እየተጠበቀ ነው። የውጭ ጉዞው ከተሳካ ጤናዋ ይመለሳል፣ ችግሮች ይቀላሉ።

### የቀን ጎዶሎ...

የቤቱ አባወራ ዛሬም ርቆ ሊሄድ ተነስቷል። አንዳንዴ ከጎሚስታ ሙያው በተጓዳኝ የኮንትራት ሥራ ካገኘ መኪና ይዞ ይጓዛል። ለዚህ ደግሞ የዓመታት የሹፍርና ልምዱ አሳፍሮት አያውቅም። እንዳሻው አገር እያቋረጠ ይመልሰዋል። እንዲህ ማድረጉ ቤቱን ለመደጎም፣ ጎዶሎውን ለመሙላት ነው። አሁን ደግሞ የጉዞ መስመሩ በሰሜን አቅጣጫ ከወሎ ምድር አውሎታል።

አባወራው መሪውን ጨብጦ መኪናውን እያሽከረከረ ነው። ከቤቱ ሲመለስ ለሚስት ለልጆቹ ሊደርግ ያቀደውን ያስባል፣ የአሁኑን ከትናንቱ፣ የዛሬውን ከነገ እያዛመደ ብዙ ርቋል። ከፊት፣ ከኋላው ከግራ ከቀኙ ‹‹ሸው›› የሚሉ መኪኖች ያልፉታል። እሱም እንዲሁ ቀድሟቸው ይፈተለካል። ይህ እውነት የየዕለቱ የመንገድ ላይ ልማድ ነው።

ከደቂቃዎች በኋላ እሱን አልፈው የሄዱ ሾፌሮች የሆነውን አስተውለው ወደመኪናው ቀረቡ። እርዳታ ለማድረግ ዘግይተው ነበር። አባወራው ሾፌር ከነመኪናው ተገልብጦ ሕይወቱ አልፏል። ማግስቱን የባለቤቷ አስከሬን ተጭኖ የመጣላት ወይዘሮ የምትይዝ የምትጨብጠውን አጣች። በአንዴ ነገሮች ተለወጡ፣ ቀኑ ጨለመባት።

አሁን ድንገቴው የመኪና አደጋ እሷን ያለአጋር፣ ልጆቿን ያለአባት አስቀርቷል። ይህን እውነት አምኖ መቀበል ግድ ቢላትም ፈጥና በይሁንታ የምትስማማበት አልሆነም። ሦስት ልጆችን ለብቻዋ ማሳደግ ቀላል አልነበረም። እንዲያም ሆኖ አስከፊ የጨለማ ቀናትን ማለፍ፣ ፊታኙን የችግር ድልድይ መሻገር የግድ አላት። ልጆቿን እንደ እናትም፣ እንደአባትም ሆና ማሳደግ የእሷና የእሷ ግዴታ ብቻ ነው።

### ከአምስት ዓመት በኋላ ...

እነሆ! ይህ ታሪክ ካለፈ ዘንድሮ አምስት ዓመታት ተቆጠሩ። እነዚህ ያለፉ ጊዜያት ለወይዘሮዋ መልከ ብዙ ገጽታዎች ናቸው። ጎዶሎ ሞልታ የልጆቿን ፍላጎት ለማሳካት ራሷን እንደሻማ አቅልጣለች። ለምግብ እንጂ ለሥራ ያልደረሱ ልጆቿን በወጉ ለማሳደር እጅ እግሯን ለሥራ፣ አእምሮዋን ለበዛ ሀሳብ አጋልጣ ብዙ ለፍታለች።



ትዕግስት ባለቤቷን በድንገቴ ሞት ካጣች በኋላ ስለልጆቿ መኖር ያልሆነችው የለም። የባለቤቷ ሥራ ጊዜያዊ ነበር። ቀድሞ የቤት እመቤት ናትና ከእጇ ያኖረችው ሽራፊ ጥሪት በቤቷ የለም። የወሰደችው አማራጭ በጉልበቷ ሠርታ ልጆቿን ማኖርና ማስተማር ነው። ልብስ እያጠበች፣ በየቤቱ ሽሮ በርበሬ እያዘጋጀች ሕይወትን መግፋት፣ ኑሮን መቋቋም ግዴታዋ ሆነ።

ዛሬም ቢሆን ልጆቿ ደርሰው እናታቸውን ‹‹አለንልሽ፣ አይዞሽ›› የሚሏት አልሆኑም። አሁንም በእሷ ስር አድረው እጆቿን የሚሹ የነገን ተስፋ የሚጠብቁ ናቸው። ከምንም በላይ ግን የሴት ልጇ ጉዳይ ለእናት ትዕግስት አሳሳቢ ሆኗል። የጤናዋ ነገር ዛሬም መፍትሔ አልባ ነው።

ቤቲ አሁን የአስራ ሰባት ዓመት ወጣት ሆናለች። እንዲያም ሆኖ እንደ ዕድሜ እኩዮቿ ትሆን ዘንድ ዕድሉ የላትም። ዛሬም በልብ ሕመም እየተሰቃየች ነው። በዓይኗ ሞራ ምክንያት ርቃ መሄድ አይቻላትም። እናቷ ለእርሷ ልክ እንደምርኩዝ፣ ከዘራዋ ናት። ያለእሷ ድጋፍ የትም መሄድ መራመድን አትሞክርም።

እስካሁን የተሻለ ሕክምና ያለማግኘቷ የጤናዋን ጉዳይ አሳሳቢ አድርጎታል። በውጭ አገር ተይዞላት የነበረው የሕክምና ቀጠሮ ዛሬም ድረስ አልተሳካም። እንዲህ ሆኖ እናቷን ለኀዘን እሷን ለብስጭት ዳርጓታል። ወይዘሮዋ ሁሌም ባለቤቷን ባሰበች ቁጥር ብቸኝነት ይሰማታል። እሱ በሕይወት ቢኖርና ከጎኗ ቢቆም የዛሬው ሸክም የእሷ ብቻ አይሆንም። ይህን ስታስብ ውስጧ በኀዘን ይሰበራል።

ቤቲ የየዕለት እንቅስቃሴዋ በድካም የተሞላ ነው። ብዙ መራመድና ርቆ መሄድ ይከብዳታል። በየግዜው ነስር አያጣትም። የዓይኖቿ ሞራ መልበስ ደግሞ ችግሯን አብሶታል። ዘወትር ከጎኗ የማትርቀው እናት ሁሌም ድካሟን ታውቀዋለች። እንደ ልጅነቷ ግን ልታዝላት፣ ልታቅፋት አትችልም። ቀን ከሌት ሠርታ ከምታገኘው ገንዘብ የትምህርቷ ክፍያ እንዳይቋረጥ እንደጣረች ነው። ለዘንድሮ ግን ይህን መቀጠል የሚቻላት አይመስልም። የክፍያው መጨመር አቅሟን አንገዳግዶታል። የዓይኖቿ መታመምም እንዲሁ።

ለቤቲ ታላቅና ታናሽ የሆኑት ሁለት ወንድሞቿ እርስ በርስ ቅርበት አላቸው። ሁሌም አብረው ይጫወታሉ፣ ይውላሉ። ቤቲ የአካል እንጂ የአእምሮ ችግር የለባትም። በፍጹም ጤንነት የሚሆነውን ሁሉ ታውቃለች። አርቃ ታስባለች፣ ስለነገዋ ታልማለች። አእምሮዋ ሠላም በሆነ ጊዜ ደስተኛ ናት። ፊቷ በፈገግታ ይበራል።

አንዳንዴ ግን ወንድሞቿ እሷን የሚረዷት፣ የሚገነዘቧት ባልመሰላት ጊዜ ውስጧ በብስጭት ይሞላል። ሁኔታቸው በእጅጉ ያተክናታል። ስለምን የሚለው ጥያቄም በልቧ እየተመላለሰ ትፈተናለች፣ ትናደዳለች። ይህ ስሜት ሁሌም ወንድሞቼ እኔን አይረዱኝም ከሚል እውነት ላይ እንዳደረሳት እናቷ ትዕግስት በኀዘኔታ ትናገራለች።

### ጥቂት ከቤቲ ጋር ...

ቤተልሔም ሞሱን ያገኘኋት እንደሁልጊዜው ሁሉ ከእናቷ ጋር ሆና ነበር። ስሟን አስተዋውቃኝ ጨዋታ ከመጀመራችን የቀደመ ፍላጎቷን ለማወቅ አልቸገረኝም። የቤቲ የመጀመሪያ ቃል ‹‹ጤንነቴ እንዲስተካከልልኝ እፈልጋለሁ›› የሚል ነበር። በዚህ መነሻ የቀጠለው ቆይታ በተለየ ብሶት የተሞላ ነበር። ቤቲን አተኩሬ አስተዋልኳት። ለዓይን የሚቀል ስሜትን ታጋባለች። ቃሏ መልካም የሚባል ነው፣ ንግግሯ ፈጽሞ አይከብድም።

ግራ ቀኝ ሰቅዞ የያዛት የአንገቷ ላይ ችግር በግልጽ ይስተዋላል። ማጅራቷ ላይ የበቀለው ውብ ፀጉር ደግሞ ለዓይን በሚስብ መልኩ ዙሪያውን ተጎዝጉዟል። በሁኔታው እንደገረመኝ ፊቴን ወደ እሷ አዞርኩ። በዓይኖቿ ተቀብላኝ ንግግሯን ካቆመችበት ቀጠለች። አሁንም ሆድ እንደባሳት፣ እንደከፋት ነች። ቤቲ አፍታ ሳትቆይ ዓይኖቿ በዕንባ ተሞሉ። እይታዋ እናቷ ላይ ነበርና የምትለውን ልረዳው አልቸገረኝም። ‹‹እናቴ ስለኔ የሆነችልኝን ሩብ ታህል መሆን አልችልም። ድኜ፣ ሰው ሆኜ ውለታዋን መመለስ እፈልጋለሁ››

በዓይኖቿ ያቆቱት ትኩስ እንባዎች በፊቷ ተዘርግፈው በአንገቷ መውረድ ጀመሩ። በቻልኩት አቅም የእናት ደግነት ግዴታ ጭምር መሆኑን ዘርዝሬ ላሳምናት ሞከርኩ። እውነቱን ለመናገር ሁኔታዋ እኔን ጭምር እየረበሸኝ፣ ከልቤ እያዘንኩ ነው። እሷ በተለይ በዚህ ዓመት የመዳን ፍላጎቷ ጨምሯል። ይህ ባለመሳካቱ ግን ብስጭት፣ ንድድ እንደሚያደርጋት ስትነግረኝ በተለየ ስሜት ሆነ። የምትለውን ሁሉ በጥሞና አዳመጥኳት።

አሁን ይበልጥ ሆድ እየባሳትና ውስጧ በኀዘን እየነደደ ነው። በየዓመቱ ስለራሷ እንደምትሳልና ስለቷ ለምን እንደማይደርስ ራሷን መጠየቅ ያዘች። ወዲያው ደግሞ ብሶቷ አይሎ ተበሳጨች። ይህ ሁሉ ውስጧ ተከማችቶ የኖረ ኀዘን መሆኑ አልጠፋኝም።

ቤቲ ሕጻን ሳለችና በአሁን ዕድሜዋ ስሜቷ ይለያያል። የዛኔ ከእኩዮቿ ጋር ያለአንዳች ስጋት ትጫወት ነበር። አሁን ላይ ግን ሁሉም እንደራቋትና እንደማያወሯት ሆኖ ይሰማታል። ከወንድሞቿ ጋር ያላት ግንኙነትም ከዚህ አይለይም። መቼም ‹‹አይረዱኝም፣ አይሰሙኝም›› ስትል ታስባለች። ቤቲ ስለእነሱ ተስፋ ቆርጣለች። እንዲህ አይነቱ እውነት እያደር ፍራቻን ፈጥሮባታል። አንድ ቀን እናቷን ብታጣት የሚሆነውን ስታስብ ደግሞ ሞት ቀድሞ እንዲወስዳት አጥብቃ ትመኛለች።

### ያልተመለሰው ጥያቄ

ብሶተኛዋ ልጅ ሁሌም በውስጧ አንድ ጥያቄ ይመላለሳል። ‹‹የእኔ የልብ ክፍተት ለምን አይገጥምም? ለምንስ ሕክምናውን አግኝቼ በቶሎ አልድንም? ራሷንም፣ ሐኪሞቿንም ደጋግም ትጠይቃለች። ይህ ጥያቄ በማንነቷ ዓለም መመላለስ የያዘው ወጣትነቷ በጀመረ ማግስት ነበር። አሁን ያለችበት ዕድሜ ብዙ እንድታስብ እንደእኩዮቿ አርቃ እንድታልም እያስገደዳት ነው።

ቤቲ ከትናንት ይልቅ ዛሬ ላይ የመኖር ፍላጎቷ ጨምሯል። ቢያንስ የዓይኗ ላይ ሞራ ቢነሳላት ተስፋዋ እንደሚለመልም ታውቃለች። አንዱ ሕመሟ ለሌላው አለመዳን ሰበብ ሆኖ ግን ዓመታትን ያለመፍትሔ አስቆጥሯታል። በአንድ ወቅት የደም ናሙናዋ ወደ እስራኤል ሀገር ተልኮ ውጤቱን በጉጉት ስትጠብቅ ነበር። ጥቂት ቆይቶ ግን ሁሉም እንዳልተሳካ ተነገራት።

ይህ አይነቱ አጋጣሚ ውስጧን ሰብሮ ተስፋዋን ያጨልመው ያዘ። ‹‹በቃ! አልድንም›› ይሉትን ስሜት እንዳትርቀው ምክንያት ሆነ። ቤቲ ከምንም በላይ የእናቷ ጉዳይ ውስጧን ያባባዋል። በምድር ላይ ያለቻት ብቸኛ ተስፋዋ ነችና ሕይወትን ያለእሷ ማሰቡ ይቸግራታል። ከፍቅሯ ብዛት በእጅጉ ትሳሳላታለች፣ ሁሌም ልፋት ድካሟ ዘልቆ ይሰማታል።

ቤቲ ባለባት ተደራራቢ የጤና ችግር ፍቅርና እንክብካቤ ያሻታል። በዚህ ክፍተት ግን እሷ በየቀኑ ሆድ እየባሳት ነው። ‹‹እናቴን በድንገት ባጣትስ ይሉት ስጋት ደግሞ ዕንቅልፍ ነስቷታል። ስለእናቷ ውለታ ብዙ ታስባለች። በሆነችላት ልክ ባይሆንም ነገን ልታሳርፋት፣ ልታስደስታት ትመኛለች። እናቷ ለእሷ ከቃል በላይ ነች። በትንፋሿዋ የምትፈውሳት መድኃኒቷ፣ ኖሯ የምታኖራት ጥላ ከለላዋ።

# የባቡር ትራንስፖርትንና ሎጂስቲክስ አገልግሎትን ለማዘመን ያለመው ሪፎርም

**ማሕሌት አብዱል**

ኢትዮጵያ ወደ ብልፅግና ለመሸጋገር ለምታደርገው ጉዞ የባቡር መሠረተ ልማት ወሳኝ የልማት አንቀሳቃሽ እንደሆነ ታምኖበታል። በመሆኑም ዘርፉን ለማሳደግ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን በማከናወን ላይ ትገኛለች። በሀገር ውስጥ የተጀመሩ የልማት ሥራዎች እንዲሳለጡና ከዓለም ጋር ያላትን የንግድ ትስስር የሚያቀላጥፍና የሚያሳድግ እንደመሆኑም አሁን ያለውን የባቡር መሠረተ ልማት በእጅጉ ለማዘመን ቆርጣ ተነስታለች። ለዚህም እንዲረዳ ስትራቴጂካዊ የሆኑ የአሠራር ሂደቶችን፣ ሕግና መመሪያዎችን በማሻሻል ጭምር እየተንቀሳቀሰች ነው።

በሌላ በኩልም በሀገሪቱ እየተመዘገበ ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስቀጠል የባቡር መሠረተ ልማቱን ከማዘመን ጎን ለጎን የሎጂስቲክ አገልግሎቱንም አቅም በእጅጉ ማጎልበትና አሁን ከሚታይበት የተንዛዛ አሠራር ማላቀቅ ወሳኝ መሆኑም እንዲሁ ታምኖበታል። ለዚህ ደግሞ በተለይም በዘርፉ የተሻለ ተሞክሮ ካላቸው ሃገራት ልምድ መውሰድ ተገቢ እንደሆነ እሙን ነው።

የኢትዮጵያ የባቡር ትራንስፖርት ከሕግ ማዕቀፍ፣ ከመዋቅርና ከአሠራር ሥርዓት እንዲሁም ከፋይናንስ እጥረት ጋር በተያያዙ ችግሮች ምክንያት ለሃገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት የሚገባውን ሚና መጫወት አለመቻሉን የዘርፉ ተዋናዮች ይናገራሉ።

በተለይም እየመጣ ካለው ፈጣን እድገትና ፍላጎት ጋር የሚመጥን አገልግሎት በመስጠት ረገድ በዘርፉ ከፍተኛ የሆነ የአቅም ውስንነት መኖሩን፣ ደረጃውን የሚጠብቅ መሠረተ ልማት ያለመዘርጋቱ፣ የተርሚናል ግንባታ በሚፈለገው መጠን ያለመከናወኑ፣ ዘመኑ በሚጠይቀው ልክ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የሚመራ አለመሆኑ እንዲሁም የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓቱ ጠንካራ ያለመሆኑ ዘርፉን ወደኋላ የጎተተው መሆኑ ይጠቀሳል። በተጨማሪም ተቋማዊ የሆነ የቴክኒካል አደረጃጀት፣ ግልፅና ተጠያቂነት የታከለበት የአሠራር ሥርዓት ያለመዘርጋቱና ገለልተኛ ተቆጣጣሪ አካል ያለመኖሩም ለዘርፉ ያለማደግ በምክንያትነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው።

መንግሥት በዘርፉ የሚስተዋሉትን ውስብስብ ችግሮች መፍታት ያስችለው ዘንድ በተለያዩ ጊዜያት የአሠራር ማሻሻያዎችን አድርጓል። አሁንም ይህንኑ ቀጥሎበታል። ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በባቡር ትራንስፖርቱም ሆነ በሎጂስቲክ አገልግሎቱ ላይ የሚስተዋሉትን ክፍተቶች ነቅሶ የለየና የመፍትሔ አቅጣጫንም ጭምር ያስቀመጠ የሪፎርም ሰነድ አዘጋጅቶ ከሰሞኑ ይፋ አድርጓል።

ይህም በባቡር መሠረተ ልማት ላይ የሚደረገው ሪፎርም ኢትዮጵያ ከምሥራቅ አፍሪካ ሃገራት ጋር ያላትን ሁሉን አቀፍ ግንኙነት በእጅጉ የሚያጠናክር፤ በዓለም ገበያም ተወዳዳሪ ሆና እንደትቀጥል የሚያግዛት እንዲሁም አጠቃላይ የትራንስፖርት ዘርፉን በከፍተኛ ደረጃ የሚያዘምን ይሆናል ተብሎም ተስፋ ተጥሎበታል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሩ ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር) ሪፎርሙን አስመልክቶ በቅርቡ በተካሄደ መድረክ ላይ እንደተናገሩት፤ በባቡር ትራንስፖርት ዘርፉ ላይ የሚደረገው ሪፎርም የንግድ ሥርዓቱን ለማዘመን፣ አቅም ለማጎልበት፣ ከሃገራት ጋር ያለውን የትራንስፖርት ትስስር ለማጠናከር እንዲሁም ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ልማት በምሥራቅ አፍሪካ ሃገራት እንዲመጣ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ኢትዮጵያ እንደሃገር በዘርፉ ሪፎርሙን ማካሄዷ ፈጣን እድገቷን በማስቀጠል ብልፅግናዋን እውን ለማድረግ ያስችላታል ተብሎም ይጠበቃል።

በዘርፉ የሚስተዋሉት ውስብስብ ችግሮች ኢትዮጵያ በሃገር በቀል ኢኮኖሚ መርሐ ግብሯ ዜጎቿን ከድህነት ለማላቀቅ ለምታደርገው ብርቱ ጥረት በተለይም ደግሞ በገቢና ወጪ ንግዱ ስኬታማነት ላይ ተግዳሮት ሆነው መቆየታቸውን ዓለሙ (ዶ/ር) ያመለክታሉ። በባቡርና በመንገድ ዘርፉ ላይ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር ጥናት መደረጉንና በዚያ ጥናት መሠረት ለሃገሪቱ ወሳኝ የሚባል ሪፎርም ለማድረግ መታሰቡን አስታውቀዋል።

«ሎጂስቲክስ የአንድ ሃገር የደም ስር ነው፤ ሎጂስቲክስ ከሌለ ኢኮኖሚው ሕይወት ሊኖረው አይችልም» የሚሉት ሚኒስትሩ፤ በተለይ የውጭ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ




መጥተው ኢንቨስት ለማድረግ ከሚያይዋቸው ወሳኝ ጉዳዮች አንዱ የሎጂስቲክስ ዋጋ መሆኑን ያመለክታሉ። በዚህ ረገድ በተለያዩ ምክንያቶች በኢትዮጵያ ያለው የሎጂስቲክስ ግንዛቤ ደካማ መሆኑ፤ አሠራሩም የዘመነ ባለመሆኑ ኢንቨስትመንቱን በሚፈለገው ልክ መሳብ አለመቻሉን ያስረዳሉ።

በተለያዩ ጊዜያት ዘርፉን ለማዘመን በርካታ ማሻሻያዎች ቢደረጉም ውስብስብና በርካታ ችግሮች ያሉባቸው በመሆናቸው ውጤት ማምጣት አልተቻለም ሲሉም ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት ዘርፉን ለማሻሻል ባቡርና መንገድ ጭነት አገልግሎት ላይ ትኩረት ያደረገ ጥናት መደረጉን፤ ጥናቱም አዳዲስ የመፍትሔ ሃሳቦችን መያዙን ያመለክታሉ።

በጥናቱ ከተለዩ ችግሮች መካከል በተለይ አሁን ያለው የባቡር መስመር በሙሉ አቅሙ መሥራት አለመቻሉ ዋነኛው ችግር መሆኑን ጠቅሰው፤ «ካሉን ባቡሮች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት እየሠሩ አይደሉም» ይላሉ። ይህም የሆነው ከውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር በተያያዘ አነስተኛ መለዋወጫዎች አምጥቶ መጠገን ባለመቻሉ እንደሆነ ያብራራሉ።

ከዚህም ባሻገር በአገልግሎት ላይ ያሉትም ባቡሮች በተፈቀደላቸውና መሄድ ባለባቸው ፍጥነት ልክ እንደማይንቀሳቀሱ ይናገራሉ። «መንገዱ አጥር ወይም መከለያ ስለሌለው ባቡሩ የሚያልፈው በአብዛኛው በአርብቶ አደርና በአርሶ አደር አካባቢዎች በመሆኑ ሰውና እንስሳ እየገባበት አንዳንድ አደጋዎች እየደረሱ የሚቆምበት ሁኔታ አለ» ሲሉ አብራርተዋል። አደጋውን ተከትሎም የሚነሳው የካሣ ጥያቄ የባቡሩን እንቅስቃሴ እያስተጓጎለው መሆኑን አመልክተው፣ የባቡር ኦፕሬተሮች ቀስ ብለው ለመሄድ መገደዳቸውን ያስረዳሉ። «በሰዓት 120 ኪሎ ሜትር መሄድ የሚገባው ባቡር 40 ኪሎ ሜትርና ከዚያ በታች ለመሄድ ይገደዳል፤ ይህም የአገልግሎቱን ቅልጥፍና ገድቦታል» በማለትም አስታውቀዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ የባቡር ትራንስፖርቱ ችግር የቅልጥፍና ብቻ ሳይሆን በመጠንም በቂ አይደለም። የባቡር መስመሩ ሲገነባ የሎጂስቲኩን አብዛኛውን ሸክም ይይዛል ተብሎ ቢታሰብም፣ አሁን ላይ ድርሻው ከ14 በመቶ አይበልጥም። አሁንም 86 በመቶ የሚሆነው እቃ በተሽከርካሪ እየተጫነ ነው ያለው። በመሆኑም የዘርፉን ቅልጥፍና በመጨመር ውጤታማ ለማድረግ ለዚህ ደግሞ ተጨማሪ ተዋናዮችን መጨመር በሚያስችል መልኩ ጥናቱ እንዲካሄድ ተደርጓል።

«ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋ በፍጥነት እያደገ ያለች ሃገር ናት፤ በዚሁ ልክ የወጪና ገቢ ምርት መጠን እየጨመረ ነው፤ አሁን ባለው ሁኔታ ይህንን ሊያስተናግድ የሚችል የሎጅስቲክ ሥርዓት የለንም» የሚሉት ዓለሙ (ዶ/ር)፤ በተለይም ጅቡቲ እቃዎች ደርሰው በጭነት አገልግሎት ችግር ቶሎ ያለመጫን፤ የተጫነውም በታሰበበት ቦታ ያለመድረስ ሁኔታዎች ዘርፉ እንዳይዘምን ተግዳሮት እንደሆነ ያስረዳሉ።

በተመሳሳይ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች በተለይም የቡና እና አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በከፍተኛ ደረጃ መጨመራቸውን ጠቅሰው፣ ሎጂስቲክሱ በሚያድገው ኢኮኖሚ ልክ ማደግ እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል፤ ኢኮኖሚውን መምራት በሚችልበት አቅም ላይ ሊደርስ እንደሚገባም ያስገነዝባሉ። ሪፎርሙ ያስፈለገውም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ ነው የጠቆሙት።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ በሃገሪቱ የጭነት ተሽከርካሪዎች ቁጥር አነስተኛ መሆኑም ሌላው አጠቃላይ የሎጂስቲክ አገልግሎቱ ቅልጥፍና እንዳይኖረው ያደረገ ምክንያት ነው። የሎጂስቲክስ የአሠራር ሥርዓቱ ያለመዘመኑና ዲጂታላይዝ ያለመደረጉም አገልግሎቱ የተንዛዛ እንደሆን አድርጎታል።

«ዘርፉ የኦፕሬሽን ብቻ ሳይሆን የሕግ ማዕቀፍ፣ የአደረጃጀትና የፋይናንስም ችግር አለበት» የሚሉት ሚኒስትሩ፤ በመሆኑም ሚኒስቴሩ ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር ባካሄደው ጥናት እነዚህንና ሌሎች በዘርፉ ያሉ ችግሮችን በዝርዝር ለመዳሰስ ጥረት መደረጉን ያመለክታሉ። በጥናቱ ላይ ከመንግሥት ተቋማት ባሻገር ከግሉ ዘርፍ ተዋናዮች ጋር ውይይት የሚደረግበትና ግብዓት የሚሰበሰብበት መሆኑን ጠቅሰው፣ እንደ ዓለም ባንክ ያሉ የልማት አጋሮችም መፍትሔ እንዲመጣ እገዛ ያደርጋሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

ይሁንና ችግሩ በዋናነት ሊፈታ የሚችለው የግል ባለሃብቱ በስፋት ዘርፉን ሲቀላቀል እንደሆነ ዓለሙ (ዶ/ር) ይናገራሉ። «የባቡር መስመሩም አሁን ባለው የኢትዮ-ጅቡቲ ኮርፖሬሽን ብቻ ኢትዮጵያ ያለመችውን እድገት ማምጣትም ሆነ በባቡር ዘርፍ ልታገኘው የሚገባትን የሎጂስቲክና ትራንስፖርት አገልግሎት ሊያሟላ አይችልም፤ ተጨማሪ ኦፕሬተር ከሃገር ውስጥም ከውጭም እንዲገባ የማበረታታት ሥራ እንሠራለን» ሲሉም ጠቁመዋል። በተባበረና በተቀናጀ መልኩ ካልተሠራ ለውጥ ሊመጣ እንደማይችል ተናግረው፣ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በሚደረገው ሪፎርም ሚናቸውን እንዲወጡም ጥሪ አቅርበዋል።

በዓለም ባንክ የኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ዳይሬክተር ማርያም ሳሊም በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ባቡር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ዘርፉ የሚስተዋለው ችግር በወጪና ገቢ ላይ እያሳደረ ካለው ጫና ባሻገር በወደፊቱም የሃገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ላይ አሉታዊ ጫና የሚያሳርፍ ነው። ኢትዮጵያ ከጠቅላላ የሃገር ውስጥ ምርቷ 30 በመቶ የሚሆነውን ለሎጂስቲክስ ታወጣለች። ይህ የሎጂስቲክስ ወጪ በኢኮኖሚያቸው ካደጉት ሃገራት በላይ ሲሆን፣ ይህም በሃገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ይገኛል። የተንዛዛውና ያልዘመነው የሎጂስቲክስ አሠራር በተለይም የግብርና እና ኢንዱስትሪው ዘርፎች ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ተጨማሪ ወጪ በየዓመቱ እንዲያወጡ ያደርጋል።

«በዘርፉ የሚታየው ችግር ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ምርት ወጪዋ ውድ እንዲሆንና በውጭ ባለሃብቶች ተመራጭ እንዳይሆን አድርጎታል» የሚሉት ዳይሬክተሯ፤ ለዚህም የአሠራር ሥርዓቱ ያለመዘመን ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ አስታውቀዋል። በተለይም ግልፅነትና ተጠያቂነት የተላበሰ ተቋማዊ አሠራር ያለመፈጠሩ ሃገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እያሳጣት ስለመሆኑ ይጠቁማሉ። በመሆኑም ሪፎርሙ አጠቃላይ የሎጂስቲክስ ዘርፉንም ሆነ የባቡር መሠረተ ልማቱን ዘመኑና ዓለም በደረሰችበት ሥልጡን ደረጃ ማሳደግ ወሳኝ መሆኑን ነው ያስገነዘቡት።

መብራቱ ደለለኝ (ዶ/ር) የኢትዮ-ጅቡቲ አክሲዮን ማኅበር የኦፕሬሽን ዘርፍ ኃላፊ ናቸው። እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ አክሲዮን ማኅበሩ ባለፉት ስድስት ዓመታት ሲገነባ ከታለመለት ዓላማ አንፃር የሚጠበቅበትን ያህል መሥራት አልቻለም። በእነዚህ ዓመታት በቻይና ኮንትራክተር ሲተዳደር የነበረ ነው፤ ካለፈው ዓመት ጀምሮ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ በኢትዮጵያውያን እየሠራ ሲሆን ካለፉት ሁለት ወራት ወዲህ ደግሞ የሪፎርም ሥራዎች እየሠራን ነው። ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት አክሲዮን ማኅበሩ የሚጠበቅበትን ዓላማ እንዲያሳካና ትርፋማ እንዲሆን ለማድረግ የሦስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የመጀመሪያው የሪፎርሙ ሥራ ተቋማዊ መዋቅር መሥራት እንደሆነ ጠቁመው፣ «በአሁኑ ወቅት ተቋሙን መሸከም የሚችል የሰው ኃይል የማደራጀት ሥራ እየተሠራ ነው። በተጨማሪም የአጭር ጊዜ ስትራቴጂክ እቅድ የተዘጋጀ ሲሆን በዚህም ከትራንስፖርት አገልግሎቱ ባሻገር በአጭር ጊዜ ኢንቨስት የሚደረጉ ፕሮጀክቶችን ቀርፀናል» በማለትም ይናገራሉ።

ለባቡር ከተገዙ የኤሌክትሪክ ሎኮሞቲቮች ውስጥ በአሁኑ ወቅት እየሠሩ ያሉት ከግማሽ በታች በመሆናቸው እነዚህን መለዋወጫዎች ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ማስገባት አንዱ የአጭር ጊዜ ፕሮጀክት እንደሆነ ያስረዳሉ። በተመሳሳይ በናፍጣ የሚሠሩትንም ወደ ሥራ ማስገባትና ለዚያ የሚያገለግሉ ግብዓቶች ከውጭ እንዲመጡ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ አብራርተዋል።


በተጨማሪም ቢዝነሱን ከማስፋት አንፃር አዳዲስ ፕሮጀክቶች መጀመራቸውን ጠቅሰው.« አሁን ላይ እየሰጠን ያለነው የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤ ነገር ግን በሪፎርሙ ባቡሩን በመጠቀም ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶችን ቀርፀን እንዲካተቱ አድርገናል» በማለት ይናገራሉ። ከዚሁ ጎን ለጎን የሎጂስቲክ አገልግሎቱን በተቀናጀና በተሳለጠ መልኩ ለመሥራት የሚያስችሉ የአሠራር ማዕቀፎች መዘጋጀታቸውን ይጠቁማሉ። እስከአሁን በሃገሪቱ የመልቲ ሞዳል ኦፕሬተር ለሌሎች ኩባንያዎች ዝግ ነበር፤ አሁን መንግሥት ባመቻቸው ዕድል በመጠቀም መልቲ ሞዳል ኦፕሬተር ለመሆን አቅደን እየተንቀሳቀስን እንገኛለን» ሲሉም አመልክተዋል።

«እስከአሁን ድረስ በዘርፉ ከነበሩ ተግዳሮቶች መካከል ዲጂታላይዝ ያለመሆኑ አንዱ ነው፤ ይህንንም ለመቀየር የሚያስችሉ ሥራዎች ተጀምረዋል። በተለይም ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለን ግንኙነት ዲጂታላይዝድ ባለመሆኑ ወደብ አካባቢ ከፍተኛ መጨናነቅና በተገልጋዮች ላይ የሚፈጠር ጫና አለ» ይላሉ። በመሆኑም የአሠራር ሥርዓቱ ዲጂታላይዝ መደረጉ በደንበኞች የሚቀርበውን ቅሬታ ለመፍታት የሚያስችል እንደሆነም ተናግረዋል። በባቡር መስመሮች ላይ ያሉትን መሠረተ ልማቶች በሦስት ዓመት ውስጥ በማሻሻል አገልግሎቱን የማዘመን ሥራ እንደሚከናወን ይጠቁማሉ።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ባቡር ወደብ አልባ ለሆነች ሃገር እንደወደብ ይቆጠራል። በዚህ ረገድም ሃገሪቱ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው ግብዓት የሚመጣው በጅቡቲ ኮሪደር ነው፤ ለዚህ ደግሞ ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ ያለው የአዲስ ጅቡቲ መስመር ነው። ይህ ኮሪደር የሃገሪቱ ገቢና ወጪ የሚንቀሳቀስበት መስመር እንደመሆኑ ሎጂስቲክሱን የማዘመን ሥራ መሠራቱ በሃገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል። በመሆኑም የተሳለጠ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ለመስጠት በተለይም እንደማዳበሪያና ዘይት ያሉ ወሳኝ ግብዓቶች በሚፈለገው ፍጥነትና ሁኔታ እንዲገቡ ለማድረግ የተቋሙን አቅም የማሳደግ ሥራ ይሠራል። ለዚህም አዲስ የከባድ ካርጎ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት ተጠናቋል፤ በቅርቡ ይጀምራል። ይህም ከዚህ በፊት ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት በ50 በመቶ ይጨምራል ተብሎ ይጠበቃል።

በሌላ በኩል ሃገሪቱ ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢዋ 30 በመቶ ለሎጂስቲክስ ዘርፉ ወጪ ታደርጋለች ሲባል አንደኛው ምክንያት ከጊዜ አጠቃቀም አኳያ እንደሆነ ያስረዳሉ። በመሆኑ በሪፎርሙ ትልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ ከውጭ የሚገቡትም ሆነ የሚላኩ እቃዎች በወደቦች ላይ ያላቸውን ቆይታ ማሳጠር ዋነኛው እንደሆነ ያመለክታሉ። ይህም የሎጂስቲክስ አገልግሎት ወጪን እንደሚቀንስ ይጠቁማሉ። «ለባቡር ፍጥነት መቀነስ ተግዳሮት የሚሆኑትን የሠላምና ፀጥታ ጉዳይ፤ የኃይል አቅርቦትና ከካሣ ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት እየሠራን ነው» በማለት ተናግረዋል።

# ስፖርት



## የዋልያዎቹን የአፍሪካ ዋንጫ ተስፋ የሚወስኑ ፍልሚያዎች

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) በ2025 የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ሦስተኛ እና አራተኛ የምድብ ጨዋታዎች ዛሬና በመጪው ማክሰኞ ከጊኒ ብሔራዊ ቡድን ጨዋታዎች ለ23 ተጫዋቾች ጥሪ አድርገው የሀገር ውስጥ ዝግጅታቸውን አጠናቀው ከቀናት በፊት ወደ ኮትዲቯር አቅንተዋል፡፡

ዛሬ በገለልተኛ ሜዳ አቢጃን አላሳኔ ኦታራ ስቴዲየም ምሽት 1፡00 ሰዓት የሚጀመረው የሁለቱ ቡድኖች ጨዋታ በ2025 በሞሮኮ በሚካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ ለመቅረብ ያላቸውን ተስፋ የሚወስን ሲሆን፣ ዋልያዎቹ ከ2021ዱ የካሜሩን አፍሪካ ዋንጫ በኋላ ወደ ውድድሩ ለመመለስ ይፋለማሉ፡፡

ኢትዮጵያና ጊኒ እኤአ ከ1976 ጀምሮ ሰባት ጊዜ የተገናኙ ሲሆን ዋልያዎቹ ማሸነፍ የቻሉት አንዱን ብቻ ነው፡፡ ይህም እኤአ 2002 ላይ በሜዳቸው 1 ለምንም ያሸነፉበት ሲሆን ቀሪዎቹን ስድስት ጨዋታዎች ጊኒ ድል አድርጋለች፡፡ ከነዚህ ድሎች መካከል ጊኒ ሦስቱን በሜዳዋ ነበር ማሸነፍ የቻለችው፡፡ ሁለቱ ቡድኖች በቅርቡ ባለፈው መጋቢት ባደረጋቸው ሁለት ጨዋታዎች ጊኒ 3ለ2 እና 2ለ0 ማሸነፏ ይታወሳል፡፡

ኢትዮጵያ በዚህ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ኳስና መረብ ማገናኘት ካልቻሉ አምስት ሀገራት አንዷ ነች። ባለፉት ሁለት የማጣሪያ ጨዋታዎቿ 19 ጊዜ ካደረገቻቸው የግብ ሙከራዎች አንዱ ብቻ ነው ለግብ የቀረበ የነበረው። ይህ የቡድኑን የግብ ሙከራ ንፃሬ 5 በመቶ ብቻ ሲሆን በማጣሪያው ከሚሳተፉ ሀገራት ሁሉ ዝቅተኛው ነው። ይህም የዋልያዎቹን የአጥቂ ችግር የጎላ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

ጊኒ ከኢትዮጵያ ጋር ባደረገቻቸው ጨዋታዎች የበላይነት ቢኖራትም ከሁለት ወር በፊት በጊዜያዊነት ከተሾሙት ፈረንሳዊው አሰልጣኝ ቻርልስ ፓኩዊል ጋር ባለፉት ሦስት ጨዋታዎች ማሸነፍ አልቻለችም፡፡ በተለይም ባለፉት አራት የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያዎች አንድም ማሸነፍ አልቻለችም። ሦስት ተሸንፍ አንዴ የአቻ ውጤት አስመዝግባለች። ለመጨረሻ ጊዜ ያሸነፈችውም መጋቢት 2023 ላይ ኢትዮጵያን 3ለ2 ነበር። ዋልያዎቹ በተለይም ከአጥቂ ችግር ጋር በተያያዘ ከተጋጣሚያቸው ጊኒ በባሰ መልኩ የተዳከሙበት ወቅት ላይ መገኘታቸው እንጂ የጊኒን የበላይነት ለመቀልበስ ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነበር፡፡ ያም ሆኖ የአሠልጣኝ ገብረመድኅን ስብስብ አሁንም በነዚህ ሁለት ጨዋታዎች አንድ ነገር ፈጥሮ ወደ ድል በመመለስ የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎውን ተስፋ የማለምለም ዕድሉ ከእጁ አልወጣም፡፡

አሠልጣኝ ገብረመድኅን ከቀናት በፊት ሁለቱን ጨዋታዎች በተመለከተ የመጨረሻውን መግለጫ በሰጡበት ወቅት ለአፍሪካ ዋንጫ ለማለፍም ሆነ ላለማለፍም ወሳኝ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ ‹‹በሁለት ቀን ልዩነት ነው ጨዋታውን የምናደርገው። የአንድ ቀን እረፍት ነው የሚኖረው። በዚህ ሁለት ጨዋታ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የመግባታችን ጉዳይ የሚወሰን ይሆናል። በድምር ውጤት የምናገኘው ተስፋ ሰጪ ነው አይደለም የሚለውን ነገር በዛው ጨዋታ ላይ ነው የምናየው። በዚህ በድምር የምናገኘው በተለይ ተጋጣሚያችንን ጥሎ ከማለፍ አንፃር ጥሩ ጠቀሜታ ስላለው የግድ የምንሄደው ለማሸነፍ ነው። ያለን ዕድል ማሸነፍ ነው። ሌላ ዕድል አይኖረንም። ምክንያቱም ከዚህ በኋላ የሚቀሩ ጨዋታዎች ሁለት ናቸው። ስለዚህ በሁለቱ ጨዋታዎች ደግሞ እኛ የምናገኘው ታንዛኒያን እና ዲሞክራቲክ ኮንጎን ነው። ስለዚህ ከባድ ሊሆን ይችላል ብለን እናስባለን። በእርግጥ በሜዳችን ብንጫወት ኖሮ ታንዛኒያን በሜዳችን እናገኛለን ብለን እናስብ ነበር፣ ነገር ግን አሁን አናገኝም ስለዚህ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው። ስለዚህ አሁን ይሄንን ሁለት ጨዋታ በተመሳሳይ ሀገር ነው የምንጫወተው፣ ምናልባት ከተማው ሊቀያየር ይችላል ግን ዞሮ ዞሮ ለሁለታችንም አንድ ነው። እነሱ ከሜዳቸው ውጪ ነው እኛም ከሜዳችን ውጪ ነው የምንጫወተው እና በዚህ በድምር ውጤት የምናገኘው ውጤት ያው ሊያሳልፈንም ሊጥለንም ስለሚችል ማድረግ የሚገባንን ሁሉ ያለንን አቅም አሟጥተን ተጫውተን አሸንፈን ተስፋችንን ለማብራት ጥረት እናደርጋለን። በማለት ገልፀዋል፡፡



ዋልያዎቹ 3ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ የምድብ ማጣሪያ ጨዋታ ዛሬ ጊኒን አቢጃን አላሳኔ ኦታራ ስቴዲየም ይገጥማሉ፣

ኢትዮጵያ በማጣሪያው ከሁለት ጨዋታ አንዱን በዲሞክራቲክ ኮንጎ 3ለ0 ተሸንፍ ከታንዛኒያ ጋር ደግሞ 0ለ0 ተለያይታ በአንድ ነጥብና ሦስት የግብ ዕዳ ከምድቧ ሦስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ጊኒ ከሁለቱ የማጣሪያ ጨዋታዎቿ በዲሞክራቲክ ኮንጎና ታንዛኒያ ተሸንፋ አንድም ነጥብ ሳትይዝ የመጨረሻውን ደረጃ ይዛለች። ዲሞክራቲክ ኮንጎ ሦስቱንም ጨዋታዎቿን በማሸነፍ ምድቧን በዘጠኝ ነጥብ ስትመራ ታንዛኒያ በአራት ነጥብ ትከተላለች።

---

## ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአሥራ አምስት ቀኑ የሚታተም

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# የጡት ካንሰር ግንዛቤ ማስጨበጫ ወር

**ኢያሱ መሰለ**

በዓለም ላይ በገዳይነታቸው ከሚታወቁ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አንዱ ካንሰር ነው። ከካንሰር አይነቶች በተለይም የጡት ካንሰር የሴቶችን ሕይወት ከመንጠቅ አንጻር ከሌሎች ሕመሞች ሁሉ የከፋ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣውን የጡት ካንሰር ለመከላከል ዓለምአቀፉ የጤና ድርጅት (WHO) የተለያዩ ፕሮግራሞችን ቀርጾ ወደ መሬት በማውረድ ሕመሙ በሰዎች ላይ በተለይም በሴቶች ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ለመግታት ከዓመት እስከ ዓመት በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። በተለየ ሁኔታ ደግሞ መላው የዓለም ሕዝብ ስለሕመሙ ግንዛቤ እንዲጨብጥና እራሱን ለጡት ካንሰር ሕመም አሳልፎ እንዳይሰጥ በዓመት አንድ ጊዜ በወርሐ ጥቅምት የግንዛቤ ማስጨበጫ ንቅናቄ ይደረጋል።

በዚሁ መሠረት በኢትዮጵያም የጡት ካንሰር ከሌላው ጊዜ ሁሉ ትኩረት አግኝቶ ሰዎች ራሳቸውን ከበሽታው እንዲጠብቁ ከዓመት እስከ ዓመት ከሚሠራው ሥራ በተጨማሪ የጥቅምትን ወር የግንዛቤ ማስጨበጫና የተያዩ ተግባራት ማከናወኛ አድርጎታል፤ በዘንድሮው ዓመትም አምና እና ካቻምና ይደረግ እንደነበረው ሁሉ ወሩ የግንዛቤ ማስጨባጫ ተግባራት የሚከናወኑበት መሆኑን የኢፌዴሪ ጤና ሚኒስቴር አሳውቋል። ‹‹የጡት ካንሰርን ቅድመ ምርመራ በማድረግ እና በመታከም ሕይወትዎን ከጡት ካንሰር ይጠብቁ›› በሚል መሪ ሀሳብ የሚከበር እንደሆነም ተገልጿል።

በኢፌዴሪ ጤና ሚኒስቴር የበሽታ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ሕይወት ሰለሞን ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፤ የጡት ካንሰር ሴቶችን በከፍተኛ ደረጃ የሚገድል እና ያደጉትንም ይሁን በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮችን ልዩነት ሳይፈጥር ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚፈጥር የካንሰር አይነት ነው። በሽታው ፆታ ሳይለይ ሊያጠቃ እንደሚችል ይታመናል ያሉት ዶክተር ሕይወት ይሁንና በአመዛኙ የበሽታው ተጠቂ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው እንደሆኑ ጠቅሰዋል።



(ፎቶ ጸጋዬ ተስፋዬ)

ዶክተር ሕይወት ሰለሞን

በሀገራችን በየዓመቱ ከ16 ሺህ በላይ ሴቶች በጡት ካንሰር ይያዛሉ፤ በየዓመቱም ከ9 ሺህ በላይ የሚሆኑት ታማሚዎች ሕይወታቸውን በጡት ካንሰር ያጣሉም ብለዋል። ከአጠቃላይ የካንሰር አይነቶች አንጻር ሲታይ የጡት ካንሰር ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዝም ገልጸው ለጡት ካንሰር አጋላጭ ተብለው ከሚገመቱ ሁኔታዎች መካከልም በቂ እንቅስቃሴ አለማድረግ፣ አመጋገብን አለማስተካከል፣ ለጨረር ተጋላጭ መሆን፣ ሲጋራ ማጨስ ፣ አልኮል ማዘውተር እና ለበሽታው ተጋላጭ የሆኑ ሆሮሞኖችን ከወላጅ መውረስ እንደሆኑ ጠቃቅሰዋል።

የጡት ካንሰር ምንም አይነት ምልክትና ስሜት ሳያሳይ ከሰዎች ጋር ረዥም ጊዜ ተደብቆ ሊኖር እንደሚችል ጠቅሰው፤ ሰዎች ሕመሙ ይኑርባቸውም አይኑርባቸውም ቅድመ ምርመራ ቢያደርጉ ለጥንቃቄ እንደሚረዳቸውና ከስጋት ነፃ መሆን እንደሚችሉ ተናግረዋል። ቅድመ ምርመራ ባለማድረጋቸው ምክንያት ከ65 እስከ 70 በመቶ የሚሆኑት ታካሚዎች ደረጃው ከፍ ያለ ካንሰር ይዘው ወደ ጤና ተቋም እንደሚመጡ ተናግረዋል። ታካሚዎች በወቅቱ ወደ ጤና ተቋማት እንዳይሄዱ እንቅፋት ከሚሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ስለበሽታው ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን እና ምርመራና ሕክምና የሚሰጡ የጤና ተቋማት በበቂ ሁኔታ አለመኖራቸው እንደሆኑ ይጠቅሳሉ።

ይህን ችግር ለመቀልበስም ስትራቴጂ ቀርጾ በማኅበረሰቡ ላይ ግንዛቤ የመፍጠር እና በተመሳሳይ የጤና ባለሙያዎችን ግንዛቤ ከፍ የማድረግ ሥራዎች የሚሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

የጡት ካንሰር ቅድመ ምርመራ ማድረግ የሕክምና ውጤትን ከማሻሻሉም በተጨማሪ የመኖር ዕድልን ከፍ የሚያደርግ ነው ያሉት ዶክተር ሕይወት የግንዛቤ ማስጨበጫ ንቅናቄው ሴቶች አስቀድሞ የመመርመር ባሕል እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው ብለዋል። በተጨማሪም ሰዎች በተለይም ሴቶች በጡታቸው ላይ የሚታዩ ምልክቶች ሲኖሩ በፍጥነት ወደ ጤና ተቋማት በመምጣት በባለሙያ የታገዘ ክትትል እንዲያደርጉ የሚያነቃ እንደሆነም ገልጸዋል።

እንደጤና ሚኒስቴር የጡት ካንሰር ሕመምን ከመከላከል አንጻር ውጤት ለማስመዝገብ የዓለም ጤና ድርጅት ባስቀመጠው መመሪያና ትልም መሠረት በተያዘው በጀት ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የጡት ካንሰር መመሪያ ተጠናቆ የማስተዋወቁ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ አብራርተዋል። ከዚሁ ጎን ለጎን የሥልጠና እና የአሠልጣኞች ማኑዋልም አልቆ በተያዘው ጥቅምት ወር መሠረታዊ ሥልጠና ለመጀመር የቅድመ ዝግጅት ሥራ እንደተሠራ አስረድተዋል።

በመሆኑም የቅድመ ምርመራ ልየታ ሥራ በመጀመሪያ ደረጃ ጤና ተቋማት ላይ በማስፋት የሪፈራል ሊንኬጅ እና ምርመራ እንዲሁም ሕክምናን በማጠናከር የጡት ካንሰር ውጤትን የተሻለ ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል። የተለያዩ የካንሰር በሽታዎችን ለመከላከልና ለማከም በርካታ የአቅም ማጎልበት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከነዚህም መካከል ዘመናዊ የጨረር ሕክምናን የማስፋፋት ሥራ ከስድስት ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ጋር በመሆን ግንባታና ማሽን ተከላ ተጠናቆ በከፊል ወደ ሥራ መገባቱን ተናግረዋል።

የካንሰር መድኃኒቶች በሀገራችን የአቅርቦት ሠንሠለታቸው ተጠብቆ በተገቢው መንገድ ለተጠቃሚው የሚደርስበትን ለማገዝ መንግሥት በየዓመቱ ከ150 ሚሊዮን ብር በላይ በመመደብ የታካሚዎቹን የመድኃኒት ወጪ ለማገዝ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝም ጠቅሰዋል።

በሽታው ስር ከመስደዱ በፊት በየጊዜው ጡትን በእጅ በመዳሰስና ቅድመ ምርመራ በማድርግ የጡት ካንሰርን ቀድሞ መለየትና መከላከል ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነም ተናግረዋል። በተለይም ሴቶች ጡታቸው ላይ ለውጥ ሲያስተውሉ ወደ ሕክምና ተቋማት በመሄድ ተጨማሪ ምርመራ በማድረጉ ላይ መዘናጋት እንደሌለባቸው አሳስበዋል። ጤና ሚኒስቴር የጡት ካንሰር የሚያደርሰውን ሞት እና ሕመም ለመከላከል የሚያደርገው ጥረት በኅብረተሰቡ የሚደገፍ ሲሆን የተባለውን ውጤት ማምጣት ይቻላል ያሉት ዶክተር ሕይወት በሚዲያ፣ በጤና ተቋማትና በተለያዩ አግባቦች የሚሰጠውን ግንዛቤ የማስጨበጫ ትምህርት ሰዎች ተከታትለው ተግባራዊ እንዲያደርጉ አሳስበዋል።

የጡት ካንሰርን ለመከላከል በሚደረገው ጥረትም የሚዲያ አካላት፣ አጋር ድርጅቶችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ዶክተር ሕይወት ጥሪ አስተላልፈዋል። በቀጣይ ዶክተር ሠላማዊት አየለ በተመሳሳይ ጉዳይ የሰጡትን ሀሳብ ይዘንላችሁ የምንቀርብ ይሆናል።